አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት

በ

ወንድወሰን ሞላ

ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ ጥናት
የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ**

**የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል**

**የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር**

# በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ጥናት

**በ**

**ወንድወሰን ሞላ**

**ለአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያ ጥናት የቀረበ ጥናት**

**አማካሪ**

**ሰላማዊት መካ**

**ረዳት ፕሮፌሰር**

**ሰኔ 2007 ዓ.ም.**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

# ምስጋና

*በመጀመሪያ ይህንን ያደረገ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡ ጥናቴን ጀምሬ እስክፈጽም የሰራሁትን በማንበብ፣ አቅጣጫዎችን በመጠቆም እና ስህተቴን እንዳርም በማድረግ ላልተለዩኝ አማካሪዬ ሰላማዊት መካ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡*

*የዩኒቨርሲቲ ቆይታዬን ሸጋ ያደረክልኝ እና በክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ውጪ ላይም በርካታ ጉዳዮችን ያስተማርከኝ መምህሬ ቴዎድሮስ ገብሬ ለጥናቴ የሚጠቅሙኝን መጣጥፎች እንዴትና ከማን እንደማገኝ መንገዱን አሳይተኸኛልና የህይወት መንገድህ ሁሉ ብርሀን ይሞላ! አመሰግናለሁ፡፡*

*ለጥናቱ ገንዘብ ሲያስፈልገኝ በተለያየ ጊዜ መሀረብሽን ያስፈታሁሽ የእኔ ትክክለኛ "ብርሀን" እናቴ ፀሐይ ተክሌ ምን ብዬ እንደማመሰግንሽ አላውቅም፡፡ እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ ይስጥልኝ፡፡ አብዛኛውን ጥናቴን በትእግስት እና በፍጥነት የተየብሽልኝ ሀና ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡ ጊዜና ገንዘብህን እንዲሁም ጉልበትህን ሳትሰስት ወደ መስክ አብረኸኝ ተጉዘህ ቪዲዮ በመቅረጽ፣ ፎቶ በማንሳት እና የተለያዩ ሐሳቦችን በማመንጨት ከጎኔ ያልተለየኸኝ ወንድሜ አንተነህ ይታይህ ይህ ያንተም ልፋት ውጤት ነው፡፡ አመስግኛለሁ!*

*መረጃ ለመሰብሰብ ለመሄድ ስነሳ የድምፅና የቪዲዮ መቅረጫችሁን እንደራሴ እንድጠቀም ለተባበራችሁኝ ጓደኞቼ ዘካርያስ ብርሀኑ እና ቤተልሔም ዘሩ አግዚአብሔር ይስጣችሁ፡፡ የተለያዩ ገንቢ ሐሳቦችን በማመንጨት የሞራል ድጋፋችሁ ያልተለየኝ ጓደኞቼ አገኘሁ አዳነ እና ዮሴፍ ቦኪ አመስገኛለሁ፡፡ በመስክ ወቅት መረጃ አቀባዮችን በማገናኘት፤ የተለያዩ መረጃዎችን በመስጠት ቤተሰባዊ ፍቅር ያሳያችሁኝ አባ ሰይፈ ሚካኤል እና አባ ወልደ ሚካኤል በእናንተው ስልት "የዘርዐ ያዕቆብ እመቤት" ትርዳችሁ፡፡ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ የሚያስፈልገኝን መረጃ የሰጣችሁኝ ሁላችሁ "እመብርሀን ትስጥልኝ"፡፡ በተለያየ ጊዜ የተጻፈውን በማተም እና የፊደል ስህተቶችን በማረም ያልተለየኸኝ ቶማስ ኃይሉ ከአክሱማዊት ጋር ምስጋናህን ተቀበል፡፡ "አይዞህ" "በርታ" እያልሽ የማይታይ፣ የማይዳሰስ፣ የማይታኘክ ግን የሚያጠግብና የሚያረካ የውስጤን ምግብ የሰጠሽኝ ፍቅረኛዬ ሎዬድ ደመና የራስ ሰው ባይመሰገንም አመስግኛለሁ፡፡*

*ለጥናቴ የሚያስፈልገኝን የንድፈ ሀሳብ መጽሐፍ ከቤተ መጻሕፍት አጥቼ ግራ ስጋባ ከቤትህ አምጥተህ እገለገልበት ዘንድ ያዋስከኝ እንዳለ ጌታ ከበደ ልባዊ ምስጋናዬ ይድረስህ፡፡ እንዲሁም በቀጥታም በተዘዋዋሪም ጥናቴን አጠናቅቅ ዘንድ በተለያየ መንገድ እገዛችሁ ያልተለየኝ እህቴ ትዕግስት ሞላ፣ ጓደኞቼ ጋሻው በቀለ እና ጭኮ ባይሳ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡*

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**


ምስጋና……………………………………………………………………………..3
አጠቃሎ……………………………………………………………………………..5
1. መግቢያ ........ 6
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 7
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 8
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 8
1.4. የምርምር ጥያቄዎች ........ 8
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 9
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 9
1.7. የጥናቱ ዘዴ ........ 9
1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........ 9
1.7.2. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 11
1.8. የመስክ ቆይታ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 11
1.8.1 የመስክ ቆይታ ........ 11
1.8.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ........ 14
2. ክለሳ ድርሳናት ........ 16
2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 16
2.1.1. ተረክ ........ 16
3. አካባቢያዊ ዳራ ........ 31
3.1. የሞጃና ወደራ ወረዳ አካባቢያዊ ገለጻ ........ 31
3.3. የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አጠቃላይ ገጽታ ........ 31
3.3.1. የገዳሙ አመሠራረት ........ 31
3.3.4. የገዳሙ ሥርዓት ........ 34
3.3.4.1. አለባበስ ........ 34
4. በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ትንተና ........ 38
4.1.1. የታቦቱ (የጽላቱ) ስደት ........ 38
5. ማጠቃለያ ........ 73
ማጣቀሻ ጽሁፎች ........ 76
አባሪ አንድ ተረኮች
አባሪ ሁለት ምስሎች
አባሪ ሶስት የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መረጃ
አባሪ አራት የተለያዩ ደብዳቤዎች

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮችን በመመርመር እና በመተንተን ለገዳሙና ለገዳማውያኑ ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት የቀረበ ነው፡፡ በጥናቱ ከቤተ መጽሐፍት መረጃዎች በተጨማሪ ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢ እና በገዳሙ ውስጥ ስለሚተረኩት ተረኮች በቃለ መጠይቅና በምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ለዚህ ጥናት አስር የመረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን ስድስቱ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በማስታወሻ፣ በምስል፣ በመቅረፀ ድምፅ እና እንደአስፈላጊነቱ በቪዲዮ ካሜራ ተይዘዋል፡፡ እነዚህን መረጃዎች በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብና በተረክ ንድፈ ሀሳብ ላይ በመመስረት ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስድስት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች እና የጥናቱ አካባቢም ተቃኝቷል፡፡

በጥናቱ በገዳሙ የሚነገሩ አርባ ሰባት ተረኮች የተሰበሰቡ ሲሆን ሃያው እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ(ይዘታቸውን መሰረት በማድረግ) ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ተረኮቹ የገዳሙ አመሠራረት፣ የገዳሙ ቅድስና፣ ትንቢት፣ መንግስትና ኃይማኖት እና ፈውስ በሚሉ ርዕሶች ቀርበዋል፡፡ በውጤቱም በገዳሙ የሚተረኩት ተረኮች ገዳማውያኑን በእምነታቸው ለማፅናት፣ የአካባቢው ነዋሪዎች የአካባቢያቸውን እድገት ከገዳሙ ጋር በማያያዝ የገዳሙ ጠባቂ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ የእምነቱ ተከታዮችም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ወደ ገዳሙ እንዲመጡ ለማድረግ፣ የገዳሙ ማህበረሰቦች የገዳሙን ህግና ሥርዓት እንዲጠብቁ ለማድረግ፣ የመንግስት አካላት ገዳሙ ለሚያስፈልገው ነገር ተባባሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ፣ ወዘተ. ፋይዳ እንዳላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

# 1. መግቢያ

እምነት የአማኞቹ ህልውና የሚመሰረትበት፣ በእምነቱ ተከታዮችና በልዕለ ተፈጥሮ ኃይላት መካከል ያለውን ቁርኝት የሚያሳይ የኃይማኖት መገለጫ ነው፡፡ በአብዛኛው የምናውቃቸው እምነቶች ደግሞ መሰረታቸውን የሚያፀኑት በተረኮቻቸው ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ተረኮችን ማጥናት የማኅበረሰቡን ስነ ልቡናዊ እና ማኅበረሰባዊ ማንነት ለመረዳት ያስችላል፡፡ ተረኮች ከሚገኙባቸው ስፍራዎች መካከል ገዳማት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህ ጥናት የተከናወነውም በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን፣ ፋይዳቸውን በማሳየት ነው፡፡

ይህ ጥናት በአምስት አበይት ክፍሎች ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱን አጠቃላይ ገፅታ ማስተዋወቂያ ሲሆን፤ በውስጡም መግቢያ፣ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ዘዴ እንዲሁም የአጥኚው የመስክ ቆይታ የሚሉ ጉዳዮች በውስጡ ይዟል፡፡

ሁለተኛው ክፍል ጥናቱን ለማከናወን የሚረዱ ንድፈ ሀሳባዊ ዳሰሳ የተካሄደበት ሲሆን በውስጡም ተረክ፣ የተረክ ዓይነቶች፣ ተረክን የማጥናት አስፈላጊነትና የአጠናን ስልት እንዲሁም ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቀርበዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ስድስት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፎች ተዳሰዋል፡፡

በሶስተኛው ክፍል ደግሞ የተጠናው ገዳም አካባቢያዊ ዳራ የቀረበበት ሲሆን በውስጡም የሞጃና ወደራ ወረዳ አካባቢያዊ ገለጻ እና በሞጃና ወደራ ወረዳ የሚገኙ ቅርሶች የሚሉ ርዕሶች አሉት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አጠቃላይ ገጽታ በሚለው ርዕስ ስር የገዳሙ አመሰራረት፣ የገዳሙ የአስተዳደር መዋቅር፣ የልማት ስራዎች፣ የገዳሙ ስርዓት(አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ጸሎት፣ ጥምቀት) እንዲሁም የገዳሙ የማስተናገድ አቅም የሚሉ ንዑስ ርዕሶች ቀርበዋል፡፡

አራተኛው ክፍል በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች የተተነተኑበት ነው፡፡ ከገዳሙ የተሰበሰቡት ተረኮች ከይዘታቸው አንጻር የአመሰራረት ተረኮች፣ የስፍራው ቅድስና፣ ትንቢታዊ ተረኮች፣ መንግስትና ኃይማኖት እንዲሁም ፈውስ በማለት በአምስት ንዑሳን ርዕሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

አምስተኛው ክፍል የማጠቃለያ ክፍል ሲሆን የጥናቱ አጠቃላይ ውጤት እና ተረኮቹ ለገዳሙና ለገዳማውያኑ ያላቸው ፋይዳ ጠቅለል ባለ መንገድ የቀረበበት ነው፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ኃይማኖታዊ ፎክሎርን መዝሙር፣ ተረክ፣ እምነት፣ ስርዓት፣ መድኃኒት፣ አለባበስ፣ ጥበብ በመሳሰሉ ዘውጎች መክፈል እና ማጥናት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ኃይማኖታዊ ፎክሎር ኃይማኖታዊ እና ከኃይማኖቱ ውጪ ያሉ ልማዳዊ ጉዳዮችን የምንመረምርበት በመሆኑ እንደ እምነት እና ሌሎች ትውፊታዊ ጉዳዮች ያሉት በሁሉም ዘውጎች ሊንፀባረቁ ስለሚችሉ ክፍፍሉን አስቸጋሪ ያደርገዋል (Danielson, 1986: 52-53)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Dorson "ኃይማኖታዊ ፎክሎርን በዘውግ ከፋፍሎ ማጥናት አስቸጋሪ ነው፤ ኃይማኖታዊ ፎክሎርን በዘውግ ስንከፋፍል የኃይማኖት ዋና ጉዳይ የሆነው እምነት እንቅፋት ይፈጥራል" (1972: 219) በማለት የDanielsonን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡ ኃይማኖታዊ ፎክሎርን ለማጥናት ስንነሳ ትኩረት ማድረግ ያለብን እምነት ላይ ሳይሆን ተረኩ ላይ መሆን እንዳለበትም ይገልፃሉ (1972: 219)፡፡

የተለያዩ የታሪክ ባለሙያዎች፣ የመንፈሳዊ ትምህርት ልሂቃን፣ የፎክሎር አጥኚዎች ወዘተ… በአገራችን የሚገኙ ኃይማኖቶችን በተለይም ክርስትና፣ እስልምና እና የተለያዩ ሀገር በቀል እምነቶችን በየመስካቸው አጥንተዋል፡፡ የፎክሎር ተማሪዎች የተለያዩ ገዳማትና አድባራትን ቁሳዊ ባህል፣ የበዓል አከባበር ክዋኔ፣ የገዳማት አመሰራረትና ከገዳማቱ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮች እና የገዳም ስርዓቶች ላይ ምርምር አካሂደዋል፡፡ እንዲሁም ስርዓተ ቅዳሴ፣ ስርዓተ ግንዘት፣ የመዝሙር ግጥሞች፣ የቆሎ ትምህርት ፎክሎራዊ ገጽታዎች፣ መንዙማዎች ወዘተ… ተጠንተዋል፡፡ ገዳማት ላይ በማተኮር ከተሰሩት አብዛኞቹ ጥናቶች ከገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችን ከቁሳዊ ባህል እና ከገዳሙ ስርዓት ጋር በአንድነት ያጠኑ ናቸው፡፡ የሚጠናው ማኅበረሰብ በተረኮቹና በቁሳዊ ባህሎቹ አማካኝነት ከየት መጣነቱን፣ ማንነቱን፣ ዕምነቱን፣ ባህሉን እና አስተሳሰቡን እንደሚገልፅ ከጥናቶቹ ማወቅ ይቻላል፡፡ ነገር ግን እስካሁን በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ተሰብስበው ጥናት አልተካሄደባቸውም፡፡

በመሆኑም ይህን ክፍተት በማየቴና አንዳች የመነሻ ሃሳብ ለማኖር ተረኮች ከገዳሙ ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህ የተሰበሰቡ ተረኮችም ከሚጠሯቸው ንድፈ ሃሳቦች ጋር ተገናዝበው

ተመርምረዋል፣ ተተንትነዋል፡፡ ለገዳሙና ለገዳማውያኑ ያላቸው ፋይዳም ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በተለያዩ ምክንያቶች ጥቂት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትን የመጎብኘት ዕድል ገጥሞኛል፡፡ በተደጋጋሚ ካየኋቸው ገዳማት መካከል በሰሜን ሸዋ፣ ሞጃና ወደራ ወረዳ የሚገኘው ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አንዱ ነው፡፡ በገዳሙ ውስጥ በልዕለ ተፈጥሮ እና በልዕለ ሰብእ ኃይል የተፈፀሙ ተብለው የሚነገሩ የአመሰራረት ተረኮች፣ የፈውስ ተረኮችና በገዳሙ ውስጥ ለሚከወነው ሥርዓት መነሻ የሆኑ ተረኮችን አድምጫለሁ፡፡ የስነ ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቴን ስከታተል ደግሞ ተረኮች ተሰብስበው ቢጠኑ የማኅበረሰቡን ስነ ልቡናዊም ሆነ ማኅበራዊ ማንነት ለማወቅ እንደሚረዱ ተገንዝቤያለሁ፡፡ ነገር ግን ባለኝ ዕውቂያ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ የሚነገሩ ተረኮችን መሠረት በማድረግ ምንም አይነት ጥናት አልተካሄደም፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተረኮች ተሰብስበው ቢጠኑ እንደሚጠቅም በማሰብ ይህንን ጥናት ለመስራት ተነሳሳሁ፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ለገዳሙ እና ለገዳማውያኑ ህይወት ያላቸውን ፋይዳ መፈተሽ፣ መመርመር እና መተንተን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ ጥናት ዋና ዓላማውን የሚያጐለምሱ ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አመሰራረትን በሚመለከት የሚነገሩ ተረኮችን መተንተን፣
- በገዳሙ ውስጥ ያሉ ሥርዓቶች የተመሰረቱባቸውን ተረኮች መመርመር፣
- በገዳሙ በሚነገሩ ተረኮች ውስጥ የዘለቁትን ሚታዊ ሀሳቦች መፈተሽ፣
- የገዳማውያኑን እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ትስስር በተረኮቹ አማካኝነት መመርመር ናቸው፡፡

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

- ➢ ገዳሙ እንዴት እና በምን ምክንያት ተመሰረተ?
- ➢ ተረኮቹ ከገዳሙ መመስረት ጋር ያላቸው ቁርኝት ምን ይመስላል?

- ➢ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች በገዳሙ ለሚኖሩት መናኒያን እና ለአካባቢው ማኅበረሰብ ምን ፋይዳ አላቸው?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት መተግበር በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩ መንፈሳዊ ተረኮች በገዳሙ ላሉ መናንያን፣ እና ምዕመናን ምን ያህል ለአኗኗራቸው መሰረት፣ ለአስተሳሰባቸው መገራት፣ እና በገዳሙ ውስጥ ለሚያከናውኗቸው ሥርዓቶች ማጠንጠኛ መሆናቸውን ለማወቅ ያስችላል፡፡ በገዳሙ ላይ ጥናት ያልተካሄደ በመሆኑ ይህንን ክፍተት ይሞላል፡፡ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ በተለያየ ዘርፍ ምርምር ለማካሄድ ለሚፈልጉ ተመራማሪዎች ተጨማሪ መረጃን በመስጠት ሊጠቅም ይችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሌሎች ገዳማት የሚነገሩ ተረኮችን ለማጥናት ለሚነሱ የፎክሎር ተመራማሪዎች መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ የሚነገሩ ተረኮችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን ለገዳሙ እና ለገዳማውያኑ ያላቸውን ፋይዳ በመመርመር ላይ ብቻ ይወሰናል፡፡ መረጃዎቹም በገዳሙ ውስጥ ከሚኖሩ ገዳማውያን፣ በገዳሙ አካባቢ ካሉ ነዋሪዎችና ስለገዳሙ ከሚያውቁ ሰዎች ተሰብስበዋል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ተረኮቹ በአብዛኛው የሚተረኩት እና አገልግሎት ላይ የሚውሉት በገዳሙ በሚኖሩ ማኅበረሰቦች እና በአካባቢው ነዋሪዎች በመሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ገዳሙን አስመልክቶ በርካታ ተረኮች ይነገራሉ፡፡ ነገር ግን ከሚነገሩት ተረኮች ውስጥ ለትንታኔ ይበጁኛል ባልኳቸው ላይ ብቻ ተወስኛለሁ፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዘዴ

### 1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

መረጃ የሰበሰብኩት ከቀዳማይ እና ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ነው፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮቹ በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሳት፣ ስለገዳሙ የሚያውቁ የአካባቢው ነዋሪዎችና ከገዳሙ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ካልዓይ የመረጃ ምንጮቹ ደግሞ ለጥናቱ የሚበጁ ንድፈ ሃሳቦች እና ጽንሰ ሃሳቦች፣ የተለያዩ መጻሕፍት፣ ስለገዳሙ የሚያትቱ ድርሳናት እና ልዩ ልዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው፡፡

ስለ ገዳሙ ከተጻፈ መጽሔት እንደተረዳሁት ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ምስረታው በ15ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቢሆንም ከ500 ዓመታት በላይ ተዘግቶ

ኖሯል፡፡ በሀያኛው መቶ ክ/ዘመን መጨረሻ ዳግመኛ አንድነት ገዳም ሆኖ የተከለለው በእግዚአብሔር ፈቃድና ለረጅም ጊዜ በዋሻ ውስጥ ይጸልዩ በነበሩ አባቶችና እናቶች ተነሳሽነት ነው (የገዳሙ መጽሔት፣ 1)፡፡

ስለዚህ ተረኮችን ለመሰብሰብ የገዳሙ አባቶችና እናቶች ላይ ብቻ መወሰኑ በቂ መስሎ አልታየኝም፡፡ ስለሆነም በገዳሙ ዳግመኛ የምሥረታ ሒደት አስተዋፅኦና እውቂያ ያላቸው ሶስት መነኮሳት እና በአካባቢው ተወልደው ለብዙ ዓመታት የኖሩ ስለገዳሙ ያውቃሉ የሚባሉ ሶስት አዛውንቶች ቁልፍ የመረጃ አቀባዮቼ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስለገዳሙ የሚያውቁ አራት ሰዎች አጋዥ የመረጃ አቀባዮቼ ናቸው፡፡ በፎክሎር ጥናት የመስክ መረጃዎች በምልከታ (observation) እና በቃለ መጠይቅ (interview) ሊሰበሰቡ ይችላሉ (Goldstein, 1964: 77)፡፡

ምልከታ ተመራማሪው በመስክ ስፍራው ተገኝቶ የሚከወነውን፣ የሚነገረውን እና አጠቃላይ መቼቱን በመመልከት እና በመስማት፣ የተመለከተውን ነገር በመመዝገብ በቦታው ለሌለና የመመልከት እድሉን ላላገኘ ሰው በጽሁፍ የሚያስቃኝበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ በአግባቡ ከተተገበረ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተሻለ ተጨባጭ መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችል ነው፡፡ በምልከታ ወቅት ከአይን እይታ በተጨማሪ ሁሉንም የስሜት ህዋሳቶቻችንን በሙሉ በማንቃት እና በማጣመር ስለተከወነው ነገርና ስለከዋኙ ወይም በአጠቃላይ ስለክወና ዓውዱ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ያስችላል (Goldstin, 1964: 77)፡፡

በምልከታ ጊዜ በተመራማሪው አዕምሮ የሚመላለሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች ከዋኔውን በመመልከት መልስ የማናገኝላቸው ከሆነ በተለያዩ የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴዎች የተሻለ መረጃን ማግኘት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ዘዴዎች መካከል አንዱ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡

የቃለ መጠይቅ ዘዴ ከክዋኔው አውድ ውጪ ሙሉ መረጃ ሊሰጥ ከሚችል እና ከሚታመንበት የመረጃ አቀባይ በጥያቄና መልስ ስለክዋኔው የተፈጠሩብንን ሁነቶች የምንጠይቅበት ዘዴ ነው፡፡ ተመራማሪው ሁለቱን ዘዴዎች አጣምሮ በአግባቡ የመጠቀም ክሂሉ የላቀ ከሆነ ብዙ መረጃን መሰብሰብ ይችላል (Goldstein, 1964: 77-78)፡፡

ለቃለ መጠይቅ ዘዴ የሚዘጋጁ ጥያቄዎች የተለያየ ቴክኒክ አላቸው፡፡ ክፍት ጥያቄዎች እና ዝግ ጥያቄዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ክፍት ጥያቄዎች የሚባሉት ተጠያቂዎች ነፃ ሆነው መረጃ የሚሰጡባቸው ቀድመው ያልተዘጋጁ ነገር ግን በቃለ ምልልሱ ወቅት የሚነሱ፣

ሁነቶች የሚጠሯቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ዝግ ጥያቄዎች ደግሞ ቁርጥ ያለ መልስ ለማግኘት የሚጠየቁ ጥያቄዎች ናቸው (ፈቃደ፣ 1991፣ 101)፡፡

በዚህም መሰረት ለጥናቴ የሚጠቅመኝን መረጃ ለማግኘት ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ዝግ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎችን አዘጋጅቻለሁ፡፡ ነገር ግን መስክ ላይ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር እንደነበረኝ ግንኙነት እና እንዳገኘሁት መረጃ ክፍት ጥያቄዎችን በማቅረብ መረጃዬን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በምልከታ እና ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰበሰቢያ ዘዴዎች የሚሰበሰቡ የመስክ መረጃዎች በቪዲዮና ፎቶ ካሜራ እንዲሁም መቅረፀ ድምጽን በመሳሰሉ አጋዥ መሳሪያዎች መታገዝ አለባቸው (Goldstein, 1964: 97-99)፡፡ ስለዚህ እኔም መረጃዎቼን ስሰበስብ በምልከታ ያገኘኋቸውን ለጥናቴ ያስፈለጉኝን በምስል አስቀርቻለሁ፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት እንደአስፈላጊነቱ የቪዲዮ/የፎቶ ካሜራ የተጠቀምኩ ሲሆን፣ ያደረኳቸውን ቃለ መጠይቆች ሁሉ በመቅረፀ ድምፅ በመቅረፅ ሰንጃለሁ፡፡

### 1.7.2. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከሰበሰብኩ በኋላ የምርምር ጥያቄዎቼን ለመመለስ እና የጥናቴን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመረጃ መተንተኛ ስልቴን መወሰን ነበረብኝ፡፡ ስለዚህም በዚህ ጥናት በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩት ተረኮች ለገዳሙ ሥርዓት እና ለገዳማውያኑ ህይወት ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ (Functional theory) የመተንተኛ ስልት አድርጌ ተጠቅሚያለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተረክ ንድፈ ሃሳብን (Narrative theory) ተገልግያለሁ፡፡

## 1.8. የመስክ ቆይታ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

### 1.8.1 የመስክ ቆይታ

ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት ማድረግ የሚገባኝን ቅድመ ዝግጅቶች አድርጌያለሁ፡፡ ስለተረክ እና ስለ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ፣ በገዳማት ተረኮች ላይ የተሰሩትን ጥናቶች እና ስለሚጠናው አካባቢ የተጻፉ ጽሑፎችን ከቤተ መጽሐፍት አንብቤያለሁ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስለ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚያውቁ ሰዎችን በማናገር ስለ ገዳሙ ቅድመ መስክ ግንዛቤ ጨብጫለሁ፡፡ ከዛም በቀን 18/05/07 ወደ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም በመሄድ የገዳሙን ሀላፊዎች በማግኘት

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እንደሆንኩኝ፣ በገዳሙ ተረኮች (ይትበሀሎች) ላይ ጥናታዊ ጽሑፌን ላከናውን እንደሆነ እና ምን ማሟላት እንዳለብኝ ጠይቄ፣ ህጋዊ ደብዳቤ ካመጣሁ እንደሚተባበሩኝ ነግረውኝ ተመልሻለሁ፡፡

በዚህም መሰረት ከትምህርት ክፍሉ በቀን 28/05/07 ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የትብብር ደብዳቤ ተጻፈልኝ፡፡ መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ደግሞ በቀን 29/05/07 ለሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ደብዳቤ ጻፉልኝ፡፡ በመሀል ትልመ ጥናቴን ሳዘጋጅ፣ ለጥናቴ የሚጠቅሙኝን ጽሑፎች ሳነብ እና ለመስክ የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች ሳሟላና ቅድመ ዝግጅቴን ሳደርግ ቆየሁ፡፡ በቀን 03/07/07 ከረዳቴ ጋር በመሆን ደብረ ብርሀን በመሄድ ሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በመንበረ ፓትርያርክ የተጻፈውን ደብዳቤ አስገባን፡፡ በሚያስመሰግን ፍጥነት የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ለጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ሰ/ጉ/ጽ/ቤት አስፈላጊውን ትብብር ያደርጉልኝ ዘንድ የፈቃድ ደብዳቤ ሰጥተውን ወደ ሰላ ድንጋይ አቀናን፡፡ አመሻሽ ላይ በመድረሴ ሰላ ድንጋይ ከተማ አድሬ በቀን 04/07/07 የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ ይዤ ወደ ገዳሙ ገባሁ፡፡ ገዳም ውስጥ እንደደረስኩኝ ተሳልሜ እና ጸሎት አድርጌ የገዳሙ ጽ/ቤት በመዝለቅ መጋቢውን(የገዳሙ ኃላፊ) አግኝቼ የመጣሁበትን አላማ አስረዳኋቸው፡፡ ከአሁን በፊት በተጠየኩት መሰረት ህጋዊ ደብዳቤውን ሰጠኋቸው፡፡ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተመካክረው ለመወሰን ለከሰዓት እንድመለስ ቀጠሮ ሰጡኝ፡፡ በቀጠሮዬ መሰረት ተገኝቼ ፈቃድ እንዳገኘሁና ጥናቴን መጀመር እንደምችል ተነገረኝ፡፡

ከገዳሙ ጥናቴን እንዳከናውን ፈቃድ እንደተሰጠኝ መረጃ አቀባዮቼን ወደ መምረጥ ገባሁ፡፡ ገዳሙ እንደገና የተቋቋመው በቅርብ በመሆኑ ከገዳሙ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉትን መጋቢው እንዲያዘጋጁልኝ በመንገር ከአካባቢው ማኅበረሰብ ደግሞ ስለ ገዳሙ የበለጠ መረጃ የሚሰጡኝን ለማወቅ መጠየቅ ጀመርኩኝ፡፡ በዚህ መሰረት በቀን 05/07/07 ጠዋት በደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤ/ክርስቲያን የሚያገለግሉትን አባ ወልደ ሚካኤልን ሳናግራቸው ስለገዳሙም ሆነ ስለ ቤተክርስቲያኑ እውቀት ያላቸው በአካባቢው ተወልደው ያደጉት መጋቤ-ስርዓት ደስታ ተክለ ወልድ እና ሊቀ ጠበብት ቤተ ማርያም እንደሆኑ ነገሩኝ፡፡ ሊቀ ጠበብት ቤተ ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ ስለነበሩ አገናኝተውን፣ የመጣንበትን ጉዳይ አስረድተን እኔ ጥያቄዬን ሳቀርብ እሳቸው አስፈላጊውን መረጃ ሲሰጡኝ ረዳቴ በቪዲዮ ካሜራ ቀርጾ ቆይታችንን አጠናቀቅን፡፡ ከዚህ በኋላ አባ ወልደ ሚካኤል ሌሎቹን የመረጃ አቀባዮች የማገኝበትን መንገድ

እንደሚያመቻቹልኝ ቃል ገብተውልኝ ስልክ ቁጥር ተለዋውጠን ወዳረፍኩበት ሆቴል አቀናሁ፡፡ የቀን ውሎዬን በመዝገብ ላይ አስፍሬ ጥያቄዎቼን መከለስ እና ስለገዳሙ ከሰማኋቸው መረጃዎች ጋር እያዛመድኩና እያስተካከልኩ ከረዳቴ ጋር ቀጣይ ውሎአችንን አቅደን እና የመቅረጫ መሳሪያዎቻችንን አስተካክለን አደርን፡፡

በቀን 06/07/07 በጠዋት ወደገዳሙ በማቅናት መረጃ እንዲሰጡን የተመደቡልንን ሰዎች አገኘን፡፡ እነሱ መረጃ እንዲሰጡን የተመረጡበትም ምክንያት በገዳሙ ውስጥ ካላቸው ኃላፊነት፣ ካላቸው የረጅም ጊዜ ቆይታ እና በገዳሙ ዳግም ምሥረታ ካላቸው እስተዋፅኦ እና እውቀት መሆኑን አረጋግጠን መረጃችንን መሰብሰብ ጀመርን፡፡ መጀመሪያ ቆይታ ያደረግነው ከባህታዊ ወልደ ማርያም ጋር ሲሆን የድምፅም ሆነ የቪዲዮ ካሜራ እንድንጠቀም ፈቃደኛ አልነበሩም፡፡ ይህ ለጥናቱ አስፈላጊ እንደሆነ ለማስረዳት ብንሞክርም በሀሳባቸው ስለፀኑ እኔና ረዳቴ በማስታወሻ እየያዝን መረጃ ሰብስበናል፡፡ ያልገባኝን እና ያመለጠኝን መልሼ እየጠየቅኳቸው ትህትና በተሞላበት መንገድ አስፈላጊውን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

ከባህታዊ ወልደ ማርያም ጋር ቆይታችንን እንደጨረስን ለወንዶች ክልክል ቢሆንም የመጣሁበትን አላማ በማሰብ እና እኔን ለመተባበር ሲባል ወደ ሴቶቹ በዓት እንድንገባ ተፈቀደልን፡፡ ከሴቶቹ መነኮሳት መሀል ከተመረጡልን መረጃ አቀባዮች ከእማሆይ ትርሲተ ማርያም እና ከእማሆይ እሴተ ጊዮርጊስ ጋር በመቅረጸ ድምጽ የታገዘ ቆይታ አድርገናል፡፡ ከትህትና በመነጨ አብዛኛዎቹን ጥያቄዎች ባህታዊ እንደነገሩህ ነው በማለት ለማለፍ ይሞክራሉ፡፡ ነገር ግን ከነበረን ረጅም ቆይታ እና ስለ ጥናቴ ባስረዳኋቸው መጠን የራሳቸውን መልስ እየሰጡኝ አስፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በገዳም የነበረንን የቀን ቆይታ አጠናቀን ወደማረፊያችን ተመለስን፡፡ የቀን ውሎዬን እና ያገኘኋቸውን መረጃዎች በመዝገብ ላይ አሰፈርኩ፡፡ አመሻሽ ላይ አባ ወልደ ሚካኤል ደውለው መረጃ አቀባዮቹን በማግስቱ ማግኘት እንደምችል ነገሩኝ፡፡

በቀን 07-07-07 ወደ ደብረ ምጥማቅ ቤተክርስቲያን አካባቢ በመሄድ በአካባቢው ተወልደው ረጅም ጊዜ ከኖሩት ከወ/ሮ እሸቴ መላከ እና ከወ/ሮ እቴነሽ ነገደ ወርቅ ጋር መኖሪያ ቤታቸው በመሄድ ቃለ መጠይቅ አድርገን መረጃ መሰብሰብ ችለናል፡፡

በቀን 08/07/07 አባ ወልደ ሚካኤል በቀጠሩኝ መሰረት ሄደን መጋቢ ስርዓት ደስታ ተክለ ወልድን አገኘናቸው፡፡ ከዛ በፊት ስለማያውቁን የቦታውን ታሪክና ምስጢር አሳልፈው ላለመስጠት መረጃ አልሰጥም አሉ፡፡ ነገር ግን እኔም ከመንበረ ፓትርያርክ እና ከሀገረ

ስብከቱ የተሰጠኝን ደብዳቤ አሳይቼ ስለጥናቴ አስረዳኋቸው፡፡ ረዳቴም የቤተ ክህነት እውቀት ስላለው እሳቸውን ሊያግባባ በሚችል መንገድ አስረድቷቸው ፈቃደኛ ሆኑልን፡፡ ከሳቸው ጋርም በመቅረጸ ድምጽ እና በቪዲዮ ካሜራ የታገዘ ቆይታ አድርገን በርካታ መረጃዎችን ማግኘት ችለናል፡፡

መረጃ ሰብስቤ ወዳረፍኩበት ቦታ በመሄድ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ወደ ወረቀት መገልበጥ ጀመርኩኝ፡፡ ከመስከ ሳልርቅ መረጃዎቼን ስገለብጥ ለሚፈጠሩብኝ ጥያቄዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እየተገናኘሁ፣ እየጠየኩ፣ የመረጃ ክፍተቶችን እየሞላሁ እስከ 11/07/07 ድረስ ቆየሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ከሰበሰብኳቸው ተረኮች በመነሳት ዳግም ምልከታ አደረኩኝ፡፡ በገዳሙ ውስጥ ፎቶ ማንሳት ክልክል በመሆኑ በምልከታ ጊዜ የሚያስፈልጉኝን ቦታዎች በምስል ለማስቀረት ተከለከልኩኝ፡፡ ሆኖም በጣም አስፈላጊ መሆኑን ሳስረዳ የሚመለከታቸው አካላት ተነጋግረው በስልክ እንደሚያሳውቁኝ ነገሩኝ፡፡ በዚህም መሰረት በቀን 12/07/07 እኔና ረዳቴ ወደ አዲስ አበባ ተመለስን፡፡ ከገዳም ከተመለስኩ በኋላ አንዱአለም አባተ(የአፀደ ልጅ) ወደ ጻድቃኔ ማርያም ገዳም በተደጋጋሚ እነደሚሄድና የረጅም ግዜ እውቂያ እንዳለው ከቅርብ ጓደኞቹ አረጋገጥኩ፡፡ ስለዚህም በገዳሙ ተረኮች ላይ ጥናት እያደረግኩኝ መሆኔን ነግሬው በቀን 12/08/07 በቃለ መጠይቅ መረጃ ልሰበስብ ችያለሁ፡፡

ከገዳሙ አባቶች በተሰጠኝ ቃል መሰረት በቀን 28/08/07 የተወሰኑ ቦታዎችን በምስል እንዳስቀር መፈቀዱን አባ ሰይፈ ሚካኤል ደወሉልኝ፡፡ በዚህም መሰረት በ29/08/07 ወደ ገዳሙ በመሄድ የተፈቀዱልኝን ቦታዎች ብቻ በምስል ለመያዝ ችያለሁ፡፡

በአጠቃላይ በመስክ ቆይታዬ አባ ሰይፈ ሚካኤል እና አባ ወልደ ሚካኤል መረጃ አቀባዮችን በማገናኘት፣ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች በመስጠት ቆይታዬ የተሳካ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተውልኛል፡፡ መረጃ አቀባዮቼም በሚመቸኝ ሰዓት ስቀጥራቸው በመተባበር እና መረጃ በመስጠት በአጭር ጊዜ አስፈላጊውን መረጃ እንደሰበስብ አስችለውኛል፡፡

## 1.8.2. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

በመስክ ጥናት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ እኔም በመስክ ወቅት የገጠመኝ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዳለ ሆኖ የአካዳሚውና የማኅበረሰቡ መራራቅ ዋነኛው ነው፡፡ በአካዳሚ ውስጥ “ተረክ” የሚለው ስያሜ “narrative” የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል በመተካት ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ አገልግሎት ላይ ውሏል(ዮናስ አድማሱ፣ 1992፣ 84)፡፡

ነገር ግን ይህ ቃል ጥናቴን በሰራሁበት ማኅበረሰብ ዘንድ አሁንም እንግዳ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ይህም በአካዳሚው እና ማኅበረሰቡ መካከል ያለውን ክፍተት የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ ለዚህ ክፍተት የአካዳሚው ድክመት? ወይስ የማኅበረሰቡ አዲስ ቃላትን ለመቀበል ዝግጁ አለመሆን? ሌሎች አጥኚዎች ቢመልሱት ጥሩ ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን የገጠመኝን በስያሜ ላይ የጋራ ግንዛቤ አለመኖር ለመፍታት የማኅበረሰቡን ዘይቤ በመከተል "ታሪክ" ወይም "ይትበሀል" የሚለውን ስያሜ በመጠቀም ተረኮችን መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

ሌላው የገጠመኝ ችግር አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ስለራሳቸው ለመናገር፣ በመቅረጸ ድምፅ እንድገለገል እንዲሁም ፎቶ ለመነሳት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች ከረዳቴ ጋር በመሆን በቃለ ምልልስ ጊዜ በወረቀት በመመዝገብ ችግሩን ማቃለል ተችሏል፡፡ ገዳም ውስጥ ፎቶ ማንሳት ክልክል መሆኑ ሌላው ችግር ነበር፡፡ ይህንን ለገዳሙ ኃላፊዎች በማስረዳት የሚያስፈልጉኝን ሁሉ ባይሆንም የተወሰኑ ምስሎችን ማስቀረት ችያለሁ፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1. ተረክ

የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴው የሚገጥሙትን ሁነቶች፣ በማኅበር ውስጥ የተከሰቱ ክስተቶች፣ ቢሆኑ ወይም ይሆናሉ ብሎ በምናቡ የሚያስባቸውን ክዋኔዎች እና ድርጊቶች በቋንቋ አማካኝነት አብሮት ለሚኖር ይነግራል፡፡ እነዚህ ግለሰባዊና ማኅበራዊ ገጠመኞች የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቀው ሲነገሩ ተረክ ይባላሉ፡፡ የተረክን ምንነት በማስመልከት የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡

ተረክ የሰው ልጅ የፅሁፍ ጥበብ ከመጀመሩ በፊት ጀምሮ የነበረ፣ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ስለዓለም አፈጣጠር፣ ስለነገሮች አመጣጥ፣ ስለእምነቱ፣ ስለባህሉ እና ስለማንነቱ ለመግለፅ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ተረክ ከሰው ልጅ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው፣ በማንኛውም ቡድን ወይም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኝ፣ ዘመንና ባህል የሚሻገር፣ በሁሉም የኪነጥበብ ቅርጾች የተለያዩ ጉዳዮችን ማስተላለፍ የሚችል፣ በቃል ወይም በፅሁፍ፣ በቅርጽ ወይም በስዕል፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ በዝርው ወይም በግጥም ቅርፅ ሊቀርብ የሚችል በርካታ የማኅበረሰቡን ሁነቶች የሚያሳይ መግባቢያ መንገድ ነው (Barthes, 1975: 237, Degh, 1972: 54) ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቴዎድሮስ የተረክን ምንነት እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> ተረክ ታሪኩን፣ ትረካውን፣ ታሪኩ የሚቀርብበትን ሁኔታና መንገድ ሁሉ ጠቅልሎ የሚይዝ ፅንሰ ሀሳብ ነው፡፡ በሰፊ አገባቡ ተረክ በቃል አልያም በጽሑፍ ሊቀርብ፣ በግጥም ወይም በዝርው ሊተረክ ይችላል፡፡ ከዚህም አልፎ ሊዘፈን፣ ሊተወን፣ ሊደነስ፣ ሊሳል፣ ሊቀረጽ፣ በተለያዩ መንገዶች ሊከወን የሚችልም ቅርጽ ነው (2001፣ 259-260)፡፡

ተረኮች በተለያየ ቅርጽ ይቀርባሉ ካልን የዚህ ጥናት ትኩረት ቃላዊ ዝርው ተረኮች (oral prose narratives) ናቸው፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረክ የስነቃል አንዱ ክፍል ሲሆን ግጥማዊ ባልሆነ መልክ በቃል የሚተረክ፣ ተለጣጣቂነት ያላቸው ድርጊቶችና ሁነቶች የሚፈፀሙበት፣ የድርጊቱ ተሳታፊ የሆኑ ገጸ ባሕርያት የሚገኙበት፣ እንዲሁም ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ቦታና ጊዜ የሚያመለክት ታሪክ ነው (Oring, 1986: 122)፡፡

ተረክ የግለሰብን ወይም የአንድን ማኅበረሰብ ልምድና ገጠመኝ በወጉ የተደራጁ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንድ የተከሰተ ሁነትን ማሳያ ወይም ማቅረቢያ መንገድ ነው (Oring, 1986፡ 121)፡፡ ተረክ ሁነቶች እና ድርጊቶችን ማሳያ ከሆነ አንድ ማኅበረሰብ

ወይም ግለሰብ ገጠመኙን፣ ባህሉን፣ ልማዱን፣ እምነቱን እና አስተሳሰቡን ያንፀባርቅበታል፡ ፡ ይህንንም በማስመልከት የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ያስረዳሉ፡፡

ተረክ ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶች፣ ሁነቶች እና ክስተቶች የሚፈጸሙበት፣ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታና ጊዜ የሚያሳይ፣ የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን ልማድ፣ ባህልና ዕምነት የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ፈጠራውና ተስተላልፎቱ ቃላዊ የሆነ፣ ከአንድ ትውልድ በላይ የሚዘልቅ፣ ከሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ እንደየዘመኑ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታ ራሱን በመቀያየር የሚኖርና የሚተረክ ነው (Degh, 1972: 54 ፤oring, 1986: 122)፡፡

ተረክ ማኅበረሰብ ወይም ግለሰብ ማንነቱን፣ ወግና ልማዱን፣ ባህሉን፣ ገጠመኙን እና እምነቱን የሚያንጸባርቅበት ከትውልድ ትውልድ ትውፊታዊ እሴቶችን ለማሸጋገር የሚገለገልበት መንገድ ነው፡፡ Harvilahti “Folklore and Oral Tradition” በሚለው ጽሁፋቸው “ተረክ በአብዛኛው ትውፊታዊ በሆነ ማኅበረሰብ ውስጥ ማኅበረሰቡ ባህሉን፣ ልማዱን እና የተለያዩ ገጠመኞችን ለትውልድ የሚያስተላልፍበት ቃላዊ ጥበብ ነው” በማለት የላይኛውን ሀሳብ ያጠናክራሉ (2003: 200)፡፡ ተረክ የሌለው ማኅበረሰብ ወይም ቡድን የለም፡፡ ሁሉም ማኅበረሰብ ተረኩን የሚያቀርብበት መንገድ ቢለያይ እንጂ ማንነቱን፣ ባህሉን እና ትውፊቱን የሚያዘልቅበት ተረክ አለው፡፡ ይህንንም ሀሳብ ፊቃደ ”ትረካ በማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ያለ በዕለታዊ ህይወት በተለያየ መልክ የሚከወን ጉዳይ ነው” (1991፣ 52፣) በማለት ገልጸዋል::

በአጠቃላይ ተረክ የማኅበረሰብ እና የግለሰብ መገለጫ ሲሆን ሰፊውን የሰውን ልጅ አስተሳሰብና ስሜት ያንፀባርቃል፡፡ ተረክ በግልም ሆነ በማኅበር የሚነገር የታሪክ ማሳያ ነው፡፡ በግል ይነገራል ሲባል ሰዎች ስለራሳቸው የሚተርኩት ታሪክ ነው፡፡ ተረክ ግለሰባዊ ተናጋሪነትን የሚፈጥር፤ ዕሴትን እና እምነትን የሚያሳይ፤ የሰውን የወደፊት ህይወት መስመር ማስያዝ የሚችል ነው፡፡ ተረክ የግለሰብን አስተሳሰብ እና ገጠመኝ ብቻ የሚያንፀባርቅ ሳይሆን በባህል ውስጥ የሚመላለስ፣ ስለአንድ ቡድን ከየት መጣነት፣ ገጠመኝ፣ ቃላዊና ቁሳዊ ጥበባት እና ስለማኅበረሰቡ አኗኗር ይተርካል፡፡

ተረኮች ለተለያዩ ኃይማኖቶች እምነትን ለማስረፅ፣ የኃይማኖቶቹን ሥርዓት ተጠብቆ እንዲቆይና ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ የተለያዩ ኃይማኖቶች (ለምሳሌ ክርስትና፣ እስልምና፣ ሂንዱ…ወዘተ) የኃይማኖቱን ማዕከላዊ ጉዳይ እምነት የሚያሰርጹት እና ኃይማኖታዊ እሴቶቻቸውን የሚያፀኑት በተረክ

ነው፡፡ ኃይማኖታዊ ተረኮች በኃይማኖት ቅዱሳን እና ነቢያት የሚባሉትን ሰዎች የህይወት ታሪክ እና ኃይማኖታዊ ተጋድሎ በውስጣቸው የሚይዙ ናቸው፡፡ ይሄንንም ለማረጋገጥ የክርስትና ኃይማኖት መሰረት የሆነውን የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን መጽሐፍት፣ እንዲሁም የእስልምና ኃይማኖት መሰረት የሆነውን ቁርዓን ማየት ይቻላል፡፡ይህንን በማስመልከት Dorson ካምቤልን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት የሰው ልጆች  የህይወት እና ሞታቸውን ጣጣ በተረክ አማካኝነት ይገልጻሉ፡፡ ተረኮች የሰውን ስነልቡና የሚያንጹ የኃይማኖትና የዕምነት ምንጭ ናቸው (1973: 108) ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ "የሰውን ልጅ የአስተሳሰብ ደረጃና እሴቶችን አካቶ የያዘው ስርዓት አምልኮ በሐተታ ተፈጥሮ እና በአፈ ታሪክ አማካኝነት ይገለፃል" (Messenger,1972: 220) በማለት ተረክ ለኃይማኖቶችና ለእምነት የጀርባ አጥንት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

ተረኮች የተራኪውን ማኅበረሰብ አመለካከት የያዙና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ተረኮች በማጤን የማኅበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና፣  ወዘተ. ማወቅ ይቻላል (Sims, 1963: 168)፡፡ በዘመናችን በተለያዩ ቤተ እምነቶች የተለያየ ይዘት ያላቸው ተረኮች ይተረካሉ፡፡ እነዚህ ተረኮች ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ምዕመኑን ለማስተማር እና የእምነቱን ስርዓት ጠብቆ እንዲጓዝ ለማድረግ የሚፈጠሩ እና የሚከወኑ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ተረክ ማለት የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን እና ግለሰብ አመለካከት፣ ባህል፣ እምነት እና ማኅበራዊና ስነልቡናዊ ማንነት ለማወቅ የሚያስችል፤ ሁነቶችንና ድርጊቶችን የሚያሳይ፤ ዓረፍተ ነገሮች በአግባቡ ተዋቅረው የሚያደረጁት፣ ታሪክ ያለው፣ ታሪኩን የሚያስኬዱ ገጸ ባሕርያት ያሉት የሀሳብ ማስተላለፊያ መንገድ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 2.1.2. የተረክ ዓይነቶች

አቀራረባቸው የተለያየ ቢሆንም (በቃል፣ በፅሁፍ፣ በግጥም፣ በዝርው፣ ወይም በስዕል) የተረክ ዓይነት ተብለው የሚገለፁት ሚት፣ አፈታሪክ፣ ተረት፣ አጭር ልብ ወለድ፣ ውዳሴ ግጥም፣ ቀልድ፣ እንቆቅልሽ፣ የሰው ልጅ ገጠመኝ፣ ታሪክና የህይወት ታሪክ የመሳሰሉት ናቸው (Finnegan, 1992: 36፤ Degh, 1972: 58)፡፡ በሌላ በኩል የተረክ ዓይነቶችን በተመለከተ አለም አቀፋዊ የሆነ ክፍፍል ባይኖርም ሚት፣ አፈታሪክ እና ተረት ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ ባስኮም ያስረዳሉ(1965: 5)፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ በተጨማሪ ከአካባቢ

አካባቢ የተለያዩ ክፍፍሎች እንደሚኖሩና ቀልዶች እና ትዝታዎች(የግል ትውስታዎች) በተረክ ውስጥ እንደሚካተቱ መታወቅ አለበት (Bascom, 1965: 5)፡፡

ሚት ማለት የሰው ልጅ አካባቢውን እና ተፈጥሮውን ለመረዳት፣ በአዕምሮው የሚመላለሱ የማንነት እና የምንነት ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚረዳ መንገድ ነው፡፡ ይህንን በማስመልከት ቴዎድሮስ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> ሚት የሰው ልጅ የስሜት ህዋሱን ከሚያግደው አድማስ አምልጦ በመውጣት በሜታፊዚክሳዊ ኃይል ዓይን ዓለመ ዓለማቱን ለማየት፣ ለማወቅ፣ ያወቀውን ለመበየንና ለመቆጣጠር የሞከረበት ፍልስፍናው ነው፡፡… ሚት በምርምር የማይደረስበትን፣ በተግባር ሙከራ የማይረጋገጥን ልዕለ አካላዊ ጉዳይ በመንፈስ፣ በምናብ ኃይል የምናቀርብበት ስርዓት ነው (2001፣ 67-68)፡፡

ሚት ስለፍጥረት እና ስለተፈጥሮ፣ ስለተፈጥሮና ስለፈጣሪ የሚተርክ፣ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ያላቸው መናፍስት በገጸ ባህርያትነት የሚንቀሳቀሱበት በተራኪው ማህበረሰብ እውነት ተደርጎ የሚቆጠር ተረክ ነው (Bascom, 1965: 5)፡፡

ሌላው የተረክ አይነት አፈ ታሪክ ደግሞ በውል የሚታወቅ ሁነትን ወይም ድርጊያን ተመስርቶ የሚተረክ፣ የሰው ልጆች ገጸ ባህሪ ሆነው የሚቀረፁበት፣ የጦር ጀግኖች ወይም ቅዱሳን ከሰው አቅም በላይ የሆነ ተጋድሎ ሲፈፅሙ የሚያሳይ፣ በሚተረክበት ማኅበረሰብ እውነት ተደረጎ የሚወሰድ  ተረክ ነው፡፡ የአፈ ታሪክን ምንነት በማስመልከት ቴዎድሮስ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> ባለቤቱ በሆነው ማኅበር ዘንድ ከእውነት ተቆጥሮ የሚነገር ቃላዊ ተረክ ነው፡፡ በአፈ ታሪክ ውስጥ ከሚሳሉ ገጸ ባሕርያት መሃል ዋና ዋናዎቹ ባብዛኛው ታሪክ (history) የሚያውቃቸው፣ ተረኩ መቼት ባደረገው ዘመንና ሥፍራ በእውን የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ሰዎቹ በታሪክ የተሳተፉባቸው ታላላቅ ሁነቶችና በሁነቶቹ ውስጥ የፈፀሟቸው ተጋድሎዎች (እንደ ተረኩ ዓይነት መንፈሳዊ እና ዓለማዊ ተጋድሎዎች) በአብዛኛው በተረኩ ውስጥ ሥፍራ ያገኛሉ፡፡ አፈ ታሪክ በከፊል ታሪካዊ በከፊል ደግሞ ፈጠራዊ (ምናባዊ) በመሆኑ ቃል ከዋኙ በታሪኩና በፈጠራው መካከል ሚዛን፣ ምጣኔና ህብር ይኖር ዘንድ በእጅጉ ይደክማል (2001፣ 262-263)፡፡

ተረት ደግሞ የሰው ልጆች፣ እንስሳት፣ መናፍስትና ሌሎች ፍጡራን ገጸ ባህሪ ሆነው የሚቀረፁበት፣ ሙሉ በሙሉ ፈጠራ የሆነ፣ መቼት የሚያደርገው ጊዜና ቦታ በውል የማይታወቅ፣ የራሱ የአጀማመር እና አጨራረስ ስርዓት ያለው ተረክ ነው (ቴዎድሮስ፣ 2001፣ 259 ፤ Bascom, 1965: 4)፡፡

እነዚህ የተረክ አይነቶች በተራኪው ማኅበረሰብ ዘንድ ባላቸው እውነትነት፣ በሚቀርጿቸው ገጸ ባሕርያት፣ ገጸ ባሕርያቱ በሚንቀሳቀሱበት መቼት እና በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ የተለያዩ ናቸው፡፡

ከእነዚህ ከሶስቱ አከፋፈሎች በተጨማሪ የአንድን ግለሰብ ገጠመኝ መሰረት ተደርገው የሚተረኩ ተረኮች አሉ(Bascom, 1965: 4)፡፡ እነዚህ ግለሰባዊ ገጠመኞች ላይ ተመስርተው የሚተረኩ ተረኮች በተራኪው ዘንድ እውነተኛ ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ የተለያዩ ምሁራን እነዚህን ግለሰባዊ ተረኮች "True experience stories" (Degh, 1972: 77)፣ "Personal experience stories" ወይም "Memorate" (Stahl, 1972: 269) በማለት በተለያየ ስያሜ ይጠሯቸዋል፡፡ ግለሰባዊ ተረኮች የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት ህይወቱ የሚገጥሙትን ገጠመኞች መሰረት አድርገው የሚተረኩ ናቸው፡፡ እነዚህም ገጠመኞች የስራ እና የጉዞ ማስታወሻዎች እንዲሁም የህይወት ታሪኮች ሊሆኑ ይችላሉ(Degh, 1972: 78)፡፡ እነዚህ ግላዊ ተረኮች በአተራረክ ስልታቸውና በሚያነሱት ሀሳብ ግለሰቡ የበቀለበትን ማኅበረሰብ እምነት እና ማንነት ያንጸባርቃሉ፡፡

## 2.1.3. ተረክን የማጥናት አስፈላጊነት እና የአጠናን ስልት

ከላይ እንደተመለከተው ተረክ ማለት የአንድን ማኅበረሰብ ወይም ቡድን እና ግለሰብ አመለካከት፣ ባህል፣ እምነት እና ማኅበራዊና ስነ-ልቡናዊ ማንነት ለማወቅ የሚያስችል፣ ሁነቶችንና ድርጊቶችን የሚያሳይ፣ ዓረፍተ ነገሮች በአግባቡ ተዋቅረው የሚያደረጁት፣ ታሪክ ያለው፣ ታሪኩን የሚያስኬዱ ገጸ ባህርያት ያሉት የሀሳብ ማስተላለፊያ መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም ተረክን ማጥናት ደግሞ የተራኪውን ማኅበረሰብ ማንነት፣ እምነት፣ አስተሳሰብ፣ ወዘተ. ለመረዳት ያስችላል፡፡ ይህንንም በማስመልከት ሲምስ "ተረኮች የተራኪውን ማኅበረሰብ አመለካከት የያዙና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህን ተረኮች በማጤን የማኅበረሰቡን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል፣ ርዕዮተ አለማዊ ፍልስፍና፣ ወዘተ. ማወቅ ይቻላል" (2005: 168) ይላሉ፡፡

ተረክ ሲጠና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ የተለያዩ ነጥቦች እንዳሉ ተመራማሪዎች ሀሳቦችን ሰንዝረዋል፡፡

> "በተረኮች ላይ ትንታኔ ለመስጠት ስንነሳ ከግንዛቤ ማስገባት ያለብን የተረኩን ሚና ማወቅ፣ ትልሙን መለየት፣ የተረኩን የአደረጃጀት ቅደም ተከተል መለየትና ድምጸቱን መገንዘብ፣ የትረካውን የትኩረት አቅጣጫ መለየት እና የተረኩን፣ የተራኪውን እና የአድማጩን ተዛምዶ መለየት ናቸው" በማለት ይገልፃሉ (Finnegan, 1992: 37-38)፡፡

እንደ Degh ገለፃ ደግሞ ተረክን ለማጥናት የሚነሳ ሰው ትኩረት ሰጥቶ ሊመልሳቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጥያቄዎች አሉ፡፡ እነሱም የተረኩ መልዕክት ምንድነው? ለተረኩ መፈጠር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምንድነው? እና ተረኮቹን ተራኪዎቻቸው እና አድማጮቻቸው እንዴት ይመለከቷቸዋል? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው (1972 : 54)::

ከእነዚህ በተጨማሪ Oring ተረክን ለማጥናትና ለመፈከር የሚነሳ ሰው አራት አውዶችን መረዳት እንዳለበት ይጠቁማሉ፡፡ እነሱም ባህላዊ አውድ፣ ማኅበራዊ አውድ፣ ግላዊ አውድ እና ንፅፅራዊ አውድ ናቸው፡፡ እነዚህን አውዶች መረዳት እና ከግንዛቤ ማስገባት ተረኮቹ ለማኅበረሰቡ ምን እንደሆኑ እና ሚናቸውን ለማወቅ ያስችላል (1986: 135-142)፡፡

ስለዚህ ተረክ ሲጠና ተረኩን ብቻ ወስዶ ትንታኔ ከመስጠት ይልቅ የተረኩ ባለቤት የሆነው ማኅበረሰብ ለተረኩ ያለውን አመለካከት፣ ባህል፣ የመከወኛ ቦታና የመከወኛ ጊዜ ማወቅ በተረኩ ውስጥ ያሉትን ትዕምርቶችና ሀሳቦች ለመረዳት ያስችላል፡፡ በዚህ ጥናትም በአጠቃላይ ከላይ የተገለፁት ነጥቦች ለጥናቱ የሚጠቅሙትን ያህል ማሄጃ ሆነዋል፡፡

## 2.1.4. ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ

የአንድ ማኅበረሰብ ቃላዊም ሆነ ቁሳዊ ባህል መጠናትና መመርመር ያለበት ለማኅበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ መሰረት በማድረግ ነው (sims, 2005:174)፡፡ በመሆኑም በዋናነት ገዳማውያኑ ተረኮቹን ለምን አገልግሎት ያውሏቸዋል? በገዳማውያኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ እና ለገዳሙ ስርዓት ተረኮቹ ምን አገልግሎት አላቸው? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ተመራጭ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ኃይማኖታዊ ፎክሎሮችን ለማጥናት ከሚያገለግሉት መስኮች አንዱ መሆኑን Dorson ያስረዳሉ (1972: 25)፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ ፎክሎሮችን ለማኅበሩ ምን እና እንዴት ይጠቅማሉ የሚለውን ማጥናት ያስችላል፡፡ ይህንንም በማስመልከት እነSims ሲገልፁ፡-

> ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ የአንድን ማኅበረሰብ ቃላዊ፣ ልማዳዊ እና ጽሁፋዊ ጉዳዮች በመመርመር ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ለመጋራት ካላቸው ጥቅም አኳያ ለምን እና እንዴት በሚሉ ጥያቄዎች አማካኝነት ፈትሾ ተግባራቸውን የሚያሳይ ንድፈ ሀሳብ ነው (Sims, 2005:175) ይላሉ፡፡

ተግባር ስንል በአንድ ሥርዓት ውስጥ የታቀፈ አንድ ሁነት ለአጠቃላዩ ሁነት የሚያበረክተው ድርሻ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አንድ ማኅበረሰብ በቋንቋው ወይም በባህሉ አማካኝነት የሚገልጸው ጉዳይ ተግባር የሚባለው የማኅበረሰቡ ማኅበራዊ መዋቅር ባለበት

ሁኔታ ተጠብቆ እንዲዘልቅ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ነው፡፡ ተረኮች በሚተረኩባቸው ማኅበረሰብ ዘንድ የሚያበረክረቱት ፋይዳ አላቸው፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን በማቀንቀን የሚጠቀሱት Bascom ፎክሎር አራት ተግባራት እንዳሉት ይገልፃሉ፡፡ የመጀመሪው የማስተማር ተግባር ነው (Sims, 2005: 175፤ ፈቃደ፣ 1991፣ 20)፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ ፎክሎሮች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ስርዓቶች፣ ህይወት የሚመራበትን መንገድ፣ መልካም ምግባራትን ያስተምራሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈቃደ "ስነቃሎች የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሄድ ሥርዓትን ያሳውቃሉ፡፡ በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የህብረትን ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ" (1991፣ 20) በማለት አስፍረዋል፡፡

ሁለተኛው የፎክሎር ተግባር የማምለጭ ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር ከተወሰኑብን እና በባህል ስም ከተጫኑብን ሥርዓቶች ማምለጫ ነው፡፡ ፎክሎር ከአሰልቺና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች እንድናመልጥ ያደርገናል (Sims, 2005: 176፤ፈቃደ፣ 1991፣ 20)፡፡በመሆኑም የሰው ልጅ በፎክሎር በዙሪያው ከሚገኙ የማያስደስቱ እና ነፃነት ከሚነፍጉ ጉዳዮች በማምለጥ በውስጡ የራሱን የደስታና የነፃነት ዓለም ይመሰርታል፡፡

ሶስተኛው የፎክሎር ተግባር የመትከል ወይም የመቆጣጠር ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ቅቡል የሆኑ ባህሪያትን የመትከል ወይም የመቆጣጠር ተግባር አለው፡፡ "ባህል በተፈለገ ጊዜ አንድን ሰው ወደ ተረጋገጠ የባህርይ መስመር ይወስዳል" (Sims, 2005: 176)፡፡ ይህም ማለት "በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ መልካም ከሚባሉ መርሆች የሚያፈነግጥን ግለሰብ በአርፈህ ተቀመጥ ግሳፄ መመለስ ነው" (ፈቃደ፣ 1991፡ 20)፡፡ ስለዚህም ማኅበረሰቡ ስህተት ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን መርሆች ለማጥፋትና መልካም ናቸው ብሎ ወደሚያምንባቸው መስመሮች ለመመለስ፣ እንዲሁም ሰናዮቹን ለማፅናት በፎክሎር ይገለገላል፡፡

የመጨረሻው የፎክሎር ተግባር የማረጋገጥ ወይም የማፅደቅ ተግባር ነው፡፡ ፎክሎር ስርዓትን በማክበር፣ እነዚህ ድርጊቶች በማኅበረሰቡ ህይወት ውስጥ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው በማድረግ ባህልን የማረጋገጥ ተግባር ይፈፅማል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ፈቃደ "የቡድኑ አባላት በስነቃል አማካኝነት ከልደት እስከሞት የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ክንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ" (1991፣18) በማለት ይገልፃሉ፡፡ ፎክሎር በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወኑ ክዋኔዎችና ተቀባይነት ያላቸው መርሆች ትክክለኛ እና መቀጠል

ያለባቸው እንደሆኑ ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ በማቅረብ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማድረግ አቅም አለው፡፡

ነገር ግን የባስኮም ሃሳብ በቀደምት የተግባራዊ ንድፈ ሃሳብ አራማጆች ተቀባይነት የነበረው ቢሆንም ትችት እና ተቃውሞ ገጥሞታል (Sims, 2005: 176):: Bascom የፎክሎር ተግባራትን በአራት መድበው ማስቀመጣቸው ተመራማሪዎች የሚያጠኑት የፎክሎር ዘርፍ በተጠኚው ማኅበረሰብ ዘንድ ያለውን ተግባር ከመመርመር ይልቅ እርሳቸው ያስቀመጧቸው ተግባራት ላይ መመደብ እንዲተገብሩ ሆነዋል፡፡ ይሄ ደግሞ ፎክሎር ቢጠናም ባይጠናም ተግባራቱን ባህልን ማፅናት ላይ የተወሰነ ያስመስለዋል፡፡ ፎክሎር ዘርፈ ብዙ እንደመሆኑ በርካታ ተግባራት አሉት፡፡ ቀደምት ተግባራውያን ሀገር በቀል እምነቶች ሁልጊዜ የሚያመለክቱት የማኅበረሰቡን እምነት ነው፡ ተረቶች ደግሞ በአድማጭና በነጋሪው ምክንያት ማምለጭን ያመለክቱናል በማለት ጠቅላይ ድምዳሜ ያስቀምጡ ነበር፡፡ ሀገር በቀል እምነቶች ሁልጊዜ የሚያመለክቱት እምነትን ብቻ ሳይሆን የማኅበረሰቡን የወደፊት ህይወት ለመተንበይ እና የሚመጣውን በማሰብ ጥንቃቄ ለማድረግም ጭምር እንደሆነ እነ Sims ያስረዳሉ (2005: 177)::

ከዚህም በተጨማሪ ፎክሎር ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው አዳዲስ የሚፈጠሩትንም ያጠቃልላል፡፡ የBascom አከፋፈል ግን አዳዲስ ለሚፈጠሩት ፎክሎራዊ ጉዳዮች ቦታ የሌለውና ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑን እነ Sims Mullenን በመጥቀስ አስረድተዋል(2005: 176):: የቀደምት የፎክሎር ተመራማሪዎች ድክመት ተብለው የሚጠቀሱት ፎክሎራዊው ጉዳይ የሚከወንበት ጉዳይ ላይ ተመስርተው ትንታኔ አለመስጠታቸው እና የፎክሎርን ባህሪ ተለዋዋጭነት መዘንጋታቸው ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በአንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲታይ ያደርጋል(Oring, 1986: 74 ፤ Sims, 2005: 177)፡፡

በአጠቃላይ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ቃላዊ፣ ልማዳዊና ቁሳዊ ባህሎችን የያዙ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ለተተኳሪው ማኅበረሰብ ምን እንደሚጠቅሙ እና ጠቀሜታው እንዴት እንደሚከናወን ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ግላዊ አውዱን መሰረት በማድረግ የሚያጠና ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ ጥናትም የተጠኚውን ማኅበረሰብ እምነት እና ወቅታዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ተረኮቹ ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ከእኔ ጥናት ጋር ቀጥተኛም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ የጥናቶቹ አጠቃላይ ገፅታ፣ ከእኔ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና፣ ያለባቸው ክፍተት እና የእኔ ጥናት ከጥናቶቹ በምን እንደሚለይ በዝርዝር ቀርቧል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ባደረግኩት ዳሰሳ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥናታዊ ጽሁፎች ማግኘት ችያለሁ፡፡ እነዚህን ጥናቶች መምረጥ የቻልኩት ገዳም ላይ በመመስረት ተረክን ስላጠኑ ነው፡፡

የመጀመሪያው ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በፍፁም ኩራባቸው (2006 ዓ.ም) "የዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዓላማ በዝዋይ ደሴያት አድባራት መመስረት የተገኙ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎችን ምሳሌ፣ ዘይቤና ትዕምርት አንድምታ መርምሮ ማብራራት እንዲሁም ተምሳሌታዊ ፍቺያቸውን በመፈከር የተረኮቹንና ቁሳዊ ባህሎቹን ፋይዳ ማብራራት የሚል ነው፡፡ ፍፁም ዓላማውን ከዳር ለማድረስ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ በተደጋጋሚ መስክ በወጣበት ጊዜ በምልከታ በርካታ ጉዳዮችን ከነአውዳቸው ተገንዝቧል፡፡ በምልከታ ያላገኛቸውን ደግሞ በቃለ መጠይቅ አዳብሯል፡፡ በመጨረሻም ግልፅ ያልሆኑና ያልተረዳቸውን ጉዳዮች በቡድን ውይይት ለማግኘት ችሏል፡፡ በተጠቀማቸው ዘዴዎች የለቀማቸውን መረጃዎች በገላጭ የምርምር ስልት ተንትኗል፡፡

በተዛማጅ ጽሑፍም ፍፁም ሰባት ጥናቶችን ቃኝቷል፡፡ ሦስቱ በትምህርት ክፍሉ የተሰሩ ሲሆኑ አራቱ ደግሞ ከትምህርት ክፍሉ ውጪ የተሰሩትን ጥናቶች በጥልቀት ፈትሿል፡፡ ከአላማቸው አንስቶ እስከ መጨረሻዋ ግባቸው ድረስ መርምሯል፡፡ የጥናቶቹን ጠንካራ ጎን በሚገባ አብራርቶ አቅርቧል፡፡ ድክመታቸውንም እንዲሁ፡፡ ፍፁም የቃኛቸውን ጥናቶች ደካማ ጎን ሲፈትሽ በጥናቶቹ የተነሱ የተፋለሱ ሀሳቦችን እንዲሁም ከጥናቱ አላማ ጋር የማይዛነቁ መሆናቸውንም ጭምር ነው፡፡ የእርሱም ጥናት ከቃኛቸው ጥናቶች ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት አስረድቷል፡፡ የእርሱ የተሻለ የሆነበትንም መንገድ ጠቁሟል፡፡

ፍፁም በጥናቱ መታገኒያ ያደረገው ንድፈ ሃሳብ ተግባራዊ እና ተረክ ንድፈሃሳቦችን ነው፡፡ በተጨማሪም የቁሳዊ ባህልን ጽንሰ ሃሳብ አካቷል፡፡ የተመሰረተባቸው ንድፈ ሃሳቦችና ጽንሰ ሃሳብ ጥናቱን በጥልቀት መርምሮ በስፋትና በምላት እንዲተነትን አስችለውታል፡፡

ፍፁም በጥናቱ ተረኮቹ ገዳምና አድባራቱን የመዘከር፣ ታሪካዊነትን የመናገር፣ ቅድስናን የመስበክ፣ የስፍራውን ክብር ከፍ የማድረግ፣ ሉአላዊነትን የማስከበር ተግባር እንዳላቸው በስፋት አብራርቷል፡፡ ቁሳዊ ባህሎቹ በአገልግሎታቸው ለሥርዓተ አምልኮ መፈፀሚያ፣ ኃይማኖታዊ አስተምህሮን ለማጽኛ የሚያገለግሉና ከኦሪት አምልኮ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ የተረኮቹን እውነትነት ለማረጋገጥ በማስረጃነት የቆሙ እንደሆኑም ገልጿል፡፡ የቃላዊ ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ መረጃዎች ጥቅል አንድምታ የዝዋይ ደሴያት ገዳምና አድባራትን የጥበባዊ እሴት መገለጫ፣ የመንፈሳዊ እሴት ነጸብራቅ፣ የታሪካዊ ድርጊት ዘጋቢ፣ ባህላዊ ገፅታን ማሳያና የዘመንን መንፈስ መፈተሻ መሆናቸውን በጥናቱ በስፋት ተመልክቷል፡፡ በመጨረሻም ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ የኃይማኖት ማጽኛና የማንነት መገንቢያ መሳሪያዎች መሆናቸውንም አረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ፍፁም አላማው ሰምሯል፡፡ቃላዊ ተረኮቹን ተንትኗል፡፡ቁሳዊ ባህሎቹን መርምሯል፡፡ ያላቸውንም ተምሳሌት ማሳየት ችሏል፡፡ በሌላ በኩል ከስፍራው (ጥናቱ ከተካሔደበት አካባቢ) የተሰበሰቡ ተረኮች፣ ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች፣ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር መግለጫ፣ ከስፍራው የተወሰዱ ፎቶግራፎች፣ ካርታዎች እና የተለያዩ ደብዳቤዎች በአባሪነት መሰነዳቸው የአጥኚውን ብስለትና ጥንካሬ አመላካች ናቸው፡፡

የፍፁም ጥናት በገዳም ላይ መመስረቱ፣ ተረኮችን ማጥናቱም ሆነ የመተንተኛ ስልቱ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን የእኔ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለየ መሆኑ እና ተረክ ላይ ብቻ በማተኮር በመሰራቱ ከእርሱ ጥናት ይለያል፡፡

ሌላው በቴዎድሮስ ይበልጣል (2005 ዓ.ም) "የደብረወርቅ ማርያም ገዳም አመሰራረትና በገዳሟ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ የቀረበው ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ይዛመዳል፡፡ ጥናቱ ዋና አላማው ያደረገው ከደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች በገዳማውያኑና በዕምነቱ ተከታዮች ዘንድ የሚኖራቸውን ፋይዳ መመርመር ነው፡፡ ቴዎድሮስ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃውን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ዘዴ ሰብስቦ በገላጭ የምርምር ዘዴ ተንትኗቸዋል፡ ፡ በንድፈ ሃሳባዊ ዳራ አጥኚው ስለተረክ ምንነት፣ ዓይነቶችና ስለተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ለጥናቱ በቂ በሚባል ሁኔታ አብራርቶ ማቅረቡ የሚደገፍ ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴ ላይ ስለ ገላጭ ዘዴ ምንነት እና ለምን ሊመርጠው እንደቻለ የተወሰነ ማብራራት ነበረበት፡፡

አጥኚው የገዳሟን አመሰራረት ስያሜ፣ ጥንታዊነት፣ ቅዱስነት፣ ተዓምር ሰሪነትና የቅዱሳን መፍለቂያ መሆኗን የሚያሳዩ ተረኮችን ሰብስቧል፡፡ በዚህም ተረኮቹ ከላይ የተጠቀሱት

ተግባራት እንዳሏቸው ለማሳየት ሞክሯል፡፡ የሰበሰባቸውን ተረኮችም እንደሚያነሱት ጉዳይ በይዘት ለመመደብ እና ለመተንተን ችሏል፡፡

ቴዎድሮስ በዚህ ጥናቱ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበረሰቡ ወይም የእምነቱ ተከታይ እምነቱን ፀንቶ እንዲቆይ የማስተማር፣ የመግታትና የመቆጣጠር ተግባር እንዲሁም ለገዳሟ ክብር ይሰጥ ዘንድ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳላቸው አሳይቷል፡፡

የቴዎድሮስ ጥናት ገዳም ላይ መመስረቱ፣ ተረክን ማንሳቱ፣ እና ተግባራዊ ንድፈ ሃሳብን በመተንተኛ ስልትነት መጠቀሙ ከእኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ነገር ግን የእኔ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም እና የእርሱ ጥናት የተመሰረተበት ገዳም የተለያየ ነው፡፡

ሌላው ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ሞገስ ጀንበር (2003 ዓ.ም) "ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና አምልኳዊ ሥርዓቶች" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ዓላማም ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያይዘው በሚነገሩ ተረኮችና በገዳሙ ውስጥ በሚፈፀሙ አምልኳዊ ስርዓቶች የገዳማውያኑ እምነት ምን እንደሚመስል መመርመርና ይህም እምነት ለገዳማውያኑ ያለውን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ በዚህም የደሴቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የኖህ መርከብ፣ የመስቀልና የመሶበ ወርቅ ቅርጽ ያለው መሆኑ፣ የተሰወረ የመድኃኔዓለም ኃይል አለበት መባሉን፣ በገዳሙ ጠላቶች ላይ ጥቃት የሚያደርስ ለቅዱሳኑ እርዳታ የሚሰጥ ኃይል አለ የሚል እምነት ያለ መሆኑን የሚያሳዩ ተረኮች እንዳሉና እነዚህ ተረኮች ገዳማዊ ህይወትን የመከተልና የማጠናከር ተግባር እንዳላቸውም ገልጿል፡፡ የአምልኳዊ ስርዓቶችም ለገዳማውያኑ መንፈሳዊ ድባብን ከማስረጽ በተጨማሪ ገዳማዊ ህይወትን የማጽናት ተግባር እንዳላቸውም አሳይቷል፡፡

ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተገለገለባቸው ዘዴዎች ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ ስለ ዘዴዎቹ ምንነት፣ ለጥናቱ ተገቢ ስለመሆናቸው፣ እንዴት እንደሚጠቀማቸው የሚያሳዩ መረጃዎችን አላሰፈረም፡፡ በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝቱም የቃኛቸውን ጥናቶች ከዓላማቸው ጀምሮ ይዘታቸውን በአጭሩ ያስቀምጣል እንጂ ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን፣ የየጥናቶቹ ግብ ምን ይመስላል፣ የየውጤታቸው አንድምታ ምን ይመስላል የሚሉ ጉዳዮች አልታዩበትም፡፡

የገዳማዊ ህይወት አጀማመርን ከጣና ሐይቅ ደስያት ገዳማት ጋር በተያያዘ ያቀረበው መረጃ ጠንካራ ጎኑ ነው፡፡ በጥናቱ መጨረሻ ክፍል የቀረቡት የአባሪ ፎቶዎችና ለቃለ መጠይቁ ጥያቄዎች ሳይቀሩ በሥርዓቱ ዋቢ መደረጋቸው የጥናቱን ጥንካሬ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ግን በጥናቱ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶች አሉ፡፡ የጥናቱ ዳራ

ስለ ቃላዊ ተረኩና ቁሳዊ ባህሉ መንደርደሪያ የሚሆኑ ጉዳዮችን በማንሳት፣ በመስኩ ያለውን ክፍተት በማሳየት፣ የሱን ጥናት አስፈላጊነት ማመልከት ሲኖርበት ሰፊውን ገለፃ ያደረገው ስለ ኢትዮጵያ ስነ ቃል ስብሰባና ጥናት ነው፡፡

በአጠቃላይ የእኔ ጥናት ከሞገስ ጀንበር ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ሁለታችንም በገዳማት ተረኮች ላይ መመስረታችን እና የመተንተኛ ስልታችን መመሳሰሉ ነው፡፡ ነገር ግን የእኔ ጥናት ተረክ ላይ ብቻ መከናወኑ እና ጥናቶቻችን በተመሰረቱበት ገዳም ልዩነት አለ፡፡

ሌላው ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በምህረት ተስፋዬ (2003 ዓ.ም) "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች በገዳማውያኑ ዘንድ እምነትን በመትከልና በማጠናከር ረገድ ያላቸውን ሚና የማሳየትን ዓላማ ያነገበ ነው፡፡ የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃውን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ዘዴ ሰብስቦ በገላጭ የምርምር ዘዴ ተንትኗቸዋል፡፡

ጥናቱ  የገዳማዊው ህይወትን አጀማመር በማስቃኘት በቂ መረጃ ማቅረብ በመጀመሪያ የሚነሳለት ጠንካራ ጎን ነው፡፡ ለተረኮቹ ያቀረበው ነገር ባይኖርም ቁሳዊ ባህልን ለመተንተን የተጓዘበት መንገድ፣ እያንዳንዱን ቁስ በፎቶ አስደግፎ ማቅረቡ፣ ዓላማው ግብ እንዲመታ የሚያቀርባቸው ሌሎች መረጃዎች በጣም ጥሩ በመሆናቸው እንደ ጠንካራ ጎን የሚነገርለት ነው፡፡ በአንፃሩ ጥናቱ የተወሰኑ ክፍተቶችም አሉበት፡፡  ስነ ዘዴውን ብናይ የቃለ መጠይቁና ምልከታ ዘዴን እንደሚጠቀም እንጂ ለምን እንደተመረጡ፣ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ ማስረጃ አያቀርብም፡፡

በተዛማጅ ጽሑፍ ረገድ ዳሰሳ ያደረገባቸው ጥናቶች ያላቸው ጠንካራና ደካማ ጎን፣ አንድ የሚያደርጋቸው እና የሚለያቸውን ነጥብም አልተጠቀሰም፡፡ አገልግሎት ላይ የዋለው ንድፈ ሀሳብ የተምሳሌታዊ መስተጋብራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Symbolic internationalism theory) ነው፡፡ ሆኖም ስለ ንድፈ ሀሳቡ ምንነት፣ አስፈላጊነትና እንዴት እንደሚጠቀምበት አያሳይም፡፡

ምህረት ተረኮቹና ቁሳዊ ባህሎቹ ገዳማውያኑን በበዓታቸው ፀንተው እንዲኖሩ የማድረግና የስፍራውን ህልውና የማስጠበቅ ሚና እንዳላቸው በጥናቱ ግኝት ውስጥ አሳይቷል፡፡

ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በገዳም ላይ መመስረቱ እና ተረክን ማጥናቱ ነው፡፡ ነገር ግን የኔ ጥናት የሚመሰረትበት ገዳም እና የመተንተኛ ስልት ከእርሱ ጥናት ይለያል፡፡

ተስፋዬ ተገኝ (2003 ዓ.ም) "በደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረትና ቱሳዊ ባህል ጥናት" በሚል ርዕስ የቀረበ ጥናት በጥቂቱም ቢሆን ከእኔ ጥናት ጋር የሚቀራረብ ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ አብይ ትኩረትም የገዳም አመሰራረት፣ የገዳማውያን የዕለት ተዕለት ህይወት፣ አለባበስና በሰውነት ላይ በሚደረጉ ቁሶች ላይ ነው፡፡

በስነ ዘዴ ክፍሉ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ምልከታና ቃለ መጠይቅን እንደተጠቀመና መረጃዎቹን በገላጭ የምርምር ዘዴ እንደተነተነ ጠቅሷል፡፡ ሆኖም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችና የትንተና ስልቶቹ በስርዓት ያልቀረቡበት ጥናት መሆኑን ለማስተዋል ተችሏል፡፡

በተዛማጅ ጽሑፍም ጥናቶችን ሲቃኝ ዓላማቸውን ጠቅሶ በጥናቱ የተነሳውን ዝርዝር ሀሳብ ጨምቆ ለማቅረብ አልሞከረም፡፡ ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን፣ ዘዴያቸውን፣ ዓላማቸው ግብ መምታት አለመምታቱን አይገልጽም፡፡

በክለሳ ድርሳኑም ሰፊውን ክፍል የያዘው የገዳማዊ ህይወት ገለፃ ነው፡፡ የቁሳዊ ባህልን ሀሳብም አንድ ላይ ከገዳሙ ጋር አንስቷል፡፡ ለምን ምክንያት አንድ ላይ እንዳመጣቸው አይታወቅም፡፡ መረጃውም በጣም የላላ ነው፡፡ ተረኮቹን ያየበት ንድፈ ሃሳባዊ ዕይታ የለም፡፡ በምዕራፍ ሦስት የቀረበው መረጃም ግልጽነት ይጎድለዋል፡፡ ለአንባቢው ዳራ ለመስጠት ይቅረብ ለትንተና አይታወቅም፡፡ የገዳሙን የስራ ክፍፍልና አይነትን በስፋት ያነሳል፡፡ ስለ ስራና ስንፍና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያም ይሰጣል፡፡ ከጥናቱ ጋር የሚገናኝበት መንገድ ግን አይታይም ወይም መገናኛ መንገዱን በውል አላኖረም፡፡

ጥናቱ እንደ አጠቃላይ ሲታይ የገዳሙን አመሰራረት ተረኮቹን በማንሳት፣ ቁሳዊ ባህላቸውን በመመርመር ተምሳሌታዊ ፍቺ ለመስጠትና ፎክሎራዊነታቸውን በትንታኔ ለማሳየት መነሳቱ ጠንካራ ጎኑ ሲሆን ጥናቱ የሔደባቸውና የደረሰባቸውን ነገሮች ስንመለከት ብዙ ክፍተቶች አሉበት፡፡ በመጀመሪያ የጥናቱ ዳራ የለውም፡፡ በመግቢያው ምዕራፎችን ካስተዋወቀ በኋላ በቀጥታ ወደ አነሳሽ ምክንያት ይሄዳል፡፡ የጥናቱ ወሰን ደግሞ የዳራውን ሀሳብ የያዘ ይመስላል፡፡ ኢትዮጵያ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሀገር እንደሆነች በሰፊው አስፍሮበታል፡፡

ተስፋዬ በምዕራፍ አራት ያነሳቸው የገዳማውያኑን አመጋገብ፣ አለባበስና በሰውነታቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ቁሶች በተመለከተ ሥርዓታቸውን ከመዘገብ ያለፈ ተምሳሌታዊ ፍቺ፣ ፋይዳ የሚል ነገር አላነሳም፡፡ በአጠቃላይ የተስፋዬ ጥናት ጠንካራ የማይባል አቀራረብ ሲኖረው፣ ከእኔ ጥናት ጋር ገዳም ላይ በመመስረቱና በጥቂቱ ተረክን ማጥናቱ እንጂ በተመሰረተበት ገዳም፣ በመተንተኛ ስልት እና በአቀራረብ ትልቅ ልዩነት በመካከላችን አለ፡፡

ሌላው ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በወርቁ ከተማ (2000 ዓ.ም) "የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የጨፋ መድኃኔዓለም ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሰራረትና ፎክሎራዊ ገጽታ" በሚል ርዕስ ያቀረበው ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ ይዞት የተነሳው ዓላማ በአርሲ ዞን በሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የተመሠረተው የጨፋ መድሃኒዓለም ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሰራረት እና በገዳሙ ውስጥ በፈለቀው ፀበል የማጥመቅ ስነ ሥርዓትና በገዳሙ የሚኖሩት መነኮሳት የሚፈፅሟቸውን ፎክሎራዊ ገጽታዎች ማሳየት የሚል ነው፡፡

ወርቁ በጥናቱ ምልከታና ቃለ መጠይቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ ለጥናቱ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በየትኛውም የምርምር ዘዴ እንደተነተኑ በገሃድ ባይገለጽም እንደሌሎቹ ሁሉ ገላጭ የምርመር ዘዴ መጠቀሙን መረጃዎቹ በተተነተኑበት አግባብ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ወርቁ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን አምስት ጥናቶችን ተመልክቷል፡፡አምስቱም ትኩረታቸው ገዳም ላይ እንደሆነ ጠቅሶ አምስቱም የተሰሩት በታሪክ ክፍለ ትምህርት እንደሆነም ገልጿል፡፡ ወርቁ አምስቱንም ጥናቶች በደንበኛ ተመለከታቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ምክንያቱም የየስራዎቹን መነሻና መድረሻ ሀሳብ ከመግለፅ በዘለለ ተመሳስሎና ልዩነቱን፣ የሚታይባቸውን ደካማና ጠንካራ ጎን የፈተሸ አይደለም፡፡

ወርቁ ለጥናቱ ማጎልበቻነት የክዋኔ ንድፈ ሃሳብ ተጠቅሟል፡፡ይህ ንድፈ ሃሳብ በተለይም በገዳሙ በፈለቀው ፀበል ጥምቀት በሚከወንበት ወቅት የሚስተዋለውን የክዋኔ ሥርዓት ማሳያነት ተገልግሎበታል፡፡ በተጨማሪም ከገዳሙ አመሰራረት ጋር ተያይዞ ለሚነገሩ ቃላዊ ጥበባት ሀገረሰባዊ ትረካ እና አፈ-ታሪክ የተሰኙትን ጽንሰ ሃሳቦች በማንጻሪያነት ተጠቅሟል፡፡

ወርቁ በአካባቢው ስለጸበሉ መፍለቅና ፈውስ፣ ስለአብያተ ክርስቲያናቱ መቋቋም እና ስለ ገዳሙ መመስረት አስመልክቶ ከስነ ቃል ዘርፎች መካከል ህዝባዊ ትረካ እና አፈ-ታሪኮች

የሚጠቀሱ እንደሆነ በጥናቱ አሳይቷል፡፡ መነኮሳቱ በገዳሙ ውስጥ አብረው በመኖራቸው የሚያከናውኗቸው ልዩ ልዩ ተግባራት እንዳሉና ጥቂቶቹም የአመጋገብ ሥርዓታቸው፣ የጸሎት ጊዜያቸው፣ የልማት እንቅስቃሴያቸው ሲሆኑ ይህን አስታከው የሚያከናውኗቸው ልዩ ልዩ ፎክሎራዊ ክዋኔዎች እንዳሉ በጥናቱ ተዳሰዋል፡፡

ወርቁ በጥናቱ መጨረሻ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች በፀበል ስፍራ የሚያከናውኑት በፀበል አምኖ የመጠመቅ ድርጊት ሁለቱን ወገኖች በወንድማማችነትና በእህትማማችነት ፍቅር ካስተሳሰሯቸው በርካታ ጉዳዮች መካከል አንዱ እንደሆነ ጠቅሶ ጥናቱን ደምድሟል፡፡

ወርቁ በጥናቱ ለገዳሙ መመስረት መንስኤ የሆኑ ቃላዊ ጥበባትን በገዳሙ ፀበል የማጥመቅ ሥርዓት እና በገዳሙ የሚኖሩ መነኮሳት የሚከውኗቸውን ፎክሎራዊ ገፅታና ክዋኔ ማሳየት ችሏል፡፡ በመጨረሻም የመረጃ አቀባዮችን ዝርዝር መረጃ፣ ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች፣ ጥናቱን የሚያስረዱ ፎቶግራፎች እና ጥናቱ የሚካሔድበትን ስፍራ ጠቋሚ ካርታ በጥናቱ በአባሪነት መሰነዱ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው፡፡

የወርቁ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በገዳም ላይ መመስረቱ እና በተወሰነ ደረጃ ተረኮችን በመዳሰሱ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ የእኔ ጥናት የሚመሰረትበት ገዳም፣ ተረኮቹ የሚተነተኑበት የመተንተኛ ስልትም ሆነ የመታገጊያ ንደፈ ሀሳብ ከወርቁ ጥናት የተለየ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ካየናቸው ስድስት ጥናቶች አምስቱ ተረክ በተናጠል የተጠናባቸው ሳይሆኑ ተረክ ከቁሳዊ ባህል፤ ተረክ ከስርዓት ክዋኔ ጋር ተጣምሮ የቀረበባቸው ናቸው፡፡ አንደኛው ጥናት ብቻ ተረክን በተናጠል አጥንቷል፡፡ ስለዚህ የእኔ ጥናት ተረክን በተናጠል ማጥናቱ፣ በሚመሰረትበት ገዳም እና ከአንዳንዶቹ ደግሞ በመተንተኛ ስልት ስለሚለይ የተገኘው ውጤት የተለየ ነው፡፡

# 3. አካባቢያዊ ዳራ

## 3.1. የሞጃና ወደራ ወረዳ አካባቢያዊ ገለጻ

የሞጃና ወደራ ወረዳ በአማራ ክልል ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሰሜን ሸዋ አስተዳደር ከሚገኙ ወረዳዎች አንዱ ነው፡፡ ይህ ወረዳ ከአዲስ አበባ 202 ኪ.ሜ ከደብረ ብርሃን ደግሞ 72 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የወረዳው የቆዳ ስፋት 62,200 ሄክታር ሲሆን በውስጡም 38,734 ሴቶች እና 37,971 ወንዶች በአጠቃላይ 76,704 ህዝቦች ይኖራሉ፡፡ በወረዳው የሚገኙ ሰዎችም የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው፡፡ የአየር ንብረቱ 69 በመቶ ወይና ደጋ፣ 28 በመቶ ደጋ ሲሆን 3 በመቶ ደግሞ ቆላ ነው፡፡ በወረዳው የሚኖሩ ህዝቦች በአብዛኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋኅዶ ክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡ መተዳደሪያቸውም ግብርና እና ንግድ ላይ የተመሰረተ ነው (ሀገሬ ሚዲያ፣ 2006፣ 79)፡፡

## 3.2. በሞጃና ወደራ ወረዳ የሚገኙ ቅርሶች

በሞጃና ወደራ ወረዳ የተለያዩ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ የሆኑ ኃይማኖታዊና ታሪካዊ ቅርሶች ይገኛሉ፡፡ በወረዳው ከሚገኙ ቅርሶች መካከል ምስካበ ቅዱሳን መድሃኒዓለም አንድነት ገዳም፣ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተክርስቲያን፣ የደብረ ኀኑያን ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን፣ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም፣ የወ/ሮ ዘነበወርቅ ሰገነት፣ የሰላ ድንጋይ ከተማ መነሻ የሆነው ትልቅ ድንጋይ፣ የአባት አርበኞች ማህበር የተመሰረተባት አንዲት ግራር፣ የአጃና ቅዱስ ሚካኤል የጠበል ቦታ፣ ነጭ ገደል በዓታ ለማርያም ገዳም፣ እምብስ ዋሻ፣ ተክለ ሀይማኖት ፍልፍል ዋሻ፣ የሥላሴና የጎተራ ፍልፍል ዋሻዎች ይገኛሉ (ሀገሬ ሚዲያ፣ 2006፣ 81)፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ የተመሰረተው ከእነዚህ ታሪካዊና ኃይማኖታዊ ስፍራዎች አንዱ በሆነው በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ላይ ነው፡፡

## 3.3. የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አጠቃላይ ገጽታ

### 3.3.1. የገዳሙ አመሠራረት

ከአዲስ አበባ ሲሄዱ ወደገዳሙ ለመግባት ሁለት አማራጭ መንገዶች አሉ፡፡ አንደኛው ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጋር በመውረድ፣ በጸበል ቤቱ ጋር በአቋራጭ የሚያስኬድ 1.5 ኪ.ሜ የእግር መንገድ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ሰላ ድንጋይ መናኻሪያ

በመውረድ 1.5 ኪ.ሜ ጠጠር መንገድ ነው፡፡ በሁለቱም በኩል ወደ ገዳሙ ሲገባ የገዳሙን ስርዓት የሚያሳውቁ ታፔላዎች አሉ፡፡

የገዳሙ ዋሻ መቅደስ፣ ቅድስት እና ቅኔ ማሕሌት አለው፡፡ ታቦቱ እና ነዋየ ቅድሳቱ የተሰወረበት ዋሻ ግን ስምንት በሮች እንዳለው እና በሮቹም ዘርዐ ያዕቆብ በኖራ ነጥርቀው በማተም እንደደፈኑትና ህቡዕ ስሞችን በመጥራት እንደሰወሩት ይነገራል፡፡

ገዳሙ የተመሰረተው በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት ከ1950 (G.C)[1] 1942 ዓ.ም በኋላ ነው፡፡ በገዳሙ ዋሻ ውስጥ የተሰወሩት ታቦት በንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን በአባ ሚካኤልና በአባ ገብርኤል አማካኝነት ከግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የመጣ ነው፡፡ ነገር ግን የቦታው ቅድስና ቀድሞ የነበረ እና በእግዚአብሔር የተመረጠ ቦታ እንደነበረ የገዳሙ መጽሔት ላይ እንደሚከተለው ሰፍሯል፡፡

> በስድስተኛው መቶ ክ/ዘመን በኢትዮጵያ የነገሱና በቅድስናቸው የሚታወቁት አፄ ካሌብ የሀገራቸውን ገዳማት እና አድባራት እየዞሩ ሲጎበኙ ይህንን ድንቅና ታሪካዊ ቦታ እንዶድ ዋሻን አይተው ተደሰቱ፡፡ በቦታው ጸሎት አድርገው እንዲህም በማለት ትንቢት ተናገሩ፡፡ "በዚህ ቦታ ወደፊት ትልቅ ሰው ቦታውን ያከብረዋል፡፡ በእመቤታችን ስምና በእርሱ ስም ቦታው ተከብሮ ይኖራል" (የገዳሙ መጽሔት፣ 7)፡፡

ይህ ቅዱስ ስፍራ በንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት ተመስርቶ እስከ 20ኛው መቶ ክ/ዘመን ድረስ የበቁ አባቶች ብቻ እየጸለዩበት እና የአምልኮ ስርዓቱን እያከናወኑበት ከአምስት መቶ አመታት በላይ ተደብቆ ኖሯል (የገዳሙ መጽሔት፣ 1)፡፡ ከ1980ዎቹ በኋላ የተለያዩ አባቶች እየመጡ ሲጸልዩ እና ቦታውን ሲያከብሩ ከኖሩ በኋላ በ1997 ዓ.ም አንድነት ገዳም ሆኖ ዳግም ተመስርቷል፡፡ ከዛ በፊት የገዳሙ ወሰን የነበረው ዋሻው

---

[1] ገዳሙ የተመሰረተበት ዘመን በውል ማስቀመጥ ባይቻልም በገዳሙ መጽሔት ላይ በግብጽ አሽሪፍ የተባለው ንጉስ የተነሳውና ደብረ ምጥማቅ ማርያምን ያቃጠለው በ1437/8 እንደሆነ ተጽፏል(የገዳሙ መጽሔት፣ 5-6)፡፡

ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ደግሞ በ1442 ዓ.ም. በደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስብሰባ እንዳደረገ Taddesse Tamrat "…In the mean time discussions were under way at various levels, but it was not until eight years later, in 1450, that Zar'a Ya'iqob convened a council at his new church Dabra Mitmaq in Shewa." በማለት አስፍረዋል፡፡

ስለዚህም በማኅበረሰቡ ተረክ መሰረት ከግብጽ የመጣው ታቦት እና ንዋየ ቅድሳት በዋሻ ውስጥ የተሰወረው ከደብረ ምጥማቅ ማርያም መመስረት በኋላ ነው፡፡ በመሆኑም ቁርጥ ያለውን ዘመን ማስቀመጥ ባይቻልም ከ1442 ዓ.ም. በኋላ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡

አካባቢ እና የጸበሉ ቦታ ብቻ ሲሆን አሁን ግን በውስጡ በአንድነት የሚኖሩ መነኮሳት፣ ጸበልተኞች እና ለጸሎት የሚመጡ ምዕመናን የሚያርፉበት ሰፊ ቦታ አለው፡፡

## 3.3.2. የገዳሙ አስተዳደራዊ መዋቅር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስር የሚገኘው ይህ ገዳም በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በተመደበ አንድ አስተዳዳሪ ከደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተክርስቲያን ጋር ይተዳደራል፡፡ ገዳሙና ቤተክርስቲያኑ በአንድ አስተዳዳሪ ይተዳደሩ እንጂ ለየብቻ ጽ/ቤት አላቸው፡፡

በገዳሙ ሥርዓት የበላይ አበምኔቱ ሲሆኑ ከሳቸው በመቀጠልም በቅደም ተከተል የስልጣን ተዋረድ መጋቢ ፣ምክትል መጋቢ፣ ጸሐፊ፣ ም/ጸሐፊ፣... እያለ ይቀጥላል፡፡ መነኮሳቱ ከዚህም በተጨማሪ የስራ ክፍፍል አላቸው፡፡ የንፍሮና ዳቤ ማብሰያ እንጨት የሚፈልጠው መነኩሴ "አናኮ" ይባላል፡፡ ዳቤውን እና ንፍሮውን የሚያከፋፍለው ደግሞ "እጓል መጋቢ" ነው፡፡ መነኮሳቱ በሚታመሙበት ጊዜ የሚያስታምም "ሊቀ አበው" በሚል ማዕረግ የሚጠራ ሰው አላቸው፡፡ በሴቶቹም በኩል የበላይ ተጠሪዋ እመምኔት ሲባሉ ሌሎችም የስራ ክፍፍሎች አሉ፡፡

## 3.3.3. የልማት ስራዎች

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ ሃያ አምስት ወንድ መነኮሳት እና ሰላሳ ሴት መነኮሳት ይገኛሉ፡፡ እነዚህ መነኮሳት በጾም፣ በጸሎት ከመትጋታቸው በተጨማሪ የገዳሙን ልማት ለማፋጠን እና የሰው እጅ ከማየት ለመዳን (የሚያስፈልጋቸውን ለማሟላት) የተለያዩ የልማት ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ በገዳሙ ውስጥ ከሚሰሩት ስራዎች መካከል የልብስ ስራ ተጠቃሽ ነው፡፡ እነዚህ ለመነኮሳቱም ሆነ በገበያ ቀርበው ለነዋሪዎች የሚያገለግሉት አልባሳት በሰለጠኑ እና ለዚህ ስራ በተመደቡ መነኮሳት ይመረታሉ፡፡



ምስል 1፡- የገዳሙ ልብስ መስሪያ ክፍል

ከዚህም በተጨማሪ ጠበልተኞቹን እና ምዕመኑን በማስተባበር በገዳሙ ክልል ውስጥ የእርሻ ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ ሴት መነኮሳትም ሆነ ወንድ መነኮሳት የሚኖሩበት ለየብቻ የተከለለ በአት(መኖሪያ፣ ማደሪያ) አላቸው፡፡ እንደ መነኮሳቱ ሁሉ ምዕመናንም የሚያርፉበት የወንድ እና የሴት ማረፊያ ግዙፍ አዳራሾች በገዳሙ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በጽህፈት ቤትነት የሚገለገሉባቸውን ዘመናዊ ቢሮዎችንም ገንብተዋል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ሰላ ድንጋይ ከተማ ላይ ለንግድ የሚያገለግል ሕንፃ አላቸው፡፡ ደብረ ብርሀን ከተማ ላይም ግዙፍ ሕንፃ እያስገነቡ እንደሆነ ያገኘሁት መረጃ ያመለክታል፡፡

## 3.3.4. የገዳሙ ሥርዓት

### 3.3.4.1. አለባበስ

በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩ መነኮሳት የሚለብሱት የመነኩሴ አለባበስ ሲሆን፤ ቀሚስ፣ ፎጣ እና ጭንቅላታቸው ላይ ደግሞ ቆብ ይደፋሉ፡፡ ወደ ገዳሙ የሚገቡ ጸበልተኞችም ሆኑ ለጸሎት የሚገቡ ምዕመናን የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የጠበቀ አለባበስ ይለብሳሉ፡፡ ሴቶቹ ረጅም ቀሚስ ለብሰው፤ ነጠላ ይደርባሉ፡፡ ጸጉራቸውንም በነጠላቸው ወይም በሻሽ ይሸፍናሉ፡፡ ወንዶቹም አግባብ ያለው ሱሪ፣ ሹራብ (ቲሸርት፣ ሸሚዝ) ለብሰው እንደሆነ ነጠላ ወይም ጋቢ በመስቀለኛ አጣፍተው ይለብሳሉ፡፡ ማንኛውም በገዳሙ የሚታይ ሰው ባዶ እግሩን ነው የሚሆነው፡፡ ለቅዱሱ ስፍራ ያላቸውን ክብር ሲገልጹ ጫማ አይጫሙም፡ ፡ እግዚአብሔር ሙሴን "የቆምክባት መሬት የተቀደሰች ናትና ጫማህን አውልቅ እንዳለው (ዘፀ፤ 3፣5) በገዳሙም ውስጥ ጫማ ተጫምቶ መግባት የተከለከለ ነው፡፡

### 3.3.4.2. የጸሎት ስነ-ሥርዓት

የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አባቶችና እናቶች በጸሎት የሚተጉበት ቅዱስ ስፍራ ነው፡፡ በአካለ ስጋ የሚታዩ እና የሚጸልዩ አባቶች እንዳሉ ሁሉ ከእይታ ተሰውረው የሚጸልዩ አባቶችም አሉ (ሀገሬ ሚዲያ፣ 81)፡፡ በገዳሙ ውስጥ ዋናው ተግባር ጸሎት ነው፡፡ የጋራ ጸሎት በቀን ሁለት ጊዜ በዋሻው ውስጥ ይከናወናል፡፡ ከሌሊት ዘጠኝ ሰዓት እስከ ንጋት አስራ ሁለት ተኩል ሰዓታት ይቆማል፡፡ ኪዳን ይደረሳል፡፡ ቀጥሎም የወንጌል አገልግሎት ዘወትር ከኪዳን በኋላ እስከ ጠዋቱ ሶስት ሰዓት ይከናወናል፡፡ ቀን ከዘጠኝ ሰዓት ጀምሮ እስከ አስራ አንድ ሰዓት ደግሞ የምህላ ጸሎት ይደረጋል፡፡ ከነዚህ ውጪ ያሉት ሰዓቶችንም ሰባቱን የጸሎት ሰዓቶችን ጨምሮ (ጠዋት 12፡00 ሰዓት፣ 300 ሰዓት ፣ ቀን 6፡00ሰዓት ፣ 9፡00ሰዓት ፣ ማታ 12፡00ሰዓት ፣ ምሽት 3፡00ሰዓት እና ሌሊት 9፡00ሰዓት) ቀኑም ሆነ ሌሊቱ በምስጋና እና በጸሎት ያልፋሉ፡፡ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚከወነው ሌላው ጸሎት ቅዳሴ ነው፡፡ እንደ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሁሉም በዓላትና የሰንበት ቀኖች ቅዳሴ አይከናወንም፡፡ ቅዳሴ የሚቀደሰው በአመት ለስምንት ቀናት ብቻ ሲሆን እነሱም መስከረም 21፣ ህዳር 21፣ ጥር 21፣ ግንቦት 21፣ ትንሳኤ፣ ልደት፣ ሰኔ 21 እና ነሐሴ 16 ናቸው፡፡

### 3.3.4.3. የጥምቀት ስነ-ሥርዓት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለት አይነት ጥምቀት አለ፡፡ የመጀመሪያው ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀን ሴት ልጅ ደግሞ በተወለደች በ80 ቀን የሚከናወን የእግዚአብሔርን ልጅነት የሚያገኙበት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በብዙ ቤተ ክርስቲያናት እና ገዳማት በየዕለቱ የሚተገበረው ፈውስ የሚገኝበት የጥምቀት ስነ-ስርዓት ነው፡፡

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አብዛኛው ሰው የሚመጣው ሱባኤ ለመያዝ እና ጠበል ተጠምቆ ፈውስ ለማግኘት ነው፡፡ ይህ የጠበል መጠመቅ ስነ-ስርዓት ጠዋት ከማለዳ ጀምሮ ይከናወናል፡፡ በጠበል ቤቱ የሚያጠምቅ ካህን የለም፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ራሷ እንደምታጠምቅ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ፡፡

የወንዶች መጠመቂያና የሴቶች መጠመቂያ የተለያየ ነው፡፡ ሁለት የጠበል ቤቶች ሲኖሩ ትንሹ የጠበል ቤት በ1994 ዓ.ም የተሰራው፤ ሁለት ክፍል ሲኖረው በአንድ ጊዜ ሁለት ሰው ብቻ ያስተናግዳል፡፡ ሁለተኛው እና ስድስት ሴት እና ስድስት ወንዶችን በአንድ ጊዜ

የሚያስተናግደው የጠበል ቤት ደግሞ በአትሌት ቀነኒሳ በቀለ በ1996 ዓ.ም. የተሰራው ነው፡፡ እነዚህ ጠበል ቤቶች ሳይሰሩ በፊት ለረጅም ጊዜ ሲገለገሉበት የነበረው ጠበል በተለምዶ የዐይን ጠበል እየተባለ ይጠራል፡፡ ይህንን ስያሜ ያገኘውም በጸበሉ ተጠብለው በርካታ ዐይነ ስውራን ብርሀናቸው ስለተመለሰላቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ እዚህ ገዳም ጠበል በመጠመቅ በርካታ ሰዎች ከህመማቸው እንደተፈወሱ እና አሁንም እንደሚፈወሱ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ፡፡



ምስል2፡- በ1994ዓ.ም የተሰራው ጠበል ቤት



ምስል 3፡- በ1996ዓ.ም የተሰራው ጠበል ቤት

#### 3.3.4.4. አመጋገብ

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚኖሩ መነኮሳትም ሆኑ ለጠበል እና ለጸሎት መጥተው በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ ምዕመናን የሚመገቡት በቀን አንድ ጊዜ ነው፡፡ የመነኮሳቱ የዘወትር ምግብ ዳቤ እና ንፍሮ ሲሆን፤ ምዕመናኑ ደግሞ በሶ በጥብጠው ይጠጣሉ፡፡ ቆሎ እና ቂጣም ይመገባሉ፡፡ በገዳሙ ውስጥ ሁል ጊዜ የመመገቢያ ሰዓት 11፡30 ሰዓት - 1፡00 ሰዓት ነው፡፡ ሰንበት ወይም በዓለ ሀምሳ ካልሆነ በቀር ሁሉም ቀናቶች የጾምና የጸሎት ቀናት ናቸው፡፡ ሰንበት እና በዓለ ሃምሳ ሲሆን ግን የመመገቢያ ሰዓት ጠዋት 4፡00 ሰዓት ነው፡፡ ነገር ግን ሰንበት እና በዓለ ሃምሳ ቢሆን እንኳን እንጀራ በወጥ፣ ስጋ፣ ቅቤ፣ የመሳሰሉት የላሙ የጣሙ ምግቦች ወደ ገዳሙ አይገቡም፡፡ ይህ አጥብቆ የተከለከለ ነው፡፡

### 3.3.5. በአመት የሚስተናገድ የህዝብ መጠን

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም በአመት ከ 300,000 - 400,000 የሚጠጉ ሰዎች ይስተናገዳሉ (ሀገሬ ሚዲያ፣ 2006፣ 81)፡፡ ዓመቱን ሙሉ ከተለያየ ቦታ

የመጡ በርካታ ሰዎች በገዳሙ ለጠበል እና ለጸሎት ይኖራሉ፡፡ አብይ ፆም፣ ግንቦት 21-25፣ እና ፍልሰታ ፆም ወደ ገዳሙ የሚመጣው ሰው በከፍተኛ ቁጥር ይጨምራል፡፡ ከማረፊያ አዳራሾቹ የመያዝ አቅም በላይ ስለሚሆንም በገዳሙ ውስጥ በሚገኙ ዋሻዎች እና በገዳሙ ውስጥ ድንኳን በመትከል በርካታ ምዕመናን በጸሎት የሚተጉበት ገዳም ነው፡፡ በእነዚህ ጊዜያቶች የሰው ቁጥር የሚጨምረው አብይ ጾምና ፍልሰታ ጾም የሱባኤ ጊዜ ስለሆኑ ሲሆን፣ ከግንቦት 21-25 ግን ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤ/ክርስቲያን በዓለ ንግስ ስላለ እና በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ በግብጽ ደብረ ምጥማቅ እመቤታችን በእነዚህ ቀናት እንደምትገለጥ እና በርካታ ተአምራትን እንደምታደርግ ተጽፏል(1988፣ 321-348)፡፡ በዚህም መሰረት በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ በጾምና በጸሎት ለተጉ ምዕመናን ቅድስት ድንግል ማርያም እንደምትገለጥና እንደምታነጋግር በመታመኑ ነው፡፡

## 4. በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች ትንተና

በዚህ ምዕራፍ፣ በገዳሙ ውስጥ የሚነገሩ ተረኮች በአምስት ንዑስ ርዕሶች ተከፍለው ቀርበዋል፡፡ እነርሱም፤ የገዳሙ አመሠራረት፣ የቦታ ቅድስና፣ ትንቢት፣ መንግስት እና ኃይማኖት እንዲሁም ፈውስ የሚሉ ናቸው፡፡ በተረኮቹ የተካተቱ ጥቅል ጉዳዮች ደግሞ ቅድመ ገዳም፣ የገዳሙ ተጨባጭ ሁኔታ እንዲሁም የገዳሙንና የአካባቢውን መፃኢ ዕጣ የተመለከቱ ናቸው፡፡ ከፍ ብዬ የጠቀስኳቸው ዝርዝር ነጥቦች በማኅበረሰቡ ተረኮች እንዴት እንደተገለጹ ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተረኮቹ ለማኅበረሰቡ ያላቸው ፋይዳ ተተንትኗል፡፡

### 4.1. የገዳሙ አመሠራረት

ስለ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም አመሠራረት ሲነገር ሁለት ጉዳዮችን ማጤን አስፈላጊ ነው፡፡ እነዚህም ቅድመ ምስረታና ጊዜ ምስረታ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታም በተረኮቹ እንዴት እንደተገለጸ፣ የታቦቱ ስደት፤ የቦታ መረጣና ምስረታ በሚሉ ሁለት ንዑሳን ርዕሶች ቀርቧል፡፡

#### 4.1.1. የታቦቱ (የጽላቱ) ስደት

ታቦት በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠውን መመሪያ መሠረት በማድረግ (ዘፀ 25-27) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ አገልግሎት የምትገለገልበት የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጥበት ነው፡፡ “ታቦት ማለት የእግዚአብሔር አስርቱ ህግጋት፣ የተጻፈበት፣ የሚጻፍበት ሲሆን የስሙ ማደሪያና የክብሩ መገለጫ ነው” (አበበ፣ 2005፣ 36)፡፡ በሌላ መልኩ ታቦት የእግዚአብሔር ጽላት የሚያድርበት ሳጥን መሰል ንዋየ ቅዱስ ነው (ኪዳነ ወልድ፣ 1948፣ 892)፡፡ ታቦት የሚለው ቃል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጽላቱንም ማደሪያውንም በአንድ የሚወክል ሲሆን ጽላትም ታቦትም እየተባለ እንደሚጠራ መጻሕፍት ያስረዳሉ (አበበ፣ 2005፣ 36)፡፡ ታቦት መሰራት የተጀመረው በኦሪት ዘመን ሙሴ ከእግዚአብሔር በተሰጠው መመሪያ መሰረት ነው (ዘፀ፣ 25)፡፡ ስደት ማለት ደግሞ አንድ ነገር በሚኖርበት አካባቢ (ቦታ) በሁኔታዎች አለመመቸት ወደ ሌላ አካባቢ የሚያደርገው ጉዞ ነው፡፡ ይህንንም ኪዳነ ወልድ ተሰደደ ለሚለው ግስ “ግብር መሮት፣ አገዛዝ ጸንቶበት፣ ችግር በዝቶበት ካገር ወጣ፤ አገር ጥሎ፣ ቁርበት ጠቅሎ ኼደ” በማለት ይፈቱታል (1948፣1164)፡፡

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ተረኮች ውስጥ በርካታ የስደት ገጠመኞች አሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ህዝበ እስራኤል በተለያዩ አጋጣሚዎች ተሰደዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል ከግብጽ ባርነት ወጥተው በነቢዩ ሙሴ ከዛም በኢያሱ መሪነት ለአርባ አመታት የተስፋይቱን ምድር እስኪያገኙ ተሰደዋል (ዘፀ፣12 - 40)፡፡ የክርስትና እምነት መስራች ኢየሱስ ክርስቶስ ህጻን ሳለ ከሄሮድስ ለማምለጥ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም እና ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብጽ በረሃ ተሰዷል (ማቴ 2÷13-15)፡፡ ከዘመናት በኋላም የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ከተቀበረበት ወጥቶ በተለያዩ ጊዜያት አባቶች ይዘውት መሰደዳቸውን የቤተ ክርስቲያኒቱ መጽሐፍት ያስረዳሉ (በላይ፣ 1996፣ 60-70)፡፡ በገድላት እና በቤተ ክርስቲያን ተረኮች ውስጥ የቅዱሳን አባቶች ስደት በአብዛኛው የሚታይ የጋራ ባህርይ ነው፡፡

የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የአመሰራረት ተረክ በመጀመሪያ ከስደት ይጀምራል፡፡ የገዳሙ አባቶች እና እናቶች ስለ ገዳሟ ሲተርኩ መነሻቸውን ተዓምረ ማርያም መጽሐፍ ላይ ያደርጋሉ፡፡

> …ከዚህም በኋላ ዮሐንስ ከሚባል ሊቀ ጳጳሳት ጋር የክርስቲያን ወገኖች ተሰብስበው ወደ ንጉሳችን ወደ ዘርዐ ያዕቆብ ጌታችን ንጉሳችን ሆይ ዕወቅ፤ አስተውል ብለው መልዕክት ላኩ፡፡ መመስገኛውና ማደሪያው፣ የገዳማት እናታቸው፣ የማርና የወተት መፍሰሻ፣ የክርስቲያን መመኪያ የምትሆን የከበረው የጌጣቸው መገኛ ቦታ ደብረምጥማቅ በኃጢአታችን ፈርሳለችና፡፡ ዛሬ ግን የላሞችና የበጎች መሰማሪያ ሆነች፡፡ ስለዚህ የታመናችሁ የኢትዮጵያ ወገኖች ስለጠፋው ክብራችን አልቅሱልን፡፡… ንጉሳችን ዘርዐ ያዕቆብም በደብረ ምጥማቅ አምሳል ቤተክርስቲያን እኛ እነሆ እንሰራለን አለ፡፡ ከዚህ በኋላም ቤተክርስቲያንን ባማረ በበጎ ግብር አስጊጦ ሰራ፡፡ ደብረ ምጥማቅም ብሎ ስም አወጣላት፡፡… (ተአምረ ማርያም፣ 1989፣ 63-64)፡፡

ከላይ የቀረበው ከተአምረ ማርያም ላይ የተቀነጨበው ተረክ ለታቦቱ ስደት እና አሁን ላለው ገዳም መመስረት መነሻ ነው፡፡ ይሄንን የተአምረ ማርያም ተረክ መነሻ አድርገው የታቦቱን የስደት ጅማሬ እንዲህ ይገልጻሉ፡፡

> ለመጀመሪያ ጊዜ ከግብጽ አሽራፍ የተባለው አህዛብ ንጉስ ደብረ ምጥማቅ የተባለችውን ቤተ ክርስቲያን ሲያቃጥላት አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል ታቦቷን አምጥተው ጅባት ሚጫ የተባለ ቦታ ላይ ለዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ሰጧቸው፡፡ አምጥተው ሲሰጧቸው በድንኳን ብዙ ዘመን አስቀመጧት፡፡ ከዚህ በኋላ እመቤታችን ወደ ሰሜን ይዘህኝ ሂድ ስትላቸው አምጥተው አዲስ አበባ አሁን እንጦጦ ማርያም ቤ/ክርስቲያን ያለችበት ቦታ ላይ በድንኳን አሳረፏት፡፡ አዲስ አበባ ያን ጊዜ ጫካ እና ምድረ በዳ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላም እመቤታችን ወደ ሰሜን ይዘህኝ ሂድ ስትላቸው ደብረ ብርሃን ስላሴ ቤተ ክርስቲያን ያለበት ቦታ ላይ በድንኳን አስቀመጧት፡፡ በወቅቱ ንጉሱ ብዙ ካህናት እና አብሮ የሚያጫውታቸው

መኳንንት እና ሴት ወይዛዝርቶች ነበሯቸው፡፡ በዚያ እየተጸለየ እንደተቀመጡ አሁንም ወደ ሰሜን ይዘሽኝ ሂድ እያለች በራዕይ ታነጋግራቸው ነበር፡፡ እንደገና ይዘው ሄደው እዚህ ሰላይንጋይ ባሻገር ዋሲያ የሚባል ተራራ ላይ በድንኳን አስቀመጧት፡፡ አሁንም በራዕይ ተገልጣ ከመጣህበት ወደ ኋላ ትንሽ ተመለስ አለቻቸው፡፡ እንደገና ወደኋላ ተመልሰው ቀጮ የሚባል ባለ እርሻ ኦሮሞን ከመሬቱ ትንሽ ለቤ/ክርስቲያን መትከያ ብለው ለምነው እዚያ ቦታ በድንኳን አስቀመጧት፡፡ አሁንም ደሞ ከዚያ ወደ ምስራቅ ይዘሽኝ ሂድ ይሄ ቦታዬ አይደለም ስትላቸው፣ ካህናቱንም፣ መሳፍንቱንም፣ ሁሉንም እመቤታችን ያዘዘችኝን ቦታ እስካገኘው ድረስ መፈለግ አለብኝ ብለው እናንተ ከኋላ ተከተሉኝ እኔ ልቅደም ብለው በበቅሏቸው ተቀምጠው ታቦቱን ይዘው ብዙ እንደተጓዙ ይነገራል (ደስታ ገ/ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ ከተረኩ እንደተመለከተው የታቦቷ ስደት መጀመሪያ (መነሻ) በግብጽ ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን የሚያቃጥል፣ ክርስቲያኖችን የሚያጠፋ አረመኔ ንጉስ መነሳት ነው፡፡ አሽሪፍ የተባለው ንጉስ ደብረ ምጥማቅ የምትባለዋን ቤተ ክርስቲያን አቃጠላት፡፡ በዚህ ጊዜ አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል የሚባሉ አገልጋዮች ታቦቱን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት ጅባት ሜጫ የተባለው ስፍራ ላይ ለንጉሱ አስረከቡት፡፡ ንጉሱም በታላቅ ደስታ ከተረከባቸው በኋላ ታቦቷን በድንኳን አስቀመጣት፡፡ እዚህ ላይ የተለያዩ ሐሳቦችን ማንሳት ይቻላል፡፡ ደብረ ምጥማቅ በግብጽ የተሰራችው እንዴት ነው? ቤተ ክርስቲያኗ ምን አይነት ቃል ኪዳን አላት? የሚሉት ነጥቦች ለአብነት መነሳት የሚችሉ ናቸው፡፡ ይህም በተአምረ ማርያም እንደሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል፡፡

> ዳግመኛ በኋላ ዘመን በእኔና በአንቺ ስም ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ይሰራል ብሎ ነገራት፡፡
> ለመነኮሳት ገዳም ይሆናል፡፡
> ከእሱም ተዓምራት ይገለፃል፡፡
> ለህዝቡ ሁሉ በየቋንቋው ብዙ ምስጢር ይገለፃል፡፡
> ያመኑ ሰዎች ሁሉ እስላሞችም ያዩታል… (ተዓምረ ማርያም፣ 1988፣ 321)፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ማቴ 2÷13-15 ላይ እንደተጻፈው ኢየሱስ ክርስቶስ ህጻን ሳለ ወደ ግብጽ በረሃ ተሰዶ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ በግብጽ ቁስቋም ሳሉ ለቅድስት ድንግል ማርያም ይህንን ቃል ኪዳን እንደገባላት ደግሞ በተዓምረ ማርያም መጽሐፍ ሰፍሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በቃል ኪዳኗ መሰረት ከግንቦት 21-25 ቀን በተለያየ ጊዜ ቅድስት ድንግል ማርያም ሚካኤል በቀኟ፣ ገብርኤል በግራዋ ሆነው በብርሀን መልክ ተገልጣ በርካታ ተአምራትን ያሳየችበት፣ ምእመናኑን የባረከችበት ቅዱስ ስፍራ እንደሆነ በተአምረ ማርያም መጽሐፍ ተጽፏል(1988፣ 321-348)፡፡ ታዲያ የጻድቃኔ ማርያም የታቦቷ ስደት ከዚህ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ መተረኩ በግብጽ የምትገለጠውን ድንግል ማርያም በኢትዮጵያ መገለጥ እንደምትጀምር ለመግለፅ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም በግብጽና በኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል

የቅድስና ሽሚያ (የብኩርና መነጣጠቅ)[2] እንዳለ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ ይህም መሆኑ የገዳሙ መመስረት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተዘዋዋሪም ቢሆን ግንኙነት እንዳለው ያሳያል፡፡

ከደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በአባ ሚካኤል እና በአባ ገብርኤል አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ የገባው ታቦት እዛው ጅባት ሜጫ የተባለ ቦታ ላይ ለረዥም ጊዜ በድንኳን ተቀምጧል፡፡ ድንግል ማርያም ለአጼ ዘርዐ ያዕቆብ በራዕይ ተገልጣ ወደ ሰሜን ይዘኸኝ ሂድ እስክትለው ድረስ፡፡ ከዚያም አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ታቦቷን በካህናት አስይዞ በርካታ ቦታዎች ላይ እንዳረፈች በተረኮቻቸው ይነግራሉ፡፡ ይህ ታቦት በድንኳን ካረፈባቸው ቦታዎች መካከልም አሁን እንጦጦ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተሰራበት ቦታ፣ ደብረ ብርሃን ስላሴ የተሰራበት ቦታ እና ሸዋ ተዓምረ ማርያም ይጠቀሳሉ፡፡ ከእነዚህም በተጨማሪ ብዙ ቦዎች ላይ በድንኳን አርፋለች "ልክ መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ አስቀምጡ ተብሎ የግሽን ማርያምን አምባ እስኪያገኙ እንደተሰደዱ ሁሉ እነ ዘርዐ ያዕቆብም የታቦቱን ማረፊያ እስኪያገኙ ድረስ በድንኳን እያሳረፉት ተሰደዋል" (ቤተ ማርያም፣ 05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስም ታቦተ ጽዮን /የሙሴ ታቦት/ በዳዊት ልጅ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ እስኪሰራላት ድረስ የተለያየ ቦታ በድንኳን (በእግዚአብሔር ድንኳን) ትቀመጥ ነበር (ዘፀ

---

[2] በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ እና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ግብጽ እንደተሰደዱና ሄሮድስ ሲያልፍ እንደተመለሱ ተጽፏል (ማቴ 2÷ 13-15)፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የድርሳን መጻሕፍት ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ቅድስት ድንግል ማርያም ኢትዮጵያ ውስጥ መጥተው ተቀምጠው ነበረ፡፡ አንድ ቦታ መቀመጥ ብቻ ሳይሆን በደብረ ዳሞ፣ በትግራይ፣ በጎንደር፣ በአክሱም፣ በደብረ አባይ፣ በጎጃምና በጣና እንደተዘዋወሩ እና ኢትዮጵያን እንደባረኳት ይነገራል (ድርሳነ ዑራኤል፣ 1991)፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የጌታችንን ግማደ መስቀል የሚመለከት ሲሆን፣ በወቅቱ የግብጽ ሱልጣኖች በግብጽ ክርስቲያኖች ላይ ያደርሱት በነበረው ተፅዕኖና መከራ ምክንያት በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል አለመግባባት ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሱ ዐፄ ዳዊት በግብፅ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁኔታቸው ካልተስተካከለ የአባይን ወንዝ እገድባለሁ ሲሉ በማስፈራራታቸውና በግብጻውያን ዘንድ ስጋት ስለተፈጠረ የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ነገሩን ለማርገብ የጌታ ቀኝ እጅ ያረፈበትን ግማደ መስቀል ለኢትዮጵያ መንግስት በስጦታ መልክ እንዳበረከተች ይነገራል(መንግስቱና አሳምነው፣ 98-99 ፤አበበ ጋሻዬ፣ 64-68)፡፡

እነዚህን ጨምሮ በግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ጽላት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በጻድቃኔ ማርያም ገዳም ዋሻ ውስጥ እንዳለ መነገሩ በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የቅድስና ሽሚያ (የብኩርና እሽቅድምድም) የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ጋሻዬ፣ 64-68)፡፡

እነዚህን ጨምሮ በግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የነበረውን ጽላት በአፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በጻድቃኔ ማርያም ገዳም ዋሻ ውስጥ እንዳለ መነገሩ በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የቅድስና ሽሚያ (የብኩርና እሽቅድምድም) የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

36፣ ዘፀ 40፣ ዘሌ 1)፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ ተረክም የጻድቃኔ ማርያም ገዳም ዋሻ ውስጥ ተሰውሮ የሚገኘው ታቦት በስደቱ ጊዜ በድንኳን ውስጥ ያሳድሩት ነበር፡፡ ይህ ታቦት ያረፈባቸው ቦታዎች ዛሬ ታላላቅ ቤተ መቅደሶች ተሰርተውበታል፡፡ ጉዞውም ለንጉሱ በራዕይ እየተነገረው ነበር፡፡ የገዳሙ አባቶች ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ታቦቱን ካሳረፈ በኋላ በጸሎት ይተጋ ስለነበር ድንግል ማርያም ተገልጣ ወዴት መሄድ እንዳለበት ትነግረው እንደነበር በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከታቦቱ ጋር የመጡ ብዙ መጻሕፍት እንደነበሩ እና ከእነሱም መካከል አንዱ ተዓምረ ማርያም መሆኑን የሚያሳይ ተረክ አለ፡፡

> ቤተ ክርስቲያኗ የምትሰራበትን ቦታ ፍለጋ እየተጓዙ ሳለ የተዓምረ ማርያምን መጽሐፍ ያረፉበት ቦታ ረስተውት ይሄዳሉ፡፡ ከዚያም ብዙ ከተጓዙ በኋላ መጽሐፉን እንደረሱ በማወቃቸው ሁለት ሰዎችን ይልካሉ፡፡ ሰዎቹ በሚሄዱበት ጊዜ ዝናብ ዘንቦ አካባቢው ሁሉ ጨቅይቶ ሳለ መጽሐፉ ያለበትን ቦታ ግን ምንም ውሃ ሳይነካው ደረቅ ሆኖ አገኙት፡፡ ቦታውም እስከዛሬ ተዓምረ ማርያም እየተባለ ይጠራል (እማሆይ እሴተ ማርያም፣ 06/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ የቀረበው ተረክ የታቦቱ ስደት በተአምር የታጀበ እና ለሌላ አካባቢ ስያሜ ምንጭ እንደሆነም ያሳያል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስትና አማኞች ዘንድ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው የተአምረ ማርያም መጽሐፍን ተአምር አድራጊነት የሚያሳዩበት ተረክ ነው፡፡ እንዲሁም ከታቦቱ ጋር የመጡትን መጻሕፍትና ታላቅነት እና ተአምር ሰሪነት የሚነግሩበት ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በገዳሙ ውስጥ ስለታቦቱ ስደት የሚተረኩት ተረኮች የአተራረክ ሂደታቸውን በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ይመሰርታሉ፡፡ የታቦቱ ጉዞ የመለኮታዊ ኃይል ረዳትነት ያጀበው፣ መለኮት እና ሰው የሚነጋገሩበት፣ በተዓምር የታገዘ መሆኑ እና የታቦቱ በድንኳን ማረፍ እግዚአብሔር ለሙሴ ከሰጠው ታቦት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ምዕመናን ለሚያነሱት ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ መስጠት እንዲቻል ያደርጋል፡፡ በዚህም የስውሩን ታቦት ቅድስና እና መለኮታዊ ኃይል ለማስገንዘብ እና ምዕመናኑን ለማፅናት ይጠቀሙበታል ማለት ይቻላል፡፡

### 4.1.2. የቦታ መረጣና ምስረታ

ከግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የመጣው ታቦት ለማረፊያነት የተፈቀደው ቦታ እስኪገኝ ብዙ እንደዞረ በመጀመሪያው ክፍል አይተናል፡፡ በማኅበረሰቡ ተረክ መሰረት ድንግል ማርያም ስትፈቅድ የተገኘው ቦታ አሁን ደብረ ምጥማቅ ማርያም

ቤተ ክርስቲያን ያረፈበት ቦታ ነው፡፡ ለገዳሙ መመስረት የመጀመሪያው ምስረታ ቤተ ክርስቲያኑ መሰራት እንደሆነ ከማኅበረሰቡ ተረኮች መረዳት ይቻላል፡፡ በተረክ አራት እንደተመለከተው ይህ አሁን ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተሰራበት ቦታ "በጋ ሆኖ የማይጎድል፣ ክረምት ሆኖ የማይፈስ ባህር ነበር" (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ከረጅም ጊዜ በኋላ ከበርካታ ቦታዎች መካከል ይህ ውሃማ ቦታ መመረጡ እንዴት ሊታወቅ እንደቻለ እንሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> ታቦቱን የተሸከመው ካህን እዚህ ቦታ ሲደርስ መንቀሳቀስ አቃተው፡፡ ንጉሱም በበቅሎ ቀድመው ሄደው ስለነበር ይትባረክ ውእቱ የሚባል አሽከራቸው ካህኑ መሄድ እንዳቃተው ደርሶ ቢነግራቸው ከበቅሏቸው ወርደው በእግራቸው ወደኋላ ተመለሱ፡፡ ከዚያም ካህኑን አመመህ ወይ ቢሉት ደህና እንደሆነ እና መሄድ እንዳቃተው ነገራቸው፤ ንጉሱም እንዲህ ሲሉ አዘዙ፡፡ የኔንም ድንኳን፣ የታቦቱንም ድንኳን ትከሉ፡፡ እዚሁ እንቁምና እንጸልይ አሉ (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ታቦቱን የተሸከመው ካህን መሄድ ስላቃተው ብቻ ቦታው ይህ ነው ተብሎ አልተመረጠም፡ ፡ ይልቅ ንጉሱ፣ መኳንንቱ እና ካህናቱ ሁሉ አንዳች ሳያስተጓጉሉ በምስጋና እና በጸሎት እንዲተጉ ሆነ እንጂ፡፡ ይህንንም ሲያስረዱ፡-

> … አሁን ዳዊት ሲደገም ተዋለ፡፡ ሌሊት ሰዓታትም ሲቆም አደረ፡፡ ጠዋት ቅዳሴ ተቀደሰ፡፡ አሁንም ዳዊት ሲደገም ተዋለ፤ ማታ ሰዓታት ተቆመ፤ ከዚያም ከሌሊቱ ልክ 6፡00 ሰዓት ንጉሱ ከድንኳናቸው ወጥተው ከፍ ባለ ድምጽ እልልታ አሰሙ… (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከተረኩ እንደምንረዳው ካህኑ መንቀሳቀስ ያልቻለበትን ምክንያት ለማወቅ ሁሉም በጸሎት እና በምስጋና ተጉ፡፡ ጠዋት ቅዳሴ፣ ቀን ዳዊት፣ ማታ ሰዓታት ተቆመ፡፡ እነዚህ የጸሎት ስርዓቶች አሁን ድረስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰዓታቸውን ጠብቀው የሚተገበሩ ናቸው፡፡ ይህም እነዚህን ሳያስታጉሉ መከወን ከአምላክ መልስ እንደሚያስገኝ አሁን ላሉት የእምነቱ ተከታዮች ማስተማሪያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብና አብረዋቸው ያሉት በጸሎት ስለተጉ ቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጣ "ምዕራፍየ ለዓለም" (ለዘላለም ማረፊያዬ ነው) እንዳለቻቸው ይነገራል፡፡

እንደ ማኅበረሰቡ ተረክ ይህ ባህር ለቤተ ክርስቲያን መስሪያነት ከተመረጠ በኋላ ንጉሱና አብረዋቸው ያሉት ግር እንዳላቸው እና ምን ማድረግ እንደሚችሉ ስለማያውቁ አሁንም በጸሎት መጠየቅ ጀመሩ፡፡ የገዳሙ አባቶች ይህ ባህር እንዴት ወደ ደረቅ መሬትነት ሊቀየር እንደቻለ በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡

… ከዚህ በኋላ እንግዲህ እዚህ ቦታ ከመረጠችልኝ ብለው ከዚያው ከደብረ ምጥማቅ እና ከኢየሩስአሌም 100 ግመል አፈር፣ ሶስት የመሰረት ዲንጋይ አምጥተው ባህሩ ላይ አንድ ማረሻ ባነሳ የወርቅ ቀለበት፣ ጸሎት ጸልየው ሲጥሉበት፣ ባህሩ እታች ወረደ፡፡ ይሄ አሁን ህዝቡ የሚጠመቅበት ማለት ነው፡፡ ጸበሉም ሶስት ሲሆን የበዓለ ወልድ፣ የመድኃኔዓለምና የእመቤታችን ነው… (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ ከተረክ አራት ተቀንጭቦ ከቀረበው ተረክ መረዳት የሚቻለው የገዳሙ አባቶች ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ባህር የነበረ መሬት ላይ እንደተሰራች ያምናሉ፡፡ ሙሴ በበትሩ ባህሩን በመታው ጊዜ በእግዚአብሔር ኃይል ባህሩ ለሁለት እንደተከፈለ እና ህዝበ እስራኤል በደረቅ መሬት እንደተሻገሩ (ዘፀ 14፡17-25)፤ እግዚአብሔር በጻድቁ ንጉስ በዘርዐ ያዕቆብ ላይ አድሮ ውሃውን በማድረቅ የእናቱ ቤተ ክርስቲያን እንዲሰራበት አዘዘ፡፡ ሙሴ በበትሩ ባህሩን ሲመታ እግዚአብሔር ሁለት ቦታ ከፍሎ በደረቅ አሻገራቸው፡፡ ዘርዐ ያዕቆብ በእምነት ከኢየሩሳሌም 100 ግመል አፈር አስመጥቶ አንድ ማረሻ ባነሳ የወርቅ ቀለበት ባህሩ ላይ ቢጥል ውሃው ወደ ውስጥ ሰረገ፡፡ ደረቅ መሬትም ሆነ ተብሎ ይታመናል፡፡ በገዳሙ ተረክ ሙሴ እና ዘርዐ ያዕቆብ የተጠቀሙበት ቁስ፣ የኖሩበት ዘመን እንዲሁም ያደረቁት ባህር ይለያይ እንጂ እግዚአብሔር በሁለቱም አድሮ ባህር አድርቋል፡፡

ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የተሰራችበት ቦታ የነበረው ባህር ወዴት ሄደ ለሚለውም ገዳማውያኑ መልስ አላቸው፡፡ ዛሬ በገዳሙ ውስጥ ሳያቋርጥ እየፈሰሰ ለምዕመናን ፈውስ የሚሰጠው ጸበል ውስጥ ለውስጥ ከደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የመጣ እንደሆነ ያስረዳሉ (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ፤ ቤተ ማርያም፣ 05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡ ባህሩ ደርቆ ቤተ ክርስቲያኗ ስትመሰረት በጣም ሰፊ ግዛት እና ብዙ አገልጋዮች እንደነበሯት ተራኪዎቹ ይናገራሉ፡፡ ይሄንንም ሲገልጹ፡-

የዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗ ስትመሰረት 770 የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ነበራት፡ ፡ ሰባው መነኮሳት የቀሩት አገልጋይ ካህናት እና ዲያቆናት ነበሩ፡፡ ግዛቷ የነበረው ከሞፈር ውሃ እስከ አማውሃ፣ ከፈረስ በረት እስከ ሰንበልት፣ ከሙቀጪት እስከ ጎራይት፣ ሙቀጪት የሚባለው በደብረ ብርሃን አውራጃ ነው፡፡ መንዝ ወዲያ ነው፡፡ ጭቃ ሹም 1001 ነበረ በጊዜው የሚባለው፡፡አማ ውሃ ማለት “ደብረ ሲና ነው” እራሱ ግልጽ ያለው አማውሃ ደብረ ሲና ነው፡፡ ፈረስ በረት የሚባለው በይፋት ነው፡ ፡ ሰንበልት ደግሞ በደብረ ብርሃን ወረድ ብሎ ነው፡፡ አዳባይን ተሻግሮ እስከ ሞረት ድረስ ግዛቷ ነበር (ቤተ ማርያም፣ 05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የቤተ ክርስቲያኗ ግዛት በጣም ሰፊ እና በአሁን ሰዓት ትልልቅ ከተማ ተብለው ከሚታወቁት ከደብረ ብርሃን እስከ ደብረ ሲና እንዲሁም መንዝ ድረስ የዘለቀ ነበር ይላሉ፡፡ ይህንን ማለታቸው በወቅቱ ከነበረው የነገስታት እና የቤተ ክርስቲያን ቁርኝት አንጻር እውነት ሊሆን ይችላል፡፡ አንድም በዚያ ግዛት የነበሩ ባለርስቶች ለቤተ ክርስቲያኗ ይገብሩ ነበር ለማለት ይሆናል፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ ይትበሀል ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ብዙ ጊዜውን በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያሳልፍ ነበርና፡፡

ይህቺ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተሰራች ከአመታት በኋላ አሁን ላለው ገዳም መመሰረት ምክንያት ተፈጠረ፡፡ ይህም ምክንያት የአህመድ ግራኝ መነሳት አስቀድሞ ለንጉሱ በራዕይ ስለተነገራቸው ነው፡፡

> ከዛም እዚህ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ሲጸልዩ እመቤታችን በራዕይ ተገልጻ ቤተ ክርስቲያንን የሚያወድም፣ ካህናትንም የሚያጠፋ አህዛብ መጥቷልና ነዋየ ቅድሳትን፣ ተራራውን ቆፍረህ፣ ገደሉን ጠርበህ ከዓለም ሰውር ብላ ነገረቻቸው፡፡ ግራኝ አህመድ ከመምጣቱ በፊት ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ እንደነገረቻቸው አድርገው ሰወሩት፡፡ እንደሚባለው ዋሻውን በወቅቱ የቆፈሩት የወይራ እንጨት አሹለው እንደ መቆፈሪያ በመገልገል ነው፡፡ አሁን ጻድቃኔ ማርያም ተብሎ የሚጠራው ዋሻ ገዳም፡፡ የዚህ ቦታ የቀድሞ ስሙ እንጾጽ ይባል ነበር፡፡ እንጾጽ በአካባቢው ይበዛ ስለነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ንጉሱ ንዋየ ቅድሳቱን ሰውረው አሁን የዘርዓ-ያዕቆብ ዋሻ ተብላ የምትጠራው ውስጥ በመግባት ሱባኤ ያዙ፡፡ እመቤቴ ሆይ አሁንስ መቼ ነው ከዚህ ዋሻ ውስጥ የማወጣሽ ብለው ቢጠይቋት አይ እኔ ከዚህ አልወጣም እንዳንተ የነቃ፣ የበቃ ጻድቅ ይየኝ፡፡ አንተ ወደ ህዝብህ ሂድ ስትላቸው ከዚህ በኋላ አልቅሰው ወደ ህዝባቸው ሄዱ፡፡ የገዳሙም ስም ጻድቃኔ ማርያም ተባለ (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ ከቀረበው ተረክ እንደምንረዳው ግራኝ አህመድ ከመነሳቱ አስቀድሞ ቅድስት ድንግል ማርያም ለንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ተገልጻ ጽላቱንም ሆነ ነዋየ ቅድሳቱን ዋሻ ውስጥ እንዲሰውር ነገረችው፡፡ ይህንን የዋሻ ቦታ እንዴት ሊመርጠው ቻለ ሲባል የገዳሙ መጋቢ እንደዚህ ያስረዳሉ፡፡ “...ይሄንን ቦታ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ ታቦቱን እና ንዋየ ቅድሳቱን ለመሰወር ሊመርጡት የቻሉት እመቤታችን በቀስተ ደመና አሳይታቸው ነው...” (ባህታዊ ወልደ ማርያም፣ 06/07/07፣ ቃለመጠይቅ)፡፡

የገዳሙ መመስረት ከግራኝ አህመድ መነሳት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ግራኝ አህመድ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሳ የቤተ ክርስቲያን ጠላት እንደሆነ እና ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን፣ መጻሕፍትን ያቃጠለ፣ ክርስቲያኖችን የገደለ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣1966 ፤ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ 1953፤ ፍስሀ ያዜ፣ 2003)፡

፡ እንደ ተረኮቹ ከግራኝ አህመድ  መነሳት ጋር ተያይዞ ጽላቱን ጨምሮ ብዙ መጽሐፍት፣ ከወርቅ እና ከብር የተሰሩ የቤተ ክርስቲያን መገልገያዎች እና ቅዱሳን በዋሻ ውስጥ ተሰውረዋል፡፡ በዚህ የተነሳ የገዳሙ ዋሻ የተሰወረ ታቦት እና ንዋየ ቅድሳት ያሉበት፣ በድንግል ማርያም የተመረጠ፣ የተቀደሰ ስፍራ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ስለ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን መመስረት እና ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ በደብረ ምጥማቅ ስብሰባ እንዳካሄደ የሚያሳዩ የታሪክ መዛግብት አሉ (Taddesse, 1972: 230)፡፡ ነገር ግን በእኔ ፍለጋ ስለ ጻድቃኔ ማርያም ገዳም አመሠራረት የተጻፈ ታሪካዊ መዝገብ አላገኘሁም፡፡ ስለዚህም ስለ ገዳሙ አጠቃላይ ሁኔታ  ከ500 አመታት በላይ በተረክ አማካኝነት ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቶ፣ ገዳሙ ዳግም ተመስርቷል ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ተረኮች ለገዳሙ ዳግም ምስረታ ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ገዳም አመሠራረት ተረኮች ላይ እንደተስተዋለው ታቦቱ በፊት ከነበረበት ግብጽ ደብረ ምጥማቅ ተንቀሳቅሶ ወደ ኢትዮጵያ የተሰደደው ቤተ ክርስቲያንን የሚያቃጥለው አሽሪፍ የተባለው አረመኔ ንጉስ በመነሳቱ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተሰራው ቤተ ክርስቲያንም ወጥቶ ዋሻ ውስጥ የተሰወረው ግራኝ አህመድ  በመነሳቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ታቦቱ ማንኛውም ጠላት ቢመጣ እንደማይቃጠል እና ከእግዚአብሔር የተፈቀደ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ህጻን ሳለ ለእናቱ የገባውን ቃል እየጠበቀ መሆኑን የማስረገጥ ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የታቦቱ በድንኳን ውስጥ ለረዥም ጊዜ መኖር ከታቦተ ሙሴ ጋር ፣ የዘርዐ ያዕቆብ ባህርን ማድረቅ ከሙሴ የኤርትራን ባህር መክፈል ጋር የተያያዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ያላቸው በመሆናቸው ምዕመኑ ተረኮቹን አምኖ እንዲቀበል ያስገድደዋል፡፡ ሌላው ተረኮቹ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከወኑት የጸሎት ስነ ሥርዓቶች መከበር እና መጠበቅ እንዳለባቸው በማስተማር ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ በገዳሙ ዋሻ ውስጥ የተሰወረው ታቦት ከግብጽ ደብረ ምጥማቅ እንደመጣ መነገሩም ገዳማውያኑ እና ምዕመናኑ ለገዳሙ ያላቸው ክብር እንዲጨምር እና በእምነታቸው እንዲጸኑ የማድረግ ፋይዳው ከፍተኛ ይመስለኛል፡፡

## 4.2. የሥፍራው ቅድስና

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ሁሉም ገዳማት እና አድባራት የእግዚአብሔር ቅዱስ ስፍራዎች ናቸው፡፡ ቅዱስ ማለት ለፈጣሪው ሲል ከአለም የተለየ፣ በፈጣሪው የተባረከ፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ርቆ በመልካም የተሞላ ማለት ነው፡፡ ኪዳነ ወልድ

ክፍሌ "ቅዱስ" ለሚለው ቃል "በቁሙ ልዩ፣ የተቀደሰ፣ የተባረከ፣ የነጻ፣ የበቃ፣ ብሩክ፣ ንጹህ፣ ምስጉን" በማለት ፍቺ ይሰጡታል (1948፣ 1034)፡፡

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ እና በገዳሙ አካባቢ የሚገኙ ሰዎች የገዳሙን ቅድስና በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡ ገዳሙ ቅዱስ ከሚባልባቸው ምክንያቶች አንዱ ቅድመ ገዳም ማለትም በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጸለየበትና ትንቢት የተነገረለት መሆኑ ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ ቤተ ማርያም እንደሚከተለው ይተርካሉ፡፡

> በኢትዮጵያ የነገሱና በሀይማኖታቸው ቅዱስ የሆኑት አፄ ካሌብ የሀገራቸውን ገዳማት እና አድባራት እየዞሩ ሲጎበኙ ይህንን ድንቅ ቦታ እንዶድ ዋሻን አይተው ተደሰቱ፡፡ በቦታው ጸሎት አድርገው ከጨረሱ በኋላ ወደፊት ትልቅ ሰው ይህንን ቦታ ያከብረዋል፡፡ በእመቤታችን ስምና በእርሱ ስም ቦታው ተከብሮ ይኖራል በማለት ትንቢት ተናገሩ ይባላል (ቤተ ማርያም፣ 05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ዐፄ ካሌብ በስድስተኛው መቶ ክ/ዘመን የነበሩ የአክሱም ንጉስ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ፣ ክብርና ሞገስ ያላቸው ንጉስ ናቸው(መንግስቱ እና አሳምነው፣ 2000፣ 98፤ ጋስፓሪኒ፣ 1952፣ 133)፡፡ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ቅዱስ ታቦት ሳይሰወርበት ከ1000 ዓመት አስቀድሞ ንጉሱ ቦታው ላይ ጸሎት ማድረጋቸውና ከዚያም ቦታው እንደሚከብር መናገራቸው መተረኩ የቦታውን ጥንታዊነትና ቅድስና የሚያሳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ሌላው የገዳሙን ቅድስና የሚያሳየው የቦታው አመራረጥ ነው፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ ተረክ ይህ ቦታ ገዳም ከመሆኑ በፊት ሰው የሌለበት በእንዶድ የተከበበ ጫካ ነበር፡፡ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በግራኝ አህመድ እንደምትቃጠል ለንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ቀድሞ በተነገረው ጊዜ ታቦቱን የት እንደሚሰውር አያውቅም ነበር፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ለንጉሱ ተገልጻ ታቦቱን እና ነዋየ ቅድሳቱን እንዲሰውር ስትነግረው ይህንን ቦታ ከደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተክርስቲያን ጀምሮ "ቀስተ ደመና" በመዘርጋት መርታ አሳየችው፡፡ ይህንንም በማስመልከት ሲተርኩ "…ይሄንን ቦታ አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ታቦቱን እና ንዋየ ቅድሳቱን ለመሰወር ሊመርጡት የቻሉት እመቤታችን በቀስተ ደመና አሳይታቸው ነው…" (ባህታዊ ወ/ማርያም፣ 06/07/07፣ ቃለመጠይቅ) ይላሉ፡፡

ይህ ገዳም ሲመረጥ የንጉሱ ቀልብ አርፎበት ወይም አባቶች ፀሎት ይዘውበት አይደለም፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም "በቀስተ ደመና" ጠቁማ ጽላቷ እና ነዋየ ቅድሳቱ እዚህ ቦታ ላይ መሰወር እንዳለባቸው ነግራቸው ነው፡፡

ቀስተ ደመና በተለያዩ ሀገራት እና ኃይማኖቶች የራሱ ሚታዊ ፍቺ አለው፡፡ "*Virve Sarapik"* በጽሑፋቸው ቀስተ ደመና በተለያዩ ማህበረሰቦች ያለውን ሚታዊ ትርጉም እንደሚከተለው አስፍረውታል፡፡

> Older representations of rainbow in different mythologies can be divided into animate and inanimate ones. From the latter the already mentioned image of bridge and path of gods, which binds heaven, the ulterior or gods' world and this, the human world, is rather common everywhere (e.g. Greece, Japan, Indonesia, India, Mesopotamia). The heroes of Polynesian and Hawaiian myths take by it the souls of the dead to paradise, in Indonesia it is the bridge of soul boats. In the myths of Finno-Ugric and other Nordic nations many features supposedly attributed to the rainbow have been melted with the image of the Milky Way, supported largely by their similar outward appearance. Last but not least, the folk legends grounded on Christianity depict the rainbow as a bridge by what the dead will raise to the Heaven on doomsday, with an angel sitting on it calling them with a trumpet. Underfoot of the wicked dead the bridge will break down. So the rainbow as a bridge has near always been connected with the other world, the realm of gods and dead (1998, 2).

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በተለያዩ ማኅበረሰቦች ቀስተ ደመና የአማልክት መንገድ፣ ሰማይና ምድርን የሚያገናኝ ድልድይ፣ የጻድቃን (የተጋዳሊያን) ነፍስ ወደ ገነት የምትጓዝበት መንገድ፣ የመሳሰሉት ትርጉሞች አሉት፡፡ እኔ ባደኩበት አካባቢ (ሐረር) ደግሞ "የማርያም መቀነት" እየተባለም ይጠራል፡፡

ወደ አውዱ ስንመለስ ቀስተ ደመና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ የተለያዩ ትርጓሜዎች አሉት፡፡ በኖህ ዘመን እግዚአብሔር ሰዎችን በማየ አይኅ(በጥፋት ውሃ) ካጠፋ በኋላ፣ ይህ ጥፋት እንደማይደገም ለኖህ ቃል ኪዳን ሲገባለት ምልክት አድርጎ የሰጠው ቀስተ ደመናን ነው (ዘፍ 9÷13)፡፡ ስለዚህም ቀስተ ደመና የቃል ኪዳን እና የተስፋ ምልክት ነው፡፡ ለዚህም ቅድስት ድንግል ማርያም ቀስተ ደመና ትባላለች፡፡ እግዚአብሔር በጠባብ ደረት፣ በውሱን ቁመት በመሬት ተመላልሶ አለምን ያድን ዘንድ አስቀድሞ የሰጣት የጌታ መወለድ ምልክት ናትና (ሐረገወይን፣ 1996፣ 18)፡፡ የገዳሙ አባቶችም የገዳሙ መመረጥ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለማሳየት "በቀስተ ደመና" እንደተጠቀመ ይናገራሉ፡፡ ቀስተ ደመናው ከደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን

እስከ ጻድቃኔ ማርያም ገዳም መዘርጋቱም በቤተ ክርስቲያኑም ሆነ በገዳሙ የቅድስት ድንግል ማርያም በረከት እንዳለ ለማሳየት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ቦታውም የምህረት፣ የበረከት እና የቃል ኪዳን ቦታ እንደሆነ ለማሳየት የቃል ኪዳን ምልክት የሆነው ቀስተ ደመና ተዘርግቶ እንደተመረጠ ይናገራሉ፡፡

ሌላው የገዳሙ ቅድስና የሚገለጸው ቃል ኪዳን የተገባበት ስፍራ መሆኑ ነው፡፡ የቦታው ቃል ኪዳንም ቅድስት ድንግል ማርያም ለንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ የተናገረችው ነው፡፡ ደስታ ገብረ ወልድ እንደሚተርኩት፡-

> ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ጽላቷን እና ነዋየ ቅድሳቱን በዚህ ዋሻ ውስጥ ከሰወረ በኋላ፣ ትንሽ ዋሻ በመቆፈር ሱባኤ ያዘ፡፡ እመቤታችንም ተገልጻ በምታናግረው ጊዜ ይህንን መቼ ነው ከዋሻ ውስጥ የማወጣው ብሎ ጠየቃት፡፡ እሷም አንተ አታወጣውም፣ ነገር ግን እንዳንተ የበቃ የነቃ ጻድቅ እዚህ እየመጣ ይየኝ አለችው (06/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡+

ከዚህ ተረክ መረዳት የምንችለው የገዳሙን ቅድስና ነው፡፡ "እዚህ ቦታ እየመጣ እንዳንተ የበቃ የነቃ ጻድቅ ይየኝ" የሚለው ቃል ለንጉሱ ዘርዐ ያዕቆብ የተገባለት ጻድቃኔ ማርያም ገዳም ውስጥ በምትገኝ ዋሻ ውስጥ ሲጸልይ ነው፡፡ ይህንን ቃል ኪዳን ምክንያት በማድረግ ብዙ የእምነቱ ተከታዮች ከተለያየ አቅጣጫ ስፍራው ላይ በመገኘት በጾምና በጸሎት ይተጋሉ፡፡ የአካባቢው ነዋሪዎችም ድንግል ማርያም በቃል ኪዳኗ መሰረት እንደምትገለጥ ይናገራሉ፡፡ ወ/ሮ እሸቴ ሲነግሩኝ "እመቤታችን በሶስት ቀን ጸሎት እየተገለጠች ለሁሉም ትታያለች፡፡ ማደሪያውንም ትነግራለች.." (07/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡



ምስል 6፡- ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ የጸለየበት ዋሻ (የዘርዐ ያዕቆብ ዋሻ)

ይሄ የቅድስት ድንግል ማርያም በስፍራው መገለጥ መታየት ብቻ አይደለም፡፡ ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ ምዕመናን የወደፊት ዕድላቸውን ቀድመው ያውቃሉ፡፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ትነግራቸዋለች፡፡ ከስጋዊም ሆነ ከመንፈስ በሽታዎችና ደዌዎች ፈውስን ያገኛሉ፡፡ ይህንንም ሲያስረግጡ የተለያዩ የምስክርነት ቃሎችን የሚሰጡ ሰዎች አሉ፡፡

ማንም የሰው ልጅ ዛሬ ላይ ሆኖ ወደፊት የሚገጥመውን አያውቅም፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ተረኮች ውስጥ በልዕለ ተፈጥሮአዊ (በመለኮታዊ) ኃይል ድጋፍ ይህ ሲሆን ይስተዋላል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአለም አፈጣጠር ጀምሮ የሆነው እና ወደፊት የሚሆነው በተለያዩ የትንቢት መጽሐፎች ውስጥ ሰፍሯል (ትንቢተ ኢሳያስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ የዮሐንስ ራዕይ፣ ወዘተ.)፡፡ በተለያዩ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አዋልድ መጽሐፍት ውስጥም ስለ ዓለም እና ስለ ሀገር የወደፊት እጣ ፈንታ ተነግሯል፡፡ ለምሳሌ በፍካሬ ኢየሱስ ወደፊት በኢትዮጵያ ስለሚሆነው ነገር እንደሚከተለው ሰፍሯል፡፡

> በዚያን ጊዜ ለብዙ ክብር የታጩ በማዕረግ በሹመት ያደጉ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሁሉ አደራቸውን ይዘነጋሉ፤ ሀገራቸውን ይከዳሉ፤ መሐላቸውን ያፈርሳሉ፤ ከባለሟልነታቸው ይወጣሉ፤ ከማዕረግና ሹመት ጓደኞቻቸው ይለያሉ፡፡ ክፉ ስራቸው በተገለጠባቸው ጊዜ ግን ይፀፀታሉ፡፡ በገዛ እጃቸው ታንቀው ተሰቅለው ወይም በአልባሌ ቦታ ወድቀው ይሞታሉ (ፍካሬ ኢየሱስ፣ 42-43)፡፡

ነገር ግን አንድ ግለሰብ የህይወት ውጣ ውረዱን እያስተናገደ ሳለ ዛሬ ላይ ቆሞ ነገ ምን እንደሚሆን የማወቅ አቅም የለውም (የተለየ መለኮታዊ ሀይል ከሌለው በስተቀር)፡፡ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ግን ሰው ወደፊቱን ቀድሞ ይመለከታል፡፡ ወይም በቃል ይነገረዋል፡፡ ለወደፊት እንዲህ ሊሆን ይችላል ብሎ መላምት በማስቀመጥ ሳይሆን፣ ወደፊት እንዲህ ትሆናለህ ተብሎ የሚሆነውን አውቆ ይመለሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ወ/ሮ እቴነሽ ሲነግሩኝ እንዲህ ይላሉ፡፡

> … ጥሬ ሽንብራ እየቆረጠሙ በሚጸልዩበት ጊዜ ትገለጥላቸዋለች፡፡ ማደሪያቸውን ታሳያቸዋለች፡፡ ገበሬም ከሆነ ግብርናውን፣ ነጋዴም ከሆነ ንግዱን፣ መምህርም ከሆነ ወደ መምህርነት እንዲሰማሩ ያንን ትነግራቸዋለች፡፡ ሁሉም እንዳለቻቸው ይሆናል (07/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

እነዚህ ሰዎች ቅድስት ድንግል ማርያም እንደምትገለጥና የወደፊት እጣ ፈንታን እንደምትናገር በሙሉ እምነት ያስረዳሉ፡፡ ይህንንም ሲሉ ለአብነት የተደረገላቸውን (ወደፊታቸው የተገለጠላቸውን) ግለሰቦች እየጠቀሱ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ የአሁኑ የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ኤፍሬም ልጅ እያሉ እዚህ ገዳም ውስጥ ገብተው ጸሎት ሲያደርጉ "…ትልቅ ዙፋን እያሳየቺኝ ይህ የሥላሴ ወንበር ነው፡፡ ወደፊት እዚህ ላይ

ትቀመጣለህ አለችኝ....” በማለት መፃኢ ዕጣን እንደምትናገር ምስክርነት ሰጥተዋል (የገዳሙ መፅሂት ቁጥር 2፣ ገፅ 76)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ደስታ ተክለ ወልድ ገዳሙ ውስጥ “በማገለግልበት ጊዜ ብዙ ሰዎች በጾም በጸሎት ከተጉ በሶስተኛው ወይም በሰባተኛው ቀን እመቤታችን እየተገለጠችላቸው ፈውስን እንደሰጠቻቸው እና ወደፊት የሚሆኑትን እንደነገረቻቸው ይነግሩኝ ነበር” በማለት አስረድተውኛል፡፡

ይህ የወደፊትን ማወቅ በገዳሙ ውስጥ እንደሚቻል መነገሩ ገዳሙ ቅዱስ እንደሆነ፣ ማንኛውም ሰው አምኖ ወደዚህ ስፍራ ቢመጣ እና ሱባኤ ቢይዝ ሀሳቡ እንደሚሞላለት ምዕመኑ እንዲያውቅ፣ ለገዳሙ ክብር እንዲኖረው፤ የገዳሙን ስርዓት እንዲፈጸም የማድረግ ፋይዳ አለው፡፡

ከተለያዩ ደዌዎች መፈወስን “ፈውስ” በሚለው ርዕስ የምንመለከተው ይሆናል፡፡ በዚህ ገዳም የወደፊትን ለማወቅም ሆነ ከደዌ ለመፈወስ ገዳሙ ውስጥ ሲገቡ መተግበር ያለባቸው ህጎች አሉ፡፡ እነዚህ ህጎች በብዙ ገዳማት ያሉ ሲሆኑ ይህ ገዳም ከሌሎች ገዳማት የሚለይበትን እንዲህ በማለት ይናገራሉ፡፡

> እንጀራ እዚህ ገዳም ውስጥ አይገባም፡፡ ምክንያቱም የሱባኤ ቦታ ነው፡፡ ገዳሙ ውስጥ ይዞ መግባት የሚፈቀደው ዳቦ፣ ቆሎ እና በሶ ብቻ ነው፡፡ ይህም አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ምንም ሳይጎድልበት የላመ የጣመ ሳያምረው ከቆመ ሳይቀመጥ፣ ከዘረጋ ሳያጥፍ ሱባኤ መያዙን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ቦታ ከሌሎች ቦታዎች ሁሉ የሚለየው የሱባኤ እና የጥሞና ቦታ መሆኑ ነው (ባህታዊ ወልደ ማርያም፣ 06/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ ባህታዊ ከተናገሩት ተረክ መረዳት የሚቻለው ገዳሙ የተለየና የተቀደሰ መሆኑን ነው፡፡ ከሁሉም ስፍራ ፈውሰ ስጋ ፈውሰ ነፍስ ለማግኘት የሚመጡ ምዕመናን ይህንን ህግ ማክበር አለባቸው፡፡ ይህን ህግ ካላከበሩ ግን በምህረት ፈንታ መቅሰፍትን፣ በፈውስ ፈንታ በሽታን ይሸምታሉ ብለው ያምናሉ፡፡ ጽሞና እና ጸሎት በሁሉም ገዳም ያለ ቢሆንም ገዳማውያኑ ግን የሚለይበት ብለው መናገራቸው አንድም የገዳሙን ቅድስና ለማግዘፍ፤ አንድም በገዳማውያኑና በምዕመናኑ ዘንድ የገዳሙን ታላቅነት ለመትከል የታሰበ ሊሆን ይችላል፡፡

በብዙ ገዳማት የሚበላው በቀን አንድ ጊዜ ነው፡፡ በየቦታው ምን መበላት እንዳለበት ይታወቃል፡፡ የሰው ልጅ ህይወቱን ለማቆየት እና ጤነኛ ሆኖ ለመኖር የተመጣጠነ በቂ ምግብ ያስፈልገዋል፡፡ በገዳም ህይወት ግን መናንያን እና መነኮሳት በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ይመገባሉ፡፡ ይህም የተመረጠ ምግብ ነው፡፡ ወደ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን

አንድነት ገዳም የሚሄዱ ምዕመናንም የለመዱትን በቀን ሶስት ጊዜ የመብላት ሁኔታ ያስወግዱና በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ይመገባሉ፡፡ በከተማ ሳሉ እየመረጡ የሚበሉትን የምግብ አይነት ረስተው ቆሎ፣ በሶ እና ቂጣ ብቻ እንዲመገቡ ይደረጋሉ፡፡ እነዚህንም የሚመገቡት እንዳገኙ ሳይሆን በተመጠነ መልኩ ነው፡፡ ይህም የሚደረገው የዘርዐ ያዕቆብን ሱባኤ መሰረት በማድረግ እንደሆነ ባህታዊ ወልደ ማርያም ያስረዳሉ፡፡ በማኅበረሰቡ እምነት ይህ ካልተደረገ ፈውስ የለም፡፡ ይህ ካልተተገበረ ምህረት አይኖርም፡፡ የመጡበትም አይሳካም፡፡ ይህንንም የገዳሙ እናቶችና አባቶች ብቻ ሳይሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎችና ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ምዕመናን በሙሉ እምነት ህጉን ይፈፅማሉ፡፡ ህጉን ካከበሩ የፈለጉት እንደሚደረግላቸው ያምናሉ፡፡

እንጀራ እና ሌሎች ምግቦችን መመገብ በገዳሙ ውስጥ ክልክል እንደሆነ መነገሩ በምዕመናኑ ዘንድ ለገዳሙ ያላቸውን ክብር በመጨመር እና ይደረግልኛል የሚለውን እምነት በማጽናት በኩል ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል፡፡

ሌላው የዚህ ገዳም ቅድስና መገለጫ የተሰወረ ታቦት እና ነዋየ ቅድሳት አለ ተብሎ መታመኑ ነው፡፡ ይህ ታቦት እና ነዋየ ቅድሳት ኢየሱስ ክርስቶስ ህጻን ሳለ ለእናቱ ቤተ ክርስቲያን እንደሚሰራ ቃል ከገባበት ቦታ መምጣቱ ዋጋውን ከፍ ያደርገዋል፡፡ ከታቦቱ በተጨማሪ በዚህ ገዳም ዋሻ ውስጥ ተሰውረዋል ተብሎ የሚታመነው ከወርቅና ከብር የተሰሩ መገልገያዎች እና መጻሕፍት ናቸው፡፡ እነዚህንም ደስታ ተክለ ወልድ ሲናገሩ፡-

> አሁን ዋሻው ውስጥ አለ ተብሎ የሚነገረው የቤተ ክርስቲያኗ መገልገያ 1000 ሺህ (አንድ ሺህ) መጻሕፍት፣ የንጉሰ ነገስቱ 80 (ሰማኒያ) የጸሎት መጻሕፍት፣ 6 (ስድስት) ጽላት፣ 50 (ሃምሳ) የወርቅ ጽናጽል፣ 50 (ሃምሳ) የብር ጽናጽል፣ 50 (ሃምሳ) የወርቅ መቋሚያ፣ 50 (ሃምሳ) የብር መቋሚያ፣ 2 (ሁለት) የወርቅ ከበሮ፣ 2 (ሁለት) የብር ከበሮ፣ 2 (ሁለት) የወርቅ ጫማ (ታቦት ተሸካሚው ቄስ የሚጫማው)፣ ይሄ ሁሉ ንብረት ዋሻ ውስጥ ታሽጓል፡፡ አብረው የተሰወሩት አባ ገብረ ህይወት እዛ ውስጥ አጽማቸው አለ ይባላል (08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ታቦት እና ንዋየ ቅድሳቱ በዋሻ ውስጥ እንደተሰወሩ ሁሉም ያለ ጥርጥር ያምናል፡፡ ለአምልኮ መገልገያ የሚሆኑ ከወርቅ እና ብር የተሰሩ መሆናቸውም መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ሲያስረዱ "ጌታችን በተወለደ ጊዜ ሰብዓ ሰገል ወርቅ፣ እጣን እና ከርቤ አመጡለት ይላል (ማቴ፡2) ወርቅ ለመንግስቱ፣ እጣን ለህይወቱ ከርቤ ለሞቱ ወርቅና ብር ለጌታ ለመንግስቱ ስለተሰጠ ነው" (ደስታ ተክለ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ) ይላሉ፡፡ አያይዘውም ይህንን እውነትነት ለማረጋገጥ በንጉሱ ዘመን ዋሻ ውስጥ ለመግባት እንደተሞከረ እና ውስጡ ባህር እንደሆነ፣ አለ የሚባሉትም ታቦትና ንዋየ ቅድሳት እንዳሉ

አቅርቦ በሚያሳይ መነጽር (ቴሌስኮፕ) ማየት መቻሉን ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ሁኔታ የእድሜ ባለፀጋ የሆኑት ቤተ ማርያም ሲያስረዱ የሚከተለውን ነግረውኛል፡፡

> … በኋላም መንግስት ልኳት አንዲት ፈረንጅ ተናኘወርቅ ከተባለችው የጃንሆይ ልጅ ጋር በመሆን ወደዚህ መጡ፡፡ ዋሻው ተመርምሯል ሲመረመር ታቦቷ ያለችበትን ለማግኘት እውስጡ ባህር አለ፣ ቁጠማ አለ ታቦቷን ለማግኘት ያንን ተሻግሮ ነው ያለችው፡፡ ውሃውን ተሻግሮ ለማውጣት ስለማይቻል ቦታው በድማሚት ቢፈነዳ እና ውሃው ቢሄድ ታቦቷን ማውጣት ይቻላል አለች ፈረንጂ፡፡ የአካባቢው ነዋሪም መቅሰፍት ይመጣብናል፣ ጊዜው ሲደርስ የበቃ ሰው ያወጣታል ብለን በመከልከላችን ተመልሰው ሄዱ (05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ይህ ተረክ በቃለ መጠይቅ ቆይታ ያደረጉ ሁሉ የሚናገሩት ነው፡፡ ዓመተ ምህረቱን በግልጽ ባያስቀምጡትም በንጉሱ ዘመን የንጉሱ ልጅ ልዕልት ተናኘወርቅ ከአንዲት የውጪ ዜጋ ጋር ወደ ቦታው ሄዳለች፡፡ ወደ ቦታው የሄደችውም በገዳሙ ዋሻ ውስጥ አለ የሚባለውን የቤተ ክርስቲያን ንብረት ለማየት ነው፡፡ ወደ ዋሻው ገብተው አለ የሚባለው ታቦትና ንዋየ ቅድሳት እንዳለ አይተው ለአካባቢው ሰው መናገራቸው በማኅበረሰቡ ይታመናል፡፡

በቅርብ ጊዜ እውን ከነበረች ልዕልት ተናኘ ወርቅ ጋር ተያይዞ በአይኗ ማየቷን መናገሯን ከራሷ አንደበት መስማታቸውን የዕድሜ ባለፀጎች መናገራቸው የተረኩን ተአማኒነት ከፍ ያደርገዋል፡፡ ይህ መተረኩ ለገዳሙ እና ለገዳሙ ማኅበረሰብ በግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም የነበረችው ጽላት አሁን በዚህ ዋሻ ውስጥ እንዳለች የእምነቱ ተከታዮች ውስጥ እምነቱ እንዲጸና ያደርጋል፡፡ ከዚህም ባሻገር በግብጽ ደብረ ምጥማቅ የምትገለጸው ማርያም ዛሬ በዚህ ገዳም ውስጥ እየተገለጸች ማናገሯ እና ምህረትን መስጠቷን እውን ያደርገዋል፡፡ በተዓምረ ማርያም መጽሐፍ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእናቱ ቃል ገብቶላታልና፡፡ ከዚህ ጋር ማያያዛቸውም የግብጽን በረከት በኢትዮጵያም እንዳለ ለማሳየት እና ህዝበ ክርስትያኑ ወደ ቦታው ሄዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም በረከት እንዲያገኝ ፍላጎትና ጉጉት ያጭርበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለገዳሙ የሚኖረው ክብር ከፍ እንዲልና የገዳሙን ስርዓት በአግባቡ እንዲፈጽም ተጽዕኖ ያሳድራል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው የዚህን ገዳም ቅድስና የሚያሳየው ተረክ ከቅዱሳን አጽም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በአካባቢው ተወልደው ያደጉት ደስታ ተክለ ወልድ ልጅ እያሉ አባታቸው ነጭ አሞራ በንጹህ ጨርቅ የተጠቀለለ የሰው አጽም አምጥቶ ዋሻ ውስጥ ሲያስቀምጥ ማየቱን እንደነገራቸው ይናገራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እሳቸው ራሳቸው ዋሻ ውስጥ ሄደው

አጽሙን እንዳዩ ነግረውኛል፡፡ ከእሳቸው በተጨማሪ ወ/ሮ እሸቴ "… ልጅ እያለን ገዳሙ ውስጥ ትንሽ ዋሻ ነበረች፡፡ ከላይ ደግሞ ሌላ ዋሻ ነበረ እዛ ላይ ቧጥጠን… ቧጥጠን ስንወጣ ትኩስ ሬሳ በጨርቅ ተሸፍኖ እናይ ነበር፡፡ ማን እንዴት እንደሚያመጣው ግን አይታወቅም…" (07/07/07፣ ቃለ መጠይቅ) በማለት ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች ዋሻ ውስጥ አይተናል የሚሉት አጽም አሁን ድረስ እንዳለ ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን አንዳንዶቹ ማን; እንዴት; እንደሚያመጣቸው አናውቅም ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ነጭ አሞራ እያመጣ ያስቀምጥ እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ይህንም "መልአክ በነጭ አሞራ ተመስሎ ነው" በማለት ሀሳባቸውን ያጠናክራሉ፡፡ እነሱ እንደሚሉት መልአክ የቅዱሳንን አጽም እያመጣ እዚህ ቦታ ላይ ማሳረፉ ቦታው በእግዚአብሔር የተመረጠ እና ቅዱስ ስለሆነ ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በክርስትና ታሪክ ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ ያላቸው አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል የሚባሉ አገልጋዮች እንደነበሩ ተዓምረ ማርያም ላይ ተጽፎ ይገኛል፡፡ ዛሬም ድረስ ካህናት ተዓምረ ማርያምን ሲያነቡ "እኛ አባ ሚካኤል እና አባ ገብርኤል በምንባል…" እያሉ ነው፡፡ እነዚህ አገልጋዮች የደብረ ምጥማቅ ማርያምን ታቦት ከግብጽ አምጥተው ለንጉሱ የሰጡት ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ ከሁለቱ አንዱ አባ ገብርኤል ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አጽማቸው እንዳረፈ ይነገራል፡፡ ይህም ስፍራውን የተቀደሰ እንደሆነ ለማሳየት የሚያገለግል ነው ማለት ይቻላል፡፡

በኃይማኖት ተቋማት የኃይማኖቱ ቅዱሳን የተቀበሩበት ስፍራ ትልቅ ክብር ይሰጠዋል፡፡ ማንነታቸው የማይታወቅ ቅዱሳን አፅም "መልአክ በነጭ አሞራ ተመስሎ" እያመጣው እዚህ ቦታ ማረፍ እና የአባ ገብርኤል አፅም እዚህ ቦታ እንዳረፈ መነገሩ የቦታውን ቅድስና የሚያሳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

## 4.3. ትንቢታዊ ተረኮች

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ የገዳሙን እና የአካባቢውን መጻኢ ዕጣ በማስመልከት የሚነገሩ ተረኮች አሉ፡፡ በአብዛኛው እነዚህ ተረኮች መቼ እንደሆነ ባይገልጹም (ዘመኑን በውል ባይጠቅሱም) "ወደፊት ገዳሙ እንደዚህ ይሆናል፤ አካባቢው ላይ እንደዚህ አይነት ነገር ይከሰታል" እያሉ ወደፊታቸውን ይተነብያሉ፡፡ እነዚህ ትንቢታዊ ተረኮች መጀመሪያ ማን እንደተናገራቸው በውል ባይታወቅም፤ በጽሁፍ ሰፍረው ባይገኙም፤ በገዳሙ አካባቢ ያሉ ማኅበረሰቦች በእርግጠኝነት እንደሚፈጸሙ

ያምናሉ፡፡ ሊቀ ጠበብት ቤተ ማርያም የሚሆነውን ከመናገራቸው በፊት እውነትነቱን ለማስረገጥ ተነግረው የተፈጸሙትን ያቀርባሉ፡፡

> … ልጅ እያለን ይህ ስፍራ እንዳሁኑ ዕውቅና ሳያገኝ በፊት አባቶቻችን ሲነግሩን ወደፊት ይህ ቦታ እግዚአብሔር የሚከብርበት ድንግል ማርያም የምትገለጥበት ይሆናል፡፡ ከብዙ ቦታ ሰዎች እየተሰበሰቡ ይጸልዩበታል፤ ለህመማቸው ፈውስ፣ ለችግራቸው መፍትሄ ያገኙበታል፣ ይሉን ነበር፡፡ ይሄ አሁን በአይናችን የምናየው ነው (05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በማለት ያለፉና የተፈጸሙ ትንቢቶች ላይ በመመስረት ወደፊት ይሆናል ተብሎ የሚነገረውን በእምነት እና በእርግጠኝነት ይተርካሉ፡፡ደስታ ተክለ ወልድም ሲያስረዱ፡-

> ዕድሜ ከሰጣችሁ ታያላችሁ እናንተ ባታዩ ግን የልጅ ልጆቻችን ያዩታል እያሉ አባቶቻችን የነገሩንን አሁን አይተነዋል፡፡ ስለዚህ ወደፊት ይሆናል የሚባለው የማይሆንበት ምክንያት አይታየኝም፡፡ አባቶቻችን ከራሳቸው ፈጥረው የሚያወሩት የለም፡፡ ከቅዱሳን የተረዱትን እና እግዚአብሔር ያቀበላቸውን ነው እንጂ (08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

በማለት ትንቢታዊ ተረኮቹ እንደሚፈጸሙ በእርግጠኝነት ይናገራሉ፡፡ "እግዚአብሔር ካለ" የሚለውን የዕምነት እና የፈጣሪ ፈቃድ እንደሚሆን የሚያሳውቀውን ሐረግ ጣል በማድረግ፡፡ ስለዚህ በአካባቢው ላይ ወደፊት ይሆናል (መፃኢ ዕጣችን ይሄ ነው) ብለው የሚናገሯቸው ተረኮች የታቦቱና የንዋየ ቅድሳቱ መገለጥ እና የገዳሙ መግነን እና የአካባቢው ማደግ በሚሉ ርዕሶች ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 4.3.1. የታቦቱ እና የንዋየ ቅድሳቱ መገለጥ

ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም መመስረት ዋነኛ ምክንያት ከግራኝ አህመድ መነሳት ጋር በተያያዘ ከደብረ ምጥማቅ ማርያም የመጣው ታቦት እና ንዋየ ቅድሳት በገዳሙ ዋሻ ውስጥ መሰወር ነው፡፡ ይህ ታቦት እና ንዋየ ቅድሳት ተሰውሮ እንደማይቀር እና ጊዜው ሲደርስ እንደሚወጣ የገዳሙ አባቶችና የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡ መቼ ነው የሚወጣው የሚለውን ሲመልሱ ምልክቶችን ያስቀምጣሉ፡፡ ቤተ ማርያም ታቦቱ እንደሚወጣ እና ልትወጣ ስትል ቀድመው የሚታዩትን ምልክቶች እንደሚከተለው ይናገራሉ፡፡

> አባቶቻችን ሲሉን ለእናንተ ለልጆቻችን ካደረሳችሁ የመውጫዋ ጊዜ ሲደርስ ትወጣለች፡፡ ይህም ሲደርስ ምልክት ታያላችሁ፡፡ ከምልክቶቹም አንዱ ገደሉ ይናዳል፡፡ ገደሉ በተናደ ጊዜ የመውጫ ጊዜዋ እንደደረሰ እወቁ ይሉን ነበር፡፡

> እንደውም ገደሉ ተንዷል የተናገሩት ትንቢት እየደረሰ ነው፡፡ መውጫዋ ደርሷል (ቤተ ማርያም፣ 05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

እንደ ቤተ ማርያም ሀሳብ የመውጫው ጊዜ መድረሱ ከሚታወቅባቸው ምልክቶች አንዱ "የገደሉ መናድ" ነው፡፡ ገደሉ የተባለው የገዳሙ ዋሻ የተቦረቦረበት ቦታ ያለው እንደሆነ እራሳቸው ቤተ ማርያም ነግረውኛል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መጨረሻ መቼ ይሆናል ብለው ሐዋርያቱ ሲጠይቁት ጊዜውን በውል ከመናገር ይልቅ ጊዜው ሲደርስ የሚከሰቱ ምልክቶችን ነግሯቸዋል (ማቴ 24÷1-34)፡፡ እነዚህ አባቶችም የታቦቱን እና የንዋየ ቅድሳቱን መውጫ ጊዜ በውል ከመናገር ይልቅ በኃይማኖታቸው መስራች አነጋገር(የአተራረክ ስልት) ተጠቅመው መውጫው ሲደርስ የሚታዩ ምልክቶችን ሲናገሩ ይስተዋላል፡፡

ሌላው የታቦቱ እና የንዋየ ቅድሳቱ መውጫ ሲደርስ የሚታየው ምልክት በደብረ ምጥማቅ ግቢ ውስጥ ግዙፍ (ትልቅ) ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መሰራት ነው፡፡ ይህ ቤተ ክርስቲያን ሲሰራ ታቦቱ እንደሚወጣ እና ቀድሞ በነበረበት መንበር እንደሚቀመጥ፤ የገዳሙና የቤተ ክርስቲያኑ ግዛትም በአንድ እንደሚጠቃለል በተረኮቻቸው ያስረዳሉ፡፡

> … ልጅ እያለን በጣም ትልቅ ህንጻ ቤተ ክርስቲያንም ይሰራል፡፡ በዚያን ጊዜ ጽላቷ ተገልጣ ትከብራለች፣ ጳጳስና መነኩሴ ብቻ ይቀድስባታል፡፡ መንግስትም ቆሞ ያስቀድስባታል፡፡ በአካባቢዋ ላይ ምንም አይነት መንደርም አይኖርም፡፡ በዚያን ጊዜ የበሬ መኝታ ታህል ቦታ በኖረችኝ የሚባልበት ጊዜ ይመጣል እያሉ ይናገሩ ነበር (እቴነሽ ነገደ ወርቅ፣ 07/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

የአካባቢው ሰዎች የታቦቱ እና የንዋየ ቅድሳቱ መውጫ ሲደርስ ይታያል ብለው የሚያስቀምጡት ሌላው ምልክት ደግ ንጉስ ሲነግስ እና መልካም ጳጳስ ሲሾም ነው፡፡ ይህንንም ሲተርኩ "እግዚአብሔር የፈቀደ ጊዜ ህጻን መንግስት ይመጣል፡፡ በመላው ህዝብም ፍቅረ ሰላም ይወርዳል፡፡ ታቦቷም በነበረችበት ቦታ ትቀመጣለች" (ደስታ ገብር ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ይህ ምልክት የታቦቱን መገለጥ ከሀገራዊ ሁኔታ ጋር የሚያያይዝ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ቤተ ክርስቲያን እና ቤተ መንግስት በአንድ ሆነው አገር ሲያስተዳድሩ ነበር፡፡ ንጉስ ያለ ቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም ያለ ንጉስ ተነጣጥለው የሚታዩ አልነበሩም፡፡ ነገስታት በጳጳሳት ይቀቡ ነበር፡፡ ጳጳሳትም ከነገስታቱ ጋር በመተባበር ይሰሩ ነበር፡፡

እነዚህ በጻድቃኔ ማርያም ገዳም አካባቢ የሚገኙ ማኅበረሰቦችም ያለፈውን ታሪክ በመመስረት ይመስላል ወደፊት እንደሚሆን የሚያምኑት፡፡ የመልካም መንግስት መነሳት

እና የደግ ጳጳስ መሾምን በዋሻ ውስጥ ተሰውሮ ለሚገኘው ታቦት እና ነዋየ ቅድሳት የመውጫ ጊዜ መድረስ በምልክትነት ያስቀምጣሉ፡፡

በአጠቃላይ በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩና በገዳሙ አካባቢ ያሉ ማኅበረሰቦች ከግብጽ ደብረ ምጥማቅ መጥቶ በጻድቃኔ ማርያም ዋሻ ውስጥ የተሰወረው ታቦት እና ነዋየ ቅዳሳቱ ወደፊት እንደሚወጡ ያምናሉ፡፡ ለዚህም ሶስት ነገሮችን የመድረሻ ምልክት አድርገው ያስቀምጣሉ፡፡ በገዳሙ ውስጥ ያለው ገደል መናድ፣ በደብረ ምጥማቅ ግቢ ውስጥ ትልቅ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን መቆም (መሰራት)፣ የደግ ንጉስ መነሳትና መልካም ጳጳስ መሾም ናቸው፡፡ እንደ ቤተ ማርያም አነጋገር ገደሉ ተንዷል፡፡ ግዙፍ የተባለው ህንጻ ቤተ ክርስቲያንም እየተሰራ ነው፡፡ ደግ ንጉስ እና መልካም ጳጳስ መሾም የሚለው ደግሞ ገና እንደሆነ ያምናሉ፡፡ እነዚህ ማኅበረሰቦች የታቦቱን እና የንዋየ ቅድሳቱን ወደፊት መውጣት ይጠብቃሉ፡፡ ጊዜውንም ከአምላካቸው የትንቢት አነጋገር ስልት ጋር በማመሳሰል በምልክት ይናገራሉ፡፡ የሚናገሯቸው ትንቢቶች እንደሚፈጸሙ ለማረጋገጥ ደግሞ ከዚህ በፊት ሲነገሩ የነበሩ እና ተፈፅመው (ደርሰው) የተመለከቷቸውን በማስረጃነት ያቀርባሉ፡፡

እነዚህ ተረኮች ገዳሙ ከመለኮታዊ ኃይል ጋር ያለው ትስስር ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ በዚህ የተነሳም የሀይማኖቱ ተከታዮች ለገዳሙ ከፍተኛ ክብር እና የተለየ ቦታ አላቸው፡፡ ከሁሉም ክፍላተ ሀገራት እየመጡ ጸበል በመጠመቅ ሱባዔ እንዲይዙ እና ገዳሙን እንዲረዱ ምክንያት ሆኗል፡፡ የገዳሙ እናቶችና አባቶችም በህይወታቸው ውስጥ ባሉበት በጾምና በጸሎት እንዲተጉ እና የዕምነት ጽናት እንዲኖራቸው ያደርጋል ማለት ይቻላል፡፡

### 4.3.2. የገዳሙ መግነን እና የአካባቢው ማደግ

የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ታቦት እና ንዋየ ቅድሳቱ ከዋሻው ከወጡ በኋላ ምን አይነት ለውጥ ይታያል ለሚለው ማህበረሰቡ የራሳቸው መልስ አላቸው፡፡ ታቦቱ ከወጣ በኋላ ገዳሙ በጣም እንደሚገን እና ለአካባቢው ማደግም ምክንያት እንደሚሆን በእምነት ይናገራሉ፡፡ በገዳሙ መግነን የተነሳ አካባቢው ትልቅ ከተማ እንደሚሆን፣ ለመኖሪያ የሚመረጥ፣ እግሮች ሁሉ የሚያመሩበት እንደሚሆን ሊቀ ጠበብት ቤተ ማርያም ሲተርኩ፡-

> በዚያን ጊዜ በሰላ ድንጋይ የበሬ መኝታ የምታህል ቦታ በነበረኝ የሚባልበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ሰው ይበዛል፣ ከተማም ትሆናለች ዘበኛም ይቆምበታል፣ በዚያን ጊዜ በእመቤታችን ጸበል ህሙማን ይፈወሳሉ ድውያን ይድናሉ ተብሏል እየተባለ ይነገር ነበር (05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከተረኩ መረዳት የሚቻለው የአካባቢው ነዋሪዎች የከተማቸው እድገት ከገዳሙ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ማመናቸውን ነው፡፡ “የበሬ መኝታ ታህል ቦታ በነበረኝ የሚባልበት ጊዜ ይመጣል” የሚለው አገላለጽ አብዛኞቹ ተራኪዎች የሚጠቀሙት ነው፡፡ ይህም ከገዳሙ ጸበል ፈውስን ፍለጋ የሚመጣው ሰው ሲበዛ፣ በአቅራቢያዋ መኖር የሚፈልገው ይበዛል፡፡ በዚህ ምክንያት ደግሞ ህዝብ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የሰው ፍላጎት ይጨምራል፡፡ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታም ፍላጎት ይጨምራል፡፡ ስለዚህ በአካባቢው ቦታ ማግኘት የማይቻልበት ጊዜ እንደሚመጣ የሚናገሩበት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ተራኪዎቹ ይህንን ሲያስረዱ ታቦቱ ከመገለጡ በፊት (አሁን) ራሱ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ የትንቢታቸው መደገፊያ ያደርጉታል፡፡ ከ1997 ዓ.ም በፊት ገዳሙ አንድነት ገዳም አልነበረም፡፡ ግዛቱም ዋሻዋ ያለችበት ትንሽ ቦታ እና የጸበሉ አካባቢ ብቻ ነበር፡፡ መነኮሳቱም የሚኖሩት በቁሪት ነበር፡፡ “ቁሪት” ማለት ሁሉም ለየራሱ ዋሻ ዘግቶ የሚጸልይበት የግል ጸሎት እና ሱባኤ የሚከናወንበት ስርዓት እንደሆነ ባህታዊ ወልደማርያም ነግረውኛል፡፡ ከዛ በኋላ ግን ለአካባቢው ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን ከሩቅ ለሚመጡትም ጸበልተኞች ቅድስት ድንግል ማርያም በጸበሏ የምታደርገው ተዓምር ገዳሙ ገናን እንዲሆን አድርጓል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚመጣው ሰው ቁጥር ከፍተኛ ለውጥ እያሳየ ነው፡፡ አብዛኞቹ መኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ሱቆችም በከተማው የተሰሩት ከገዳሚ መግነን ጋር ተያይዞ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትንቢቱ እየተፈጸመ እንዳለ እና ታቦቷ ስትገለጥ ደግሞ የምንጠብቀው ነገር እንደሚሆን የሚያሳይ ነው በማለት የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲያምኑ አድርጓል፡፡

እንደዚህ አይነት ተረኮች መኖራቸው ገዳሙ እየሰፋ በሚሄድበት ጊዜ የአካባቢው ነዋሪዎች መሬታቸውን ያለማንገራገር እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በገዳሙ ማደግ እና በቤተ ክርስቲያኗ መሰራት አካባቢያችን ያድግልናል የሚል እምነት ስለሚያሳድርባቸው የገዳሙ ጠባቂ እና ተቆርቋሪ የአካባቢው ነዋሪዎች እንዲሆኑ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡ የሚነገሩት ትንቢቶች እየተፈጸሙ ያሉ ስለሆነ፣ የአካባቢው ነዋሪዎች የመለወጥ ተስፋቸው ይለመልማል፡፡ በገዳም ውስጥ ያሉ መነኮሳት ከአካባቢው ጋር ያላቸው ግንኙነት ሰላማዊ እና የተደገፈ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ በኃይማኖት ደረጃም ወደፊት የሚሆነውን ቀድሞ ያሳወቃቸውን አምላክ እያመሰገኑ በእምነታቸው ፀንተው፣ በጾምና በጸሎት ይተጉ ዘንድ የትንቢታዊ ተረኮቹ ሚና ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በአሁን ጊዜ ገዳሙ ተስፋፍቶ በርካታ ልማቶችን እንዲያከናውን፣ የወንዶችና የሴቶችን ማረፊያ በሰፊው እንዲያዘጋጅ፣ ከሩቅ የሚመጡትን ምዕመናን በአግባቡ ተስተናግደው ወደ መጡበት መመለስ እንዲችሉ፣ ወዘተ. ለታዩት አዎንታዊ ለውጦች ሁሉ ትንቢታዊ ተረኮቹ ያላቸው ፋይዳ የማይናቅ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከአካባቢው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክተው ከተለያዩ ቦታዎች ወደ ምስካበ ቅዱሳን ጻድቃኔ ማርያም ገዳም የሚመጣው ሰው በአመት 300 ሺህ እስከ 400 ሺህ ይደርሳል፡፡ ከአስር አመታት በፊት በጥቂት የአካባቢው ሰዎችና የኃይማኖት አባቶች ብቻ ያውቁት የነበረ ገዳም በአሁን ጊዜ ከፍተኛ ለውጥ ማሳየቱ ትንቢታዊ ተረኮቹ እየተፈፀሙ ናቸው ለማለት ያስደፍራል፡፡

## 4.4. መንግስትና ኃይማኖት

በአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ[3] የክርስትና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላ ኢትዮጵያና ቤተ ክርስቲያን የማይነጣጠሉ ናቸው ፡፡ የነገስታት ኃይማኖት የሀገሪቱ ብሔራዊ ኃይማኖት ስለሚሆን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና ከኢትዮጵያ ነገስታት ጋር የጠበቀ ትስስር እንደነበራት የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ (ጎኑይ፣ 1999፣ 4፣ ጋስፓሪኒ፣ 1952፣ 122)፡፡

ከተለያዩ ገድላት፣ የታሪክ መዛግብት እና የነገስታት ውሎን በሚያትቱ ዜና መዋዕሎች መረዳት የሚቻለው ነገስታት ኃይማኖታቸውን በጦርነት አስፋፍተዋል፡፡ የተለያዩ ግዛቶችን በመውረር አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጸዋል፡፡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

---

[3] ...አስቀድሞ እንደተገለጸው ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን እምነትና ስርዓት ባለቤት ስለነበረች ይህ ኢትዮጵያዊ (የንግስት ሕንደኬ ጃንደረባ) የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም እንደሄደ መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል(ሐዋ. 8÷26-40)፡፡ ኢየሩሳሌም ሄዶ በዓል አክብሮ ሲመለስ የነብዩ ኢሳያስን መጽሐፍ ሲያነብ(ኢሳ. 53) እግዚአብሔር ቅዱስ ፊሊጶስን ልኮለትየክርስትናን ትምህርት ከተረዳና ከተጠመቀ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሷል፡፡ ከዚህ በኋላ ጃንደረባው ይህን የክርስትና እምነት በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲጀመር በማድረጉ ምክንያት ግምባር ቀደም ሐዋርያ ነው፡፡ ይህ የንግስት ሕንደኬ ባለሟል ያደረገው አስተዋፅኦ ታላቅ ስለነበር የክርስትና ኃይማኖት ወደ አገራችን የገባው ከጌታ ልደት በኋላ በ34 ዓ.ም. ፊሊጶስ ባጠመቀው ጃንደረባ መሆኑን እንረዳለን(መንግስቱና አሳምነው፣ 2000፣ 51-52)፡፡

የክርስትና ኃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በ34 ዓ.ም. በጃንደረባው አማካኝነት ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን በሲኖዶስ ህግ የኤጲስ ቆጶስ መንበር የተሰጣትና ምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን መፈጸም የተጀመረው በአራተኛው መቶ ክ/ዘመን ከ4ኛው የእስክንድርያ ፓትርያርክ በቅዱስ አትናቴዎስ በተሾመው በቅዱስ ፍሬምናጦስ ነው(መንግስቱና አሳምነው፣ 2000፣ 55)፡፡

ቤተ ክርስቲያን ካህናት መካከል የሀሳብ ልዩነት ሲነሳ ልዩነቱን ለማስቀረት አወያይተዋል፡ ፡ አከራክረዋል፡፡ በክርክሩ አሸናፊ የሆነው ቡድን ተቀባይነት እንዲኖረው ሲያውጁ፤ ተሸነፈ ብለው ያሰቡትን ቡድን አባላት አስረዋል፡፡ አስገድለዋል፡፡ (Taddesse, 1972፤ ፍስሐ፣ 2003)፡፡ እነዚህ ተግባራት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ኃይማኖትና መንግስት የነበራቸውን የጠበቀ ግንኙነት ወይም ሀገርን በጋራ የማስተዳደር ኃይል ያሳያሉ፡፡

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ውስጥ ከአመሰራረት ጀምሮ ወደፊት ይሆናሉ ተብለው የሚነገሩት ተረኮች የመንግስትና የኃይማኖትን ትስስር የሚያሳዩ ናቸው፡ ፡እንደ ተረኮቹ በታቦቱ ስደት፣ በደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን ምስረታ እና የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም መቆርቆርን በሚያትቱ ተረኮች ውስጥ የንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ በገዳሙ ማኅበረሰቦች ዘንድ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ከንግስናው(አገርን ከማስተዳደሩ) የበለጠ ገኖ የሚታመነው ኃይማኖታዊ እና ጻድቅ መሆኑ ነው፡፡ ከግብጽ ደብረ ምጥማቅ የመጣውን ታቦት እና ነዋየ ቅድሳት ተረክቦ ታቦቱ እንዲያርፍ የተፈቀደለትን ቦታ እስኪያገኝ አብሮ ሲጓዝ የነበረው ንጉሱ ዘርዐ ያዕቆብ ነው፡፡ በሚያርፉበት ቦታ ሁሉ ቅድስት ድንግል ማርያም በራዕይ እየተገለጠች መልዕክት ታስተላልፍ የነበረው ለንጉሱ ዘርዐ ያዕቆብ ነው፡፡ በእግዚአብሔር እርዳታ ባህሩን ወደ ውስጥ አስጥሟል ተብሎ የሚታመነው ዘርዐ ያዕቆብ ነው፡፡ በማኅበረሰቡ ተረክ ዘርዐ ያዕቆብ ጻድቅ እና ከእግዚአብሔር የተቀባ ንጉስ ነው፡፡ ደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያንን ከመሰረተ በኋላ እንደ አለማዊ ንጉስ በፈረስ ሰረገላ እና በበቅሎ ሳይሆን በነፋስ አውታር እና በደመና ሰረገላ ከኢየሩሳሌም ደብረ ምጥማቅ የሚመላለስ፤ እንደ ነገስታት በግብር እና በጦርነት ሳይሆን ሙሉ ሰውነቱ እስኪያብጥ በፆምና በፀሎት የሚተጋ ንጉስ ነበር፡፡ ለዚህ ተጋድሎውም ቅድስት ድንግል ማርያም በዚህ ቦታ (በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም) ስሜ ሲጠራ ያንተም ስም አብሮ ይጠራል ብላ ቃል እንደገባችለትና ከዛ ጊዜ ጀምሮ "የዘርዐ ያዕቆብ እመቤት" እየተባለች እንደምትጠራ የእምነቱ ተከታዮች ይናገራሉ (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፤ ቃለ መጠይቅ፣ ቤተ ማርያም፣ 05/07/07፣ ቃለ መጠይቅ፣ እማሆይ እሴተ ማርያም፣ 06/07/07 ቃለ መጠይቅ)፡፡

ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ታቦቱን ይዞ በብዙ ወታደሮችና አገልጋዮች ታጅቦ የተጓዘው ጻድቅ ስለሆነ ሳይሆን ንጉስ ስለነበር ነው፡፡ ያኛው ቦታ ላይ ሰራዊቱን፣ ካህናቱን እና ታቦቱን ይዞ የሚቀመጠው እንደ ንጉስ እንጂ እነደ አማኝ ብቻ አይደለም፡፡ እንደ ማኅበረሰቡ ተረክ ስፍራው ሲመሰረት የነበሩት በርካታ አገልጋዮች በንጉሱ የተመደቡ ነበሩ፡፡ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያንን ከመሰረተ በኋላ የነበረው የገዳሙና የቤተ ክርስቲያኑ

ሰፊ ግዛት ከንጉሱ የተበረከተ ነበር፡፡ ስለዚህም ዘርዐ ያዕቆብ ከታቦቱ ስደት አንስቶ እስከ ገዳም ምስረታው ላከናወነው ተግባር ንግስናው ዋነኛ መጠቀሚያው ነበረ ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም ምክንያት መንግስትና ኃይማኖት የነበራቸውን ትስስር ከተረኮቹ መረዳት ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ከ1426 ዓ.ም እስከ 1460 ዓ.ም በንግስና ኢትዮጵያን ማስተዳደሩ ይታወቃል፡፡ ይህ ንጉስም ከ"ዓለም" ይልቅ ለኃይማኖት ተግባር ያደላ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ (ሥርግው፣ 1981፣ 161) ፡፡ ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ጣኦታት ያመልካሉ ያላቸውን ሰዎች ጨፍጭፏል፡፡ ቤተሰቦቹን እንኳን በጣኦት አምልኮ ውስጥ ቢያገኛቸው በአደባባይ እንዲሰቀሉ አድርጓል (ፍስሐ፣ 2003፣ 253)፡፡ ዘመናዊ አስተዳደር ስርዓትን ለመንግስትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተ ንጉስ ነው፡፡ ቅዳሜ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ሆና እንድትከበር ያወጀው እሱ ነው፡፡ ደብረ ምጥማቅ ላይም በ1442 ዓ.ም ትልቅ ኃይማኖታዊ ስብሰባ አድርጓል (Taddesse, 1972, 229-230)፡፡ የንጉስ ዘርዐ ያዕቆብን ማንነት እና ህይወት ከታሪክ መዛግብት ሲመሳከሩ ለኃይማኖት ቀናኢ መሆኑ እና አብያተ ክርስቲያናት ማሳነፁ፣ መጽሐፍት መጻፉ፣ ማስተርጎሙ፣ አምልኮተ ጣኦትን መዋጋቱ ከጻድቃኔ ማርያም ገዳም ማኅበረሰብ ተረክ ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡ ደብረ ምጥማቅን እሱ እንደመሰረተም ተክለ ጻድቅ መኩሪያ በመጽሐፋቸው አስፍረዋል (1966፡171)፡፡

የንጉስ ዘርዐ ያዕቆብን ማንነት በተረኮቹ እና በታሪክ መመርመር የእኔ ዋና ጉዳይ አይደለም፡፡ ገዳሙ በንጉሱ እንደተመሰረተ መነገሩ ለገዳሙ ማኅበረሰብ ምን ፋይዳ አለው የሚለውን መመርመር እንጂ፡፡ በሁሉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው "ተአምረ ማርያም" መጽሐፍ ላይ ይህ ንጉስ "ኢትዮጵያዊው ቆስጠንጢኖስ" (ተአምረ ማርያም፣ 10) በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ገዳም በኃይማኖቱ ቅዱስ በሚባል ንጉስ መመስረቱ መነገሩ ደግሞ የገዳሙን ታሪካዊ እና ኃይማኖታዊ ዋጋ ከፍ ያደርገዋል፡፡ የኃይማኖቱ ተከታዮች ለገዳሙ ከፍተኛ ክብር እንዲኖራቸው እና ወደ ገዳሙ መጥተው በረከትን እንደሚያገኙ ያላቸውን እምነት ይጨምራል፤ ያጸናል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ማኅበረሰቦች ገዳሙ ከነገስታት የነበረውን ግንኙነት እና በገዳሙ የነበሩ ቅዱሳን ለኢትዮጵያ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ የሚናገሩበት ተረክ አላቸው፡፡

> አጼ ምኒሊክ የአድዋ ጦርነት በተጋረጠባቸው ጊዜ በጸሎትህ አትርሳኝ፣ አስበኝ ብለው ወደ የኔታ ሶምሶን ቢልኩ፣ ሶምሶንም ለምኒሊክ የእመቤታችንን ጽላት፣ የጊዮርጊስን ጽላት ያዝና 7 (ሰባት) ቀን አስቀድስ፡፡ ከዛ በኋላ ወደ ጦሩ ጽላቶቹን ያዝና ሂድ ድል አድርገህ ትመለሳለህ ብለው እንደላኩባቸው ይነገራል… (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ከላይ የቀረበው ተረክ በጻድቃኔ ማርያም ገዳም ይኖሩ የነበሩ አባት ለኢትዮጵያ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ ማኅበረሰቦች ገዳማቸው ንጉስ የመሰረታት ብቻ ሳትሆን ለንጉሶችም የጠቀመች መሆኗን ይገልጻሉ፡፡ የአድዋ ጦርነት የአለም ጥቁሮች የሚኮሩበት፣ ነጮች ለመጀመሪያ ጊዜ በጥቁር ወታደር የተሸነፉበት ድል ነው፡፡ የአድዋ ድል የቆዳ ቀለምን መሰረት ያደረገ የበላይነት እና የበታችነት እንደሌለ የዓለም ህዝብ የተማረበት ክስተት ነው፡፡ የዓለማችንን የታሪክ ጉዞ የቀለበሰ፣ በዓለም ህዝብ የሚዘከር፣ የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት የዓለም ህዝብ ያወቀበት ድል ነው፡፡

በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ያሉ ማኅበረሰቦች በዚህ የጥቁር ህዝብ ሁሉ ድል በሆነው ታሪካዊ ጦርነት ውስጥ አሻራቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይተርካሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የእስራኤል ህዝቦች በአምላካቸው ትዕዛዝ ወደ ጦርነት ሲወጡ የእግዚአብሔርን ታቦት የተሸከመ ካህን አብሯቸው ይወጣ ነበር (1ሳሙ 4)፡፡ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ ነገስታትም ወደ ጦርነት ሲሄዱ ታቦት የተሸከሙ ካህናትን አስከትለው ይዘምቱ ነበር (ተክለ ፃድቅ፣1966፤ አበበ፣ 1991 )፡፡ ታቦት ይዘው መዋጋታቸውም እግዚአብሔር ከእነሱ ጋር እንደሆነና ድል እንደሚያደርጉ እንዲያምኑ አድርጓቸዋል፡፡

በአጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ሲመጣ ንጉሱ መልዕክት የላኩት በገዳሙ ለሚኖሩ አንድ ባህታዊ እንደሆነ ከተረኩ እንረዳለን፡፡ ባህታዊውም ለንጉሱ ስንት ቀን መጸለይ እንዳለባቸው፣ የማንን ጽላት ይዘው መጓዝ እንደሚገባቸው መልዕክት ልከዋል፡፡ የማርያምን እና የጊዮርጊስን ጽላት ይዘው ዝመቱ ብለው የማሸነፊያውን ቁልፍ ሰጥተው፤ ድል አድርገው እንደሚመለሱ አመልክተዋቸዋል፡፡ ንጉሱም በተባሉት መሰረት ጽላት ይዘው እንደዘመቱ እና ድል አድርገው እንደተመለሱ የገዳሙ ሰዎች ይናገራሉ፡፡ አጼ ምኒሊክ ወደ አድዋ ጦርነት ሲጓዙ የማርያምን ታቦት መያዛቸውን የታሪክ አጥኚዎች አስፍረዋል፡፡ "ንጉሱ ወደጦርነቱ ሲደርሱ አቡነ ማትያስና የማርያምን ታቦት የያዙት ካህናት በኋላቸው ነበሩ፡፡ እቴጌ ጣይቱም ከዘበኞቻቸውና ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሆነው በአቡነ ማቴዎስና በታቦቷ ጎን ነበሩ" (አበበ፣ 1991፣ 112)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ጦርነቱ እስኪጀመር ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ገብተው ጸሎት ያደረጉ እንደነበር እንደሚከተለው ሰፍሯል፡፡ "ጦርነቱ ተጀምሮ የመጀመሪያው ጥይት በሚሰማበት

ጊዜ አፄ ምኒሊክ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው ልባዊ የሆነ ጸሎታቸውን በማድረግ ለጦራቸው ድልን ተመኝተዋል" (አበበ፣ 1991፣ 118)፡፡ በዚህ መሰረት ንጉሱ የማርያምን እና የጊዮርጊስን ጽላት ይዘው መዝመታቸው ከማኅበረሰቡ ተረክ ጋር ይዛመዳል፡፡

ታቦታቱን ይዘው በመዝመታቸው ጦርነቱ ላይ የቅዱስ ጊዮርጊስ ተሳትፎ እንደነበር የጣሊያን ምርኮኞች መመስከራቸውን አለቃ ተክለ ኢየሱስ እንደሚከተለው አስፍረውታል::

> የኢጣሊያ ጦርነት ዕለት ቅዱስ ጊዮርጊስ በገሀድ ተራዳ፡፡ የኢጣሊያን ጦር በሰይፍ ሲቀጣው ዋለ፡፡ ይሄውም ነገር ሀሰት እንዳይባል ኢጣሊያኖች ሁሉ የደም ሽማ አስሮ የሚፈክረውን ቢያዩ ከጦርነቱ ላይ ያዩትን የመሰለ ፈረሱ ከፈረሱ፣ ልብሱ ከልብሱ፣ መልኩ ከመልኩ የሚተባበረው ጀግና አጡ፡፡ ስለዚህ ምክንያት ባላምባላይ ፈረስ የጫነ፣ ፈረሰኞች ያስከተለ፣ ሰይፍ አመታቱ እንደሚካኤል፣ ፈረሱ አነሳሱ እንደ አውሎ ነፋስ የሆነ፣ የንጉስ ልጅ የመሰለ መኮንን ነው ሲፈጀን ውሎ አሁን ከሚፈክረው ሁሉ እሱን የመሰለ አጣን አሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ መሆኑ ተገለጠ (ስርግው፣ 2002፣ 192)፡፡

የአድዋ ጦርነት መለኮታዊ ተራድኦ እንደነበረው ከዚህ ጽሁፍ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ መለኮታዊ ተራድኦ እንዲኖር ደግሞ በጻድቃኔ ማርያም ገዳም የነበሩት ባህታዊ ሶምሶን ትልቅ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው የማኅበረሰቡ ተረክ ያስረዳል፡፡ የጊዮርጊስ እና የማርያም ታቦት መያዝ እንዳለበት ነግረዋል፡፡ ንጉሱ ጸሎት ማድረግ እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡ ድል አድርገው እንደሚመለሱም አሳውቀዋል፡፡ እዚህ ጋር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በፈጣሪ እና በእርሱ በርካታ አገልጋዮች (ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ መላእክት፣ ሐዋርያት) ስም ከተሰየሙ ታቦታት መካከል የቅድስት ድንግል ማርያም ታቦት እና የጊዮርጊስ ታቦት ለምን ተመረጡ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለኛል፡ ፡ የቅድስት ድንግል ማርያም ታቦት ሊመረጥ የቻለው በቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ጋር ወደ ኢትዮጵያ በመጣች ጊዜ ኢትዮጵያን የአስራት ሀገር አድርጎ ሰጥቷታል (ድርሳነ ዑራኤል ዘኅዳር፣ 1991፣ 26-28) የሚል እምነት ስላለ ሊሆን ይችላል፡፡ ቅዱስ ጊዮርጊስም በምድር እያለ ጦረኛ እንደነበር በገድሉ ላይ መጻፉ የእሱም ታቦት እንዲመረጥ ያስቻለ ይመስለኛል፡፡

እነዚህ የገዳሙ ማኅበረሰቦች በአድዋ ድል ላይ የማሸነፊያው ቁልፍ ከእነሱ ቅዱስ ስፍራ እንደተሰጠ ያምናሉ፡፡ ንጉስ ምንሊክም "ምን ላድርግ" ብለው ወደ ቦታው መልዕክት መላካቸው ሀገራዊ እና መንግስታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የኃይማኖት አባቶች ሚና ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ በገዳሙ አካባቢ ለሚገኙ ማኅበረሰቦችም ያለው ስነ ልቡናዊ እርካታ

ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዛሬም ቢሆን መንግስት ለሚገጥመው ችግር መፍትሄ ካሻው ወደዚህ ይምጣ የሚል መንፈስ ያዘለ ይመስላል፡፡

በገዳሙ ያሉ ማኅበረሰቦች ከዚህ በተጨማሪ ከአፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በጾመ ሁዳዴ እና በወርሃ ጳጉሜ የሚቀደሰው ቅዳሴ እና የሚጸለየው ጸሎት ስለመንግስት እና ስለሀገር መሆኑን ይናገራሉ (ደስታ ገብረ ወልድ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

ይህም እስከአሁን ድረስ በቦታው መንግስት በጸሎት መታሰቡ፣ መንግስትም በሚችለው ሁሉ ኃይማኖቱን ማሰብ እንዳለበት ለማስገንዘብ ይመስላል፡፡ በተረኩ በኃይማኖቱ ውስጥ ስለመንግስት ጸሎት እንደሚደረግ መነገሩ የመንግስት ህልውና በእነሱ ጸሎት ጭምር እንደሆነ እንደሚታሰብ ያሳያል፡፡ ይህም ኃይማኖቱ ከመንግስት ማግኘት የሚገባውን ጥቅም እንድታገኝ አስተዋጽኦ ያበረክታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው በገዳሙ ማኅበረሰቦች ከሚነገሩት ተረኮች ውስጥ የመንግስትን እና የኃይማኖትን ጥምረት የሚያሳየው ወደፊት ይመጣል ብለው የሚያምኑት መንግስት ነው፡፡ ደስታ ገብረ ወልድ ትንቢታዊ ተረኩን "እግዚአብሔር የፈቀደ ጊዜ ህጻን መንግስት ይመጣል፡፡ መቀመጫውንም እዚህ ያደርጋል፡፡ በመላው ህዝብም ፍቅረ ሰላም ይወርዳል፡፡ እና ጽላቷም በነበረችበት ቦታ ትቀመጣለች" (08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ) በማለት ነግረውኛል፡፡

ከዚህ ተረክ መረዳት የሚቻለው ወደፊት የሚመጣ ደግ መንግስት አለ ብለው የሚያምኑ መሆናቸውን ነው፡፡ መንግስቱን ሲገልጹም "ህጻን መንግስት" ይሉታል፡፡ ህጻን በክርስትና ኃይማኖት ውስጥ መልካምነትን፣ ንጽህናን፣ ጻድቅነትን ወዘተ. ይወክላል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ ተናግሯል፡፡ "እውነት እውነት እላችኋለሁ የእግዚአብሔርን መንግስት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ አይገባባትም" (ማር 8÷15)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ትንቢታዊ ተረኩ በፍካሬ ኢየሱስ መጽሐፍ ከሰፈረው ትንቢት ጋር ይመሳሰላል፡፡

> …ከዚህ በኋላ ከምስራቅ በኩል ታሪካዊና ደገኛ የሆነ ንጉስ ይነሳል፡፡ እሱም ፈቃዴን የፈጸሙትን፣ ከመከራ ያተረፍኳቸውን የሚሰበስብ ነው፡፡ ጳጳስም ይወጣል፡፡ ምድርን የሚባርክ ሰውን ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡ አብያተ ክርስቲያናት ይታደሳሉ፡፡ በዚያ ዘመን መቅሰፍት የለም፣ ምህረት በረከት ይበዛል.. (1991፣ 59)፡፡

በፍካሬ ኢየሱስ መጽሐፍ የተጻፈው ትንቢትና በገዳሙ የሚነገረው ተረክ ወደፊት መልካም ንጉስና ደግ ጳጳስ መሾም ላይ ይመሳሰላሉ፡፡ በማኅበረሰቡ የሚነገረው ተረክ ግን

የመንግስቱን መነሳት እና የጳጳሱን መሾም በገዳሙ ውስጥ ተሰውሮ ከሚገኘው ስውር ታቦት መገለጥ ጋር ያያይዙታል፡፡ ከፍካሬ ኢየሱስ ትንቢት ጋር መመሳሰሉ በአማኞቹ ዘንድ ቅቡል እንዲሆን የማድረግ ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል፡፡

እንደ ክርስትና አስተምህሮ መንግስተ ሰማያት የሚወረሰው በጽድቅ ስራ ነው፡፡ ህፃን ንጉስ ይነሳል ማለታቸውም ለህዝቡ እና ለአገሩ የሚቆረቆር፣ በመልካም ምግባር የተሞላ፣ እግዚአብሔር የሚወደውን ስራ የሚሰራ፣ መሪ ይመጣል ማለታቸው ይሆናል፡፡ ይህ ህጻን መንግስት ሲመጣ ደግሞ ሰላ ዲንጋይ የሚቀመጥባት፣ ደብረ ምጥማቅ ማርያም የሚያስቀድስባት ቦታ እንደምትሆን ያምናሉ፡፡ ይህንንም በተረክ ሲገልፁ "...በዚያን ጊዜ ጳጳስና መነኩሴ ብቻ ይቀድስባታል፡፡ መንግስትም ቆሞ ያስቀድስባታል..." (እቴነሽ ነገደ ወርቅ፣ 07/07/07፣ ቃለ መጠይቅ) ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ እንደ ማኅበረሰቡ ተረክ ጻድቃኔ ማርያም ገዳምን የመሰረታት ንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ነው፡፡ ይህም ንጉስ በደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያንና በጻድቃኔ ዋሻ ውስጥ እየተመላለሰ ለአገርና ለወገን ይጸልይ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላም ነገስታት ችግር ሲገጥማቸው መፍትሄ ፍለጋ በቦታው ለሚኖሩ አባቶች መልዕክት ልከዋል፡፡ ለችግራቸውም መፍትሄ አግኝተዋል፡፡ ወደፊትም ከታቦቱ መገለጥ ጋር ተያይዞ መልካም ንጉስ ይነሳል፡፡ ይህም ንጉስ መቀመጫውን ሰላ ድንጋይ ያደርጋል፡፡ ብዙ ጊዜውን በደብረ ምጥማቅ የሚጸልይና የሚያስቀድስ ይሆናል፡፡

እነዚህ ማኅበረሰቦች ያለፈ ታሪካቸው ከነገስታት ያልተለየ እንደነበር ይተርካሉ፡፡ ወደፊትም ለኢትዮጵያ የሚነሳው መልካም መሪ ህይወቱ ከታቦቱ መገለጥ ጋር እንደሆነ ይተነብያሉ፡፡ ያምናሉም፡፡ የንጉሱ መቀመጫም ሰላድንጋይ እንደምትሆን ይጠብቃሉ፡፡ በተረኮቻቸው የገዳሙን እና የቤተ ክርስቲያኑን ለአገር አስፈላጊ መሆን ይነግሩበታል፡፡ የጥሩ ነገር መነሻ እነሱ ጋር ያለው ቅዱስ ታቦት መሆኑን ያሳውቁበታል፡፡ ይህም የገዳሙን እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ በራስ መተማመን በመገንባት የተረጋጋ ስነ ልቡና እንዲኖራቸው በማድረግ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስፍራውን እንዲንከባከቡና እንዲያከብሩ፣ የገዳሙን ህግጋት እንዲፈፅሙ፣ ከመንግስት የሚፈልጉትን ነገር በቀላሉ እንደሚያገኙ እንዲያምኑ የማድረግ ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብም ገዳሙ ለህልውናቸው እና ለእድገታቸው አስፈላጊ መሆኑን እንዲያምኑ እና የገዳሙ ጠባቂ እንዲሆኑ የሚያስችል ይመስለኛል፡፡

## 4.5. ፈውስ

ፈውስ ማለት አንድ አካላዊ ወይም ስነ ልቡናዊ ችግር ያለበት ግለሰብ ለአካላዊም ሆነ ለስነ ልቡናዊ ችግሩ በእምነት የሚያገኘው መፍትሄ (ድህነት) ነው፡፡ በጻጽ ቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም በቦታው ተገኝተው ስለተፈወሱ ሰዎች ይተረካል፡፡ ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገራት በበሽታ የተጠቁ ሰዎች ወደ ጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም ፈውስ ፍለጋ ይመጣሉ፡፡ ፈልገው፣ አምነው የመጡትም የገዳሙን ስርዓት ጠብቀው በጸበል ተጠምቀው፣ እምነት ተቀብተው፣ ጸመው እና ጸልየው እየተፈወሱ እንደሚሄዱ የገዳሙ አባቶች ይናገራሉ፡፡ ደስታ ተክለ ወልድ እንደነገሩኝ እሳቸው ገዳም ውስጥ በሚያገለግሉበት ጊዜ ብዙ ሰዎች እየመጡ መፈወሣቸውን ይነግሯቸው ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች በገዳሙ ጸበል ተጠምቀው ከእርኩስ መንፈስ (የደብተራ እና የደረሣ መተት፣ ቡዳ፣ ልክፍት፣ ወዘተ.) ይድናሉ፡፡ ዘመናዊ ህክምና መድኃኒት ያላገኘላቸው፣ አይድኑም ተብለው በዓለም ተስፋ የተቆረጠባቸው በሽታዎች ሁሉ በገዳሙ ጸበል ፈውስ እንደሚያገኙ ይነገራል፡፡

> እዛ አገልጋይ እያለሁ አንዲት ወጣት መጣች፡፡ እያለቀሰች ታሪኳን ነገረችኝ፡፡ እንዲህ ስትል፡፡… ተወልጄ ያደኩት ደብረ ብርሃን ነው፡፡ ለስራ ብዬ አዲስ አበባ ሄጄ ፣ ሰው ቤት ተቀጥሬ እየሰራሁ እያለሁ ወንድየው ስራ ቦታ ሄድኩ ይልና ረፈድ ሲል መጥቶ ይደፍረኛል፡፡ እንቢ ብዬ አልሄድ ሌላ ዘመድ አላውቅም፡፡ በተደጋጋሚ እየመጣ ሲደፍረኝ ከርሟል፡፡ ከዚህ በኋላ ሰውየው በሽተኛ ኖሮ ኤች አ ይ ቪ ያዘኝ፡፡ ታመምኩ ብዬ ብለው እዚህ ቦታ እንዳላይሽ ጥፊ አለኝ፡፡ ተመልሼ መጥቼ ደብረ ብርሃን ቤተሰቦቼ ጋር ስገባ እናቴ ሞታ አባቴ ሌላ ሴት አግብቶ ነበር፡፡ አሁን ያቺ እንጀራ እናቴ ወልዳለች፡፡… ልጆቹን ልትፈጂ ነው ! በይ ጥፊ ከዚህ ቦታ ብላ ተቆጣችኝ፡፡ አባቴ እንደመጣ እንዲህ ብላለች ልጅህ ስትለው እህል ውሃ ሳይሰጡኝ ጥፊ ከዚህ ብለው አባረሩኝ፡፡ ጨልሞ ስለነበር ከብቶች በረት አድሬ ሲነጋ አበረሩኝ፡፡" ብላ እዚህ ገዳም መጥታ ነገረችኝ፡፡ …. አይ እንግዲህ ለእመቤታችን ንገሪያት፤ ለእሷ የሚሳናት ነገር የለም ትድኛለሽ ብዬ አጽናናኋት፡፡… በኋላ ስትጠመቅ ቆይታ፣ ተመልሣ እኔ ጋር መጥታ ሰላ ደንጋይ ሄጄ ተመረመርኩ ነፃ ነኝ፡፡ ደብረብርሃን ሄጄ ተመረመርኩ ነፃ ነኝ ፡፡… እመቤቴ ፈውሣኛለች ብላ በእንባ ተሞልታ ነገረችኝ፡፡… (ደስታ ተክለ ወልድ ፣ 08/07/07፣ ቃለ መጠይቅ)፡፡

እንደ ተረኩ ልጅቱ ተስፋ ስትቆርጥ እና ማረፊያ ስታጣ ወደ ገዳሙ መጣች፡፡ ሰው ተስፋ ሲቆርጥ ያለውን አማራጭ ይጠቀማል፡፡ ይህቺ ሴትም አማራጭ አድርጋ ወደ ጻድቃኔ ማርያም ገዳም መጥታ ጸበል በመጠመቋ ዓለም አይድንም ካላት በሽታ ተፈውሳለች፡፡ ይህ ተረክ መተረኩም ቦታው የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጥበት፣ ፈውስ የሚገኝበት ቦታ መሆኑን ለሌላው ያስተምራል፡፡ በዚህ ጸበል ፈውስ ያገኙ ግለሰቦች በሂዱበት ስለተደረገላቸው እና ስላዩት ይናገራሉ፡፡ ይህም የገዳሙን እውቅና በመጨመር መልኩ

የራሱ ድርሻ አለው፡፡ በጻድቃኔ ማርያም ጸበል እና እምነት ሙሉ ሰውነቷ በቁስል የተመታ ልጅ መፈወሷን እንደሚያውቅ እና የሂደቱ ተሳታፊ እንደነበረ አንዱዓለም አባተ እንደሚከተለው ተርኮልኛል፡፡

> አሁን የማወራው ታሪክ የተፈጸመው 1986 ዓ.ም. ላይ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ደብረ ብርሀን ሥላሴ ሰንበት ትምህርት ቤት አገለግል ነበር፡፡ …ከእኛ ጋር የምታገለግል አንድ እህታችን ነበረች፤ እህቷ በጣም ትታመማለች፡፡ ብዙ ቦታዎች ህክምና አድርጋለች፡፡ ሙሉ ሰውነቷ ቆስሎ እንደመፈነዳዳት ብሏል፡፡ … ቤተሰቦቿ ያላቸው ሀሳብ አዋቂ ጋር መሄድ እንዳለባት ነው፡፡ እንደውም ምንድነው? እዛ ወስደዋት የሚታኘክ ነገር አኝኮ እንትፍ፣ እንትፍ ቢልባት (ቢተፉባት) ሊያድናት ይችላል የሚል እምነት ነበራቸው፡፡ የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዋ ደግሞ ይህንን ልትቀበለው አልቻለችም፡፡ በወቅቱ ይህንን ጭንቀቷን ለእኔ ታዋየኛለች፡፡ … በወቅቱ የተወሰንን ልጆች በሳምንት ሶስት ጊዜ የምህላ ጸሎት እናደርግ ነበር፡፡ አቡነ አፍሬምም ይገኙ ነበር፡፡ ልጅቱ ይህንን ሀሳብ ከነገረችኝ በኋላ ጸሎት ማድረግ እንዳለብን ነገርናት፡፡ … ከዚያ በኋላ እኔ፣ እሷ እና አንድ ጓደኛችን እጣ ስናወጣ ጻድቃኔ ማርያም ወጣ፡፡ ቀን ቀጠርን፤ በሳምንቱ ለመሄድ፡፡ በወቅቱ ለዚህ መነሻ የሆነን አንዲት አገልጋይ በቁስል ተመትታ በአባቶች ጸሎት ፈውስ እንዳገኘች ስለምናውቅ ነው፡፡ ቀኑ ሲደርስ ታማሚዋን ልጅ ይዘን መሄድ አንችልም ነበር፡፡ ስለዚህ እኛ ሶስታችን ወደጻድቃኔ ማርያም ሄድን፡፡ … ስንጓዝ ቆይተን አመሻሽ ላይ ጻድቃኔ ደረስን፡፡ ጉዳያችንን ለአባቶች አስረድተን አንዲት ዋሻ ውስት ሱባኤ ገባን፡፡ ከዛ በኋላ የሆነው ነገር ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት ነበር፡፡ ምንም ምልክት ሳናገኝ ሰባት ቀናችንን ጨረስን፡፡ ደስ የሚል የሱባኤ ጊዜ ነበረ፡፡ ከዚያም ጸበል እና እምነት ይዘን ወደ ደብረብርሀን ተመለስን፡፡ ከተመለስን በኋላ ያመጣነውን እምነትና ጸበል ልጅቱ ሙሉ ሰውነቷን እንድትቀባው ሆነ፡፡ የቀባናት እኔና እህቷ ነን፡፡… በመጀመሪያ ቀን በጣም ተሰቃየች፤ እየበላት(እያሳከካት) ማለት ነው፡፡ ቀስ በቀስ ግን እየለቀቃት ሄዶ በሳምንት ውስጥ ሙሉ ጤነኛ ሆነች፡፡ ይህ እኔ በአይኔ ያየሁት፣ የማውቀው ነው እንግዲህ… (አንዱዓለም አባተ፣ 12/08/08፣ ቃለመጠየቅ)፡፡

ከላይ በተረኩ ውስጥ ያለችው ሴት ደግሞ አማራጭ አጥታ ወደ ገዳሙ አልሄደችም፡፡ ይልቅስ በእሷ ስቃይ የተሰቃየችው እህቷ ተራኪውን (አንዱዓለምን) አማክራ እጣ ሲያወጡ ጻድቃኔ ማርያም ወጣ፡፡ በሽተኛዋ በአካል ሳትገኝ እህቷ፣ አንዱዓለም እና አንድ ጓደኛቸው ወደ ገዳሙ ሄደው ሱባኤ ያዙ፡፡ ጾሙ፤ ጸለዩ ምንም አይነት ራዕይ ወይም ምልክት ባያዩም ጸበል እና እምነት ይዘው መጥተው በቁስል የተመታውን አካሏን ቀቧት፡፡ ቁስሉም ረገፈ፤ ተፈወሰች፡፡ በበሽተኛዋ እምነት ሣይሆን በሌሎች እምነት እርሷ ከህመሟ ተላቀቀች፡፡ ገዳሙ ቅጥር ዘልቃ ሣይሆን ከገዳሙ ብዙ ርቀት ተጉዞ በመጣ እምነትና ጸበል ፈውስ አገኘች፡፡ ይህ ተረክ መተረኩ ወደ ገዳሙ የሚሄዱ ሰዎች ሌሎች ዘመዶቻቸውን፣ በሽታኞችን አስበው ቢጸልዩ እና እምነት ወይም ጸበል ወስደው ቢያስጠምቋቸው ፈዋሽ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በራስ እምነት ብቻ ሣይሆን በሰዎች እምነትና ጸሎት ፈውስ እንደሚገኝም ያሳያል ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ ያየናቸው ፍውስ ሰዎች አንዱ የምትሄድበት ስታጣ በጭንቅ ወደ ገዳሙ ሄዳ ፈውስ ያገኘች ስትሆን ሁለተኛዋ ደግሞ ገዳሙ ውስጥ ሳትሄድ በእህቷና በጓደኞቿ እምነትና ጸበል መጥቶላት የተፈወሰች ነች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች ተአምርን በመስማታቸው ተስበው መጥተው ከሚሰቃዩበት ህመም እንደተፈወሱ የሚያስረዳ ተረክ በገዳሙ መፅሄት ላይ ሰፍሯል፡፡

ከተረኩ መረዳት እንደሚቻለው በሌላ ቦታ እየተጠመቀ እያለ ተዓምሯን ሰምቶ ወደ ጻድቃኔ ማርያም መጥቷል፡፡ ረዥም ጊዜ ከቆየ በኋላ ተስፋ ቆርጦ ወደ ሌላ ቦታ ሊሄድ ሲል በመለኮታዊ ጥሪ (በስውር ኃይል ስበት) ተመልሶ መጥቶ ከህመሙ ተፈውሶ ምስክርነት ስጥቷል፡፡ ለቀናት በትእግስት ጸበል ሲጠመቅና ሲጠጣ ከቆየ በኋላ የመጨረሻውን ቀን ሂደት እንደሚከተለው ተርኮታል፡፡

> …ነሐሴ የፍስለታ ጾም ጨርሰን ነሐሴ 21 ቀን ጸሎት አድርገን ተጠምቄ መጣሁኝና አራት ሊትር ያክል ጸበል ጠጣሁኝ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ሰውነቴ ተጨነቀ፤ በጣም አመመኝ ፡፡ ወደታች ወደታች አለኝ ፡፡ ሽንት ቤት ለመድረስ ግዜ አልሰጠኝም እንደ ማስቀመጥ አድርጎ ወድያው ትልቅ እባብ በተቅማጥ መልክ ወጣልኝ ፡፡ ሲወጣ ሕመም ነበረውና ምንድነው የወጣው ብዬ ሳየው ትልቅ እባብ ነው፡፡ በደስታ ብዛት እልል አልኩኝ አለቀስኩኝ፡፡ ከአስር ዓመት በላይ ያስጨነቀኝ መርዝ የሰይጣን ተንኮል ተወገደልኝ፡፡ ይህንን ሁሉ ዓመት ተሸክሜው ስኖር ያስቻለኝን አምላክ አመሰገንኩት፡፡ እባብ ከውስጤ እንደወጣ ብዙም አልቆየም ወድያው ሞተ፡፡ የእመቤቴ ተአምር መገለጽ አለበት፤ ብዬ በላስቲክ አድርጌ ለአባቶች አሳየዋቸው በሜትር ሲለካ 26 ሳ.ሜ ይረዝማል፡፡ በኋላ እየሚሚ መጣ እንጂ ወፍራም ነበር፡፡ ጭንቅላት አለው፡፡ አፍ አለው፡፡ ይህንን ጉድ ነው እንግዲህ እመቤቴ የገላገለችኝ (የገዳሙ መጽሔት፣ 57)

የበሽታው ምንነት በውል ባይታወቅም ከተራኪው ሆድ ውስጥ ሁለት ጊዜ እባብ ወጥቶለታል፡፡ ለረጅም ጊዜ ሲሰቃይበት ከነበረ ህመሙ ተፈውሷል፡፡ ተረክ ሰምቶ ወደ ገዳሙ በመምጣቱም ተረኮች ገዳሙ እውቅና እንዲያገኝ ያላቸውን ፋይዳ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ መልኩ ለሁሉም ጊዜ አለው የሚለው ክርስቲያናዊ አስተምህሮ በተረኩ ውስጥ ይንጸባረቃል፡፡ ይህም በገዳሙ የመጡ ሁሉ ታግሰው በጾም፣ በጸሎት እና በጥምቀት መቆየት ቢችሉ ፈውስ ሳያገኙ አይመለሱም የሚል ሐሳብ ያዘለ ይመስላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ገዳም መጥተው ፈውስ የሚያገኙት የኢትዮትያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት ተከታዮች ብቻ አይደሉም፡፡ የሌሎች እምነት ተከታዮችም እየመጡ እንደሚፈወሱ ባህታዊ ወልደ ማርያም ነገረውኛል፡፡ ለዚህም አስረጅ ይሆነኝ ዘንድ ከተሰጡት የምስክርነት ተረኮች መካከል የሚከተለውን አነበቡልኝ፡፡

ስሜ ሀሊማ ሙህዲን ይባላል፡፡ እድሜዬ 18 ዓመት የመጣሁት ከደብረ ዘይት ከተማ ሲሆን የእስልምና እምነት ተከታይ ነኝ፡፡ ጻድቃኔ ማርያም ገዳም የመጣሁት ታምሜ ስለነበር ድህነትን ፈልጌ ነው፡፡

በህክምናው ዘርፍ ከሀገር ውስጥ እስከ ውጭ ሀገር ድረስ ታክሚያለሁ፡፡ ግን መዳን አልቻልኩም፡፡ እንደውም ሞቴን እጠብቅ ነበር፡፡ ማብቂያዬ ላይ ነው ጻድቃኔ ማርያም ገዳም የመጣሁት፡፡ የነበረኝ በሽታ የደም ካንሰር፣ የደም ግፊት ሲሆን በህመሜ ምክንያት በእግሬ መሄድ አልችልም ነበር፡፡ በተጨማሪም አጥንቴ ስስ ስለሆነ ኦፕራሲዮን ማድረግ እንደማይችሉ ተነገረኝ፡፡ ለደም ካንሰሩ በሽታ በየጊዜው የሌላ ሰው ደም ይቀየርልኝ ስለነበር የሚቀየረውም ደም ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በመሆኑ፤ ደም የማይቀየርልኝ እንደሆነም ተነግሮኝ ነበር፡፡ ደም ካልተቀየረ ደግሞ በህይወት የመቆየቴ ሁኔታ አስቸጋሪ ነበር፡፡

ህመሜ ሲጸና በሀገር ውስጥ በጥቁር አንበሣና ቤተ ዛታ ሆስፒታሎች ሕክምና ሲደረግልኝ ቆይቷል፡፡ ደም በተደጋጋሚ ተቀየረልኝ፡፡ አስፈላጊው እገዛ ተደርጎልኝ በመጨረሻ መዳን እንደማልችል ተነገረኝ፡፡ ለደም ካንሰሩ ከ5-6 ዓመት ቤተ ዛታ ሆስፒታል በየሁለት ወሩ የሌላ ሰው ደም ሲሰጠኝ ደግሞ ግራ አካሌ ላይ ኦፕራሲዮን ተደርጎ ስለነበር በጣም ያመኛል፡፡ እንደኔ የታመሙ ሰዎች አይቆዩም የሚሞቱት ስለሚበዙ እፈራ ነበር፡፡ በኋላ ደግሞ ይጥለኝ ጀመር፡፡ ሐኪሞቹም ከአምስት ዓመት በላይ የሌላ ሰው ደም አይሰጥም ስላሉ እኔም የሚሞቱትን ሳይና ስቃዬ ሲበዛ የትም ይሁን መሄድ እፈልግ ነበር" ውጭ ሀገር ሂጂና ታከሚ" ሲሉኝ እሺ አልኩኝ፡፡ ጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ሪፈር ጻፈልኝ፡፡

አባቴ በመጀመሪያ ወደ ካናዳ ይዞኝ ሄደ፡፡ ካናዳ መርምረውኝ የደም ካንሰር፣ የደም ግፊት እንዳለብኝና ኦፕራሲዮን ለማድረግ ደሜንም ለመቀየር አጥንቴ ሲያዮት ስስ ስለሆባቸው ኦፕራሲዮን ማድረግ መቻላቸውን ለማረጋገጥ መርፌ ወጉኝ በሶስተኛው ቀን እግሬ መንቀሣቀስ አቃተው፡፡ ጠነከረ፤ ደረቀ ፡፡ ሐኪሞቹም የሆነውን ብንነግራቸው ያለኝ አማራጭ በዊልቸር /የሚገፋ ወንበር/ መንቀሣቀስ ብቻ እንደሆነ ነገሩኝ፡፡ አባቴ ተስፋ ሣይቆርጥ ኩዌት የታወቀ ሐኪም እንዳለ ሲነገረው ኩዌት ይዞኝ ሄደ፡፡

ኩዌት እንደደረስኩኝ የደም ሴሎቼን ለማወቅ ኦፕራሲዮን ማድረግ መቻሉን ለማወቅ አጠቃላይ የሰውነቴን ሶስት ቀን ሙሉ ራጅ አልትራሣውንድ ውስጥ ቆየሁ መጨረሻ ላይ ሐኪሙ ከአቅሜ በላይ ነው ወደ ሀገሯ ትሂድ አለ፡፡

እኔም መዳን የማልችል ከሆነ ወደ ሀገሬ ልሂድ ብዬ መጣሁ፡፡ ሀገሬ ከመጣሁ በኋላ ህመሙ ሲያሰቃየኝ ትምህርቴን አቋርጫለሁ፤ ቤት መዋል ጀመርኩኝ፡፡ ጓደኞቼ ትምህርት ቤት ውለው እኔን ለመጠየቅ ሲመጡ እንደ ጓደኞቼ መንቀሣቀስና መማር ባለመቻሌ አዝኜ ፤ እቤት እያለሁ "የለችም" አስብል ነበር፡፡

ቤተሰቦቼ ከሀገር ቤት እስከ ውጭ ሀገር የሚቻለውን አድርገው እንዳልተሳካላቸው የምታውቅ በግቢያችን ተከራይታ የምትኖር አልማዝ የምትባል የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ "ጻድቃኔ ማርያም ገዳም ጸበል ትሂድ" ትላለች፡፡ በእምነቱ ውስጥ የሌለ ሰው ለመቀበል ይቸግረዋል፡፡ ለጊዜው ቤተሰቦቼ ምንም መልስ አልሰጡም፡፡ በኛ እምነት ጸበልን ዘምዘም ነው የምንለው፡፡ ባናምንበትም እንደሚያድን እናውቃለን፡፡

“እያየናት ከምትሞት“ ተብሎ ጸበል እንድሄድ ቤተሰቦቼ ፈቃደኛ ሆኑና ብዙ ቦታዎች በአማራጭነት ቀረቡ በመጨረሻ መንቀሣቀስ ስለማልችልና እንዳላስቸግርም ታስቦ “ሸንኮራ ትሂድ ጻድቃኔ ግን አይመቻትም” ተባለ፡፡

የምድንበት ቦታ ስለሆነ በግቢያችን ያለችው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ “ጻድቃኔ ከሆነ እኔ ይዣት እሄዳለሁ” አለች፡፡ የሚገርመው ግን አልማዝ ጻድቃኔ ማርያም ገዳምን የሰማችው በዝና ብቻ እንጂ ገዳሟን አታውቅም ነበር፡፡

አልማዝ ወንድሜም አለ ይዛን ጻድቃኔ ማርያም ገዳም መጣች፡፡ እንደደረስን እንደማንኛውም ክርስቲያን የጠዋት ጸሎት (ኪዳን)፣ (ሠርክ) እንሣተፋለን፡፡ ወንዶችም ሴቶችም ተባብረው ተሸክመው ሁሉም ቦታ ይወስዱኛል፡፡ የገዳሙ አባቶች ያበረታቱኛል እምነት እንድቀባ ጸበሉን እንድከታተል ይመክሩኛል ያጽናኑኛል ምህላ ሲደረግ ወንድሜ አስቀምጦኝ ስለማያምንበት ወደ ከተማ ይሄድ ነበር፡፡ እግሬ ደርቆ ምንም የማይሰማኝ ነበር፡፡ በምህላ ሰዓት በአምስተኛዉ ቀን ቀለል አለኝ፡፡ ወዲያው አውራጣቴ ተንቀሣቀሰ ከዛ ሰባት ቀን ሞልቼ ንጹህ ስላልነበርኩኝ ከቤትም ሲደወልልኝ ከ15 ቀናት በኋላ እንመለሳለን ብለን ተመልሰን ሄድን፡፡ ብዙ የተደነቀ የለም፡፡

በሰባተኛው ቀን ምህላ ሲደረግ የነበረው የእግሬ ጣቶች መንቀሣቀስ ጀመሩ ደነገጥኩኝ ምክንያቱም ከዓመት በላይ የማይንቀሳቀስ አካል ሲንቀሣቀስ ጸሎቱ ሲያልቅ ለሚሸከሙኝ ለነአልማዝ ነገርኳቸው ፡፡ የመጣሁት ለሰባት ቀን ስለነበርና ቤተሰቦቼም ስለደውሉ ተመልሰን ወደ ቤት ሄድን፡፡

ቤት ሄጄ የተደረገልኝን ለቤተሰቦቼ ነገርኳቸው መዳን እንዳለብኝ ቢፈልጉም ለውጤ ብዙም ስላልሆነ ብዙ የተደነቀም የለም፡፡ ከ15 ቀናት በኋላ እሄዳለሁ ብዬ ስዘጋጅ ተከለከልኩኝ፡፡

አልማዝ “መሄድ አለባት ለውጥ አላት ኤች አ ይ ቪ የያዛቸው ሰዎች፣ ዐይነ ስውር የሆኑ የተለያዩ በሽታዎች ያለባቸው ሰዎች እየዳኑ መሆኑን ተናገረች፡፡ ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ ህመሜ በጣም በረታ “ትሂድ” የሚለው ግፊት ሲበረታ ሂጂ አሉኝ፡፡ አባቴ ባይስማማም እሱ በሌለበት ቀን ወንድሜና እህቴ ሆነን ወደ ጻድቃኔ መጣን፡፡

ከቤቴ ስነሳ ያድነኛል ብዬ ነው የመጣሁት ፡፡ ሞት ወይም ድህነት ብዬ ነበር፡፡ እምነቱን እቀባለሁ ጸበሉን እጠመቃለሁ፡፡ ክርስቲያኖቹ “ አንድ ወር ሁለት ወር ቆየን” ሲሉ፣ እኔ ምነው የናንተ እጣ በደረሰኝ? እል ነበር፡፡ እውነታውን አውቄ በጸለይኩም እል ነበር፡፡ “ተፈወስን” ሲሉ ምነው የናንተ ዕጣ በደረሰልኝ እል ነበር፡፡

ስጸልይ እውነቱን ግለጽልኝ እውነቱን አሣየኝ እላለሁ ፡፡ አባቴ በእምነቱ ጠንካራና አስተማሪም ስለሆነ፣ እኔም በኃይማኖቴ ብዙ ነገር አውቃለሁ፡፡ ቁርዓን እቀራ ነበር፡፡ በገዳሙ ውስጥ እያለሁ አላህ ማረኝ እያልኩ እየጸለይኩኝ መዳኔን እጠባበቅ ነበር፡፡

በኃይማኖቴ ኡስታዝ /ብዙ ያወቁ መምህራን/ ይባላሉ፡፡ ቁራን ይቀራሉ ጸሎት ይደረጋል፡፡ ከዚያም የታወቁ የኃይማኖቶቹ አባቶች ጋር “ሂጂ” ተብዬ ነበር፡፡ ውጪ ሀገር ብዙ ስለተሰቃየሁ አልሄድም አልኩኝ፡፡ ጻድቃኔ ማርያም ግን ሞት ወይም መዳን ብዬ መጣሁ፡፡ ስመጣ በ2001 ዓ.ም በአተት ምክንያት ብዙ ሰው

> ሞቶ ስለነበር ብዙ ሰው አልነበረም፡፡ እኔ ግን ውስጤ ስለቆረጠ ሞትም ቢመጣ ፍርሃት አልነበረኝም፡፡ አመጣጤ ከጭንቀትና ከስቃይ ለመራቅ ነውና፡፡
>
> ክርስቲያኖቹ “ህልም ሣይታይ አይኬድም፡፡ ህልም ይታያል” ሲሉ አላምንም ነበር፡ ፡ በሄድኩኝ በሁለተኛው ቀን ራዕይ አይቼ ነበር፡፡ ራዕዩን ካየሁ በኋላ ራዕይ አይቼ ስለማላውቅና ስላልገባኝ በጣም ፈራሁ፡፡ ራሴን አውቃለሁ፡፡ የማየው ብርሃን ነገር ነው፡፡ ለማናገር ይከብደኛል፡፡ ብርሃኑን ማየት ይከብደኝ ነበር፡፡ ራዕዩን ካየሁ በኋላ እንደምድን አውቅ ነበር፡፡ ከራዕዩ በኋላ የገዳሙን ስርዓት አከብራለሁ፡፡ ሙስሊምም ብሆን አይመለከተኝም አልልም ነበር፡፡ አከብራለሁ፡፡
>
> ቤቴ እያለሁ በቀን አስር መርፌ እየተወጋሁ ነበር በሽታውን መቋቋም የምችለው፡፡ ካልተወጋሁኝ  ይጥለኝ ነበር፡፡ ሣልወጋ አላድርም ነበር ፡፡ ጻድቃኔ ማርያም ጸበል መጥቼ ግን መርፌ ሳልወጋ ነበር የቆየሁት ምንም አልሆንኩኝ፡፡ ይህ ለኔ ድንቅ ነው፡፡
>
> በስድስተኛው ቀን ጸበል ተጠምቄ ውዬ በምህላ ጸሎት ሰዓት ላይ ቁጭ ባልኩበት በህሊናዬ እጸልያለሁ ክርስቲያኖቹ አምነው የሚያውቀት ጸሎት ሲጸልዩ እኔም ፈጣሪዬ ፍጥረትህ አይደለሁምን? ማረኝ እያልኩ እጸልይ ነበር፡፡ የምጸልየው በኃይማኖቴ ነው፡፡ ስለ ኦርቶዶክስ እምነት እኔ ሆንኩ ቤተሰቤ አናውቅም፡፡ ኦርቶዶክስ ጓደኛም የለኝም፡፡ የምናውቀውም እኛ ቤት የተከራየችው አልማዝ እና ቤተሰቦቿን ነው፡፡ “እግዚኦ” እየተባለ ምህላው ሳያልቅ እግሬ በጣም ቀለለኝ ፊት እግሬን የሚያጥፍልኝ የሚዘረጋልኝ ሌላ ሰው ነበር፡፡ እግሬ በደንብ ተንቀሣቀሰ፡፡ ደንግጬ እስኪያልቅ ድረስ ከተቀመጥኩበት አልተነሣሁም ግን  ደጋግሜ እግሬን አንቀሣቅሰው ነበር፡፡ በዛን ሰዓት መቆምም እችል እንደሆነ አረጋገጬ ነበር፡፡ ምህላው ሲያልቅ ቆምኩኝ ተራመድኩኝ፡፡ ዓመት ያክል ያልተንቀሳቀሰልኝ እግሬ ብርቱ ሆኖ መቆም ቻልኩኝ  እንደማንኛዉም  ሰው መቆም ቻልኩ፡፡ ህመሜን ያወቁ ሁሉ ከበው ያዩኛል እመቤቴ ማርያምን ያመሰግኗታል፡፡ ወንድሜና እህቴ ጸሎቱ ሲያልቅ ሊሸከሙኝ ሲመጡ እኔ በእግሬ መሄድ ጀምሬያለሁ፡፡  ተደሰቱ ተላቀስን፡፡ የገዳሙ አባቶች ያጽናኑኝ  ሰለነበር፤ ጸሎቱ ሲያልቅ የተደረገልኝን ፈውስ ነገርኳቸው፡፡ እነሱም እግዚአብሔርን አመሰገኑ (የገዳሙ መጽሔት፣ 61-67)፡፡

የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነች ልጅ ተስፋ ከቆረጠችበት ተስፋ አግኝታለች፡፡ በተለያዩ ሀገራት ዞራ ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ ተነግሯታል፡፡ ሞትሽን ጠብቂ ተብላ ቤተሰብ ሀዘን ውስጥ ገብቷል፡፡ ነገር ግን የክርስትና ተከታይ በሆነች ተከራያቸው ወደ ገዳሙ ተጠራች፡፡ መለኮታዊው ጥሪ ገዳሙን በተዓምር እና በተረክ እንጂ በአካል በማታውቀው ሴት ተላለፈላት፡፡  ቤተሰቦቿ “አይሆንም” ቢሉም  መዳኗን  ይፈልጋሉ እና ያመኑበት እና አቅማቸውን ያፈሰሱበት ሁሉ ተስፋ አስቆራጭ ስለነበር ለቀቋት፡፡ ወደ ጸበሉ መጥታ እምነቷ ባይሆንም የገዳሙን ስርዓት እያከበረች ተጠመቀች፡፡ ለዓመታት ያሰቃያት የነበረው በሽታ  በገዳሙ ውስጥ በሚደረገው የምህላ ጸሎት ላይ ለቀቃት፡፡ ሊሸከሟት የመጡት አስታማሚዎች አለቀሱ፡፡ በእግሯ  መራመድ ቻለች፡፡ ይህ ተረክ ከኃይማኖታዊ ፋይዳው በተጨማሪ ማኅበራዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነው፡፡ የፍውሷ ልጅ የሌላ ኃይማኖት ተከታይ መሆን እና በስፍራው ሆና በእምነቷ መሰረት ጸሎት (ዱኣ)

ስታደርግ በዚህ መንገድ ጸልዪ ብሎ ያስገደዳት ወይም ጣልቃ የገባባት አልነበረም፡፡ ይህም ሲተላለፍ የመጣውን የኃይማኖት መቻቻልና ማኅበራዊ ቁርኝት የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

ይህ ተረክ በገዳሙ ውስጥ መተረኩ በገዳሙ ጸበል የማይድን በሽታ እንደሌለ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የልጅቱ የሌላ እምነት ተከታይ መሆን ደግሞ ገዳሙ ፈውስ ፈልገው ለሚመጡ ሁሉ የቅድስት ድንግል ማርያምን በረከት የሚያገኙበት ስፍራ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የሁሉም እምነት ተከታዮች ፈውስ የሚያገኙበት ከሆነ ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ስፍራ ቢሆንም ሁሉም ሰዎች በጋራ ይጠቀሙበታል፡፡ የልማት ስራውን በመደገፍም እንዲተባበሩ ያደርጋል፡፡

በአጠቃላይ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን ገዳም ውስጥ የሚተረኩት የፈውስ ተረኮች፣ ውስጥ ፍውስ ሰዎቹ በተለያየ መንገድ ተጠርተው፣ ከተለያየ የእምነት ተቋም መጥተው፣ በተለያየ መንገድ ከበሽታዎቻቸው ፈውስ እንዳገኙ ያሳያሉ፡፡ በዘመናዊ ህክምና አይድኑም የተባሉ በሽታዎች ኤች አ ይ ቪ እና ካንሰር በገዳሙ ጸበል እንደሚድኑ ይተርካሉ፡፡ ሰዎች በራሳቸው እምነት መጥተው ለራሣቸውም ሆነ በውጪ ለሚኖር ሰው ቢጸልዩ እና እምነትና ጸበሉን ይዘው ቢሄዱ ፈውስ እንደሚያገኙ ያስረዳሉ፡፡ ይህም የጻድቃኔ ማርያም እምነትና ጸበል የማዳን ኃይል በቦታ የተወሰነ አለመሆኑን ያሳያል ማለት ይቻላል፡፡

እነዚህ ተረኮች መተረካቸው በእምነቱ ውስጥ ያሉ ሰዎች በእምነታቸው እንዲጸኑ፣ ከእምነቱ ውጪ ያሉ ሰዎች የቅዱሱን ስፍራ ኃይል እንዲያምኑ፣ የታመሙ ወደ ገዳሙ በመሄድ ፈውስ እንደሚያገኙ እንዲያምኑ ያደርጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሁሉም እምነት ተከታዮች ለገዳሙ ጥበቃና ድጋፍ እንዲሰጡ ያስችላል፡፡ የገዳሙ መነኮሳት በገዳማቸው ውስጥ ይህ ተዓምር መፈፀሙ፣ በሽተኞች መፈወሣቸው በጾም፣ በጸሎት፣ እና በተመስጦ እንዲጸኑ ድጋፍ ይሆናቸዋል፡፡ ፍውስ ግለሰቦቹ ሁሉ ሲድኑ የገዳሙን ህግ አክብረው ስለሆነ አሁን በገዳሙ ያሉ ጸበልተኞች እና ወደ ገዳሙ የሚመጡ ሰዎች የገዳሙን ስርዓትና ደንብ እንዲያከብሩ በማድረግም አስተዋጽኦ አለው፡፡

## 5. ማጠቃለያ

በጥናቱ እንዳየነው በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩ ተረኮች እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ በአምስት ተከፍለው ቀርበዋል፡፡

የአመሠራረት ተረኮቹ አሁን በገዳሙ ዋሻ ውስጥ ተሰውሮ አለ ተብሎ ስለሚታመነው ታቦትና ንዋየ ቅድሳት ስደት እና የገዳሙ ምስረታ የተቃኘበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ታቦቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በስደቱ ወቅት በቁስቋም ሳለ ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ከገባበት ከግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም ቤተክርስቲያን የመጣ መሆኑ፣ በኢትዮጵያ እና በግብጽ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ያለውን የቅድስና ሽሚያ ያሳያል፡፡ ከግብጽ ለመሰደዱም ሆነ ከኢትዮጵያው ደብረ ምጥማቅ ወጥቶ ገዳሙ ዋሻ ውስጥ ለመሰወሩ ምክንያቱ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች መነሳታቸው ነው፡፡ ይህም ታቦቱ ከእግዚአብሔር የተፈቀደና ጠላት ቢነሳ እንኳን ለአደጋ እንደማይጋለጥ ያሳያል፡፡ ጉዞው በተአምር የታገዘና መለኮትና ስጋ(ሰው) እየተነጋገሩ የተካሄደ መሆኑ የታቦቱን ታላቅነት ያሳያል፡፡ ይህ ታላቅ ታቦት በገዳሙ ዋሻ ውስጥ እንዳለ መታመኑ ደግሞ መነኮሳቱ በገዳማቸው ውስጥ በእምነት ጸንተው እንዲቆዩ፤ ምዕመናን ከተለያየ ቦታ ወደ ገዳሙ እየሄዱ የበረከት ተካፋይ እንዲሆኑ፤ በተለያየ መንገድ ለገዳሙ እድገት አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ስለ ገዳሙ ምንም የተጻፈ መዝገብ ባይገኝም ተረኮች ስለገዳሙ ተሸክመው ለዳግም ምስረታ በመብቃቱ፣ ተረኮች ለአንድ ማኅበረሰብ መልሶ መቋቋም ወይም ለአንድ ስፍራ ዳግም ምስረታ ያላቸውን ፋይዳ የሚያሳይ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአመሠራረት ተረኮቹ አመሠራረቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተያያዥነት እንዳለው በማሳወቅና የስፍራውን ቅድስና በማጉላት በኩል ከፍተኛ ፋይዳ አላቸው፡፡

ሁለተኛው ክፍል ላይ የቀረቡት ተረኮች የገዳሙን ቅድስና የሚያሳዩ ተረኮች ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት ገዳሙ ከመመስረቱ አስቀድሞ ንጉስ ካሌብ የጸለዩበትና ትንቢት የተናገሩለት መሆኑ፤ የተመረጠው ቅድስት ድንግል ማርያም ለንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ በቀስተ ደመና አመላክታቸው በመሆኑ፣ ቅድስት ድንግል ማርያም ቦታው ላይ መጥተው ቢጸልዩ ልትገለጥና ልትታይ ቃል የገባችበት(ለት) ቦታ መሆኑ፤ ከግብጽ ደብረ ምጥማቅ ማርያም የመጣው ታቦትና ንዋየ ቅድሳት በገዳሙ ዋሻ ውስጥ የተሰወረ መሆኑ እና የቅዱሳን አፅም ያረፈበት ቦታ መሆኑ የገዳሙን ቅድስና የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮች መተረካቸው ገዳማውያኑም ሆኑ ምዕመናኑ የቦታውን ቅድስና ተገንዝበው የገዳሙን ህግና ሥርዓት እንዲያከብሩ እና ለገዳሙ ክብር እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡

ሌላው ክፍል ትንቢታዊ ተረኮች የተተነተኑበት ሲሆን እነዚህ ተረኮችም የታቦቱና ንዋየ ቅድሳቱ መገለጥ እና የገዳሙ መግነንና የአካባቢው ማደግ በሚሉ ሁለት ክፍሎች ታይተዋል፡፡ በተረኮቹ መሰረት ቀንና ሰዓቱ በውል ባይታወቅም ወደፊት የተሰወረው ታቦትና ንዋየ ቅድሳት እንደሚገለጡ ይታመናል፡፡ ይህ መገለጥ ደግሞ የአካባቢው ማደግ ምክንያት ይሆናል፡፡ መቼ ለሚለው ጊዜውን በውል ባያስቀምጡም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም ፍጻሜ መቼ እንደሚሆን በምልክት እንደተናገረ(ማቴ፣ 24) እነሱም የመገለጡ ጊዜ ሲደርስ የሚታዩትን ምልክቶች ይናገራሉ፡፡ ትንቢታዊ ተረኮቻቸው እንደሚፈፀሙ ለማሳመንም ከአሁን በፊት የተነገሩና አሁን እውን የሆኑ ትንቢቶችን በማስረጃነት ያነሳሉ፡ ፡ እነዚህ ተረኮች መተረካቸው ገዳሙ ለሚከውናቸው የልማት ስራዎች የአካባቢው ማህበረሰብና አስተዳደር አዎንታዊ ምላሽ እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የአካባቢው ነዋሪዎች እድገታቸውን በገዳሙ መግነን እና በታቦቱ መገለጥ ላይ መስርተው ታዛዥ እንዲሆኑ የማድረግ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ገዳማውያኑ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ጤነኛ ግንኙነት እንዲኖራቸው አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

ሌላው የመንግስትና ኃይማኖትን ትስስር የሚያሳዩ ተረኮች የተተነተኑበት ክፍል ነው፡፡ ገዳሙ በንጉስ ዘርዐ ያዕቆብ ሲመሰረት ለነበረው ሰፊ ግዛት እና ለደብረ ምጥማቅ ማርያም ለተመደቡት በርካታ አገልጋዮች ንጉሱ እንደ ንጉስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው፡፡ በዐፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግስት የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ለመውረር ሲመጣ፣ ንጉሱ መፍትሄ ፍለጋ የላኩት ወደ ደብረ ምጥማቅ ነበር፡፡ ከዚያም መፍትሄ አግኝተዋል፡፡ በስፍራውም እስካሁን ድረስ የተመረጡ ግዜዎች ላይ ለመንግስት እና ለህዝብ ጸሎት ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወደፊት ከታቦቱ መገለጥ ጋር የሚነሳ መንግስት እንዳለ እና መቀመጫውም ሰላ ድንጋይ እንደሚሆን ይነገራል፡፡ እነዚህ የመንግስትን እና የኃይማኖትን ትስስር የሚያሳዩ ተረኮች መነገራቸው ገዳሙ ከመንግስት አካላት የሚያስፈልገውን ድጋፍ እንዲያገኝ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡ መንግስት ለኃይማኖት ብቻ ሳይሆን ኃይማኖትም ለመንግስት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ እንዳለ ያስገነዝባሉ ማለት ይቻላል፡፡

የመጨረሻው ክፍል የፈውስ ተረኮች የታዩበት ሲሆን፤ በተረኮቹ ውስጥ ያሉት ፍውስ ሰዎች በተለያየ ጥሪ፣ ከተለያየ ስፍራ፣ ከተለያየ የኃይማኖት ተቋም የመጡ እና በተለያየ መንገድ ከተለያየ በሽታ የተፈወሱ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ገዳሙ ቅጥር ሳይዘልቁም በገዳሙ እምነትና ጸበልም ፈውስ ተገኝቷል፡፡ እነዚህ ተረኮች መተረካቸው ገዳማውያኑ እና ምዕመናኑ በገዳሙ ላይ ያላቸውን እምነት እንዲያፀኑ ያደርጋል፡፡ የሌላ ኃይማኖት

ተከታዮች እዚህ ቦታ ፈውስ እንደሚያገኙ መነገሩም ሁሉም ማኅበረሰብ የገዳሙ ጠባቂ እና ተባባሪ እንዲሆን የማድረግ ፋይዳ አለው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ተረኮቹ የተለያዩ የኃይማኖት ተከታዮች መካከል ያለውን ማኅበራዊ ትስስር ያስቀጥላሉ፡፡ የተፈወሱት ሰዎች የገዳሙን ህግና ስርዓት አክብረው በመሆኑ ተረኮቹ የገዳሙን ህግና ሥርዓት እንዲጠበቅ የማድረግ ፋይዳም አላቸው ማለት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በጻድቃኔ ማርያም መካነ ቅዱሳን አንድነት ገዳም የሚነገሩት ተረኮች የገዳሙን ቅድስና በማሳየት፤ የገዳሙ ህግና ስርዓት እንዲከበርና እንዲጠበቅ የማድረግ፣ የገዳማውያኑን እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ግንኙነት ጤናማ እንዲሆን የማድረግ፣ ገዳማውያኑ እና ምዕመናኑ በእምነታቸው እንዲፀኑ እና እንዲጠነክሩ የማድረግ፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እና የሌሎች እምነት ተከታዮች የገዳሙ ጠባቂ፣ ተቆርቋሪና ደጋፊ እንዲሆኑ የማድረግ ፋይዳ አላቸው፡፡ በገዳሙ ለሚከወነው የልማትና የመስፋፋት ስራም የተቃና ይሆን ዘንድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

## ማጣቀሻ ጽሁፎች


ሀገሬ ሚዲያ ኮሙኒኬሽን፡፡ *የሰሜን ሸዋ ዞን የቱሪዝም ማውጫ፡፡* አዲስ አበባ፣ ማስተር ማተሚያ ቤት፣ 2006 ዓ.ም.፡፡

ሐረገወይን አገዘ እና እሸቱ ታደሰ፡፡ *ነገረ ማርያም፡፡* አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ቤት፣ 1996 ዓ.ም.፡፡

መንግስቱ ጎበዜና አሳምነው ካሳ፡፡ *የቤተ ክርስቲያን ታሪክ*(ቁጥር 2)፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፣ 2000 ዓ.ም.፡፡

ምህረት ተስፋዬ፡፡ "ከጣና ቂርቆስ የአንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ሞገስ ጀንበር፡፡ "ከዳጋ እስጢፋኖስ አንድነት ገዳም አመሰራረት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ተረኮችና አምልኳዊ ሥርዓቶች"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣2003 ዓ.ም፡፡

ሮዳስ ታደሰ፡፡ *ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ቁ.1፡፡* አዲስ አበባ፣ ካፍ ማተሚያ ቤት፣ 2003 ዓ.ም.፡፡

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፡፡ "የአማርኛ የአማርኛ መዝገበ ቃላት"፡፡ አዲስ አበባ፣ 1981(ያልታተመ)፡፡

ሥርግው ገላው፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ በአለቃ ተክለ ኢየሱስ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 2002 ዓ.ም.፡፡

ሳሙኤል ተስፋዬ፡፡ *የዘርዐ ያዕቆብ እመቤት ጻድቃኔ ቅድስት ማርያም* (ቁጥር 2) *መፅሔት፡፡* አዲስ አበባ፣ አኮትት አታሚዎች፣ 2005ዓ.ም.፡፡

በላይ ተገኝ፡፡ *ግሸን ደብረ ከርቤ የቃል ኪዳን አምባ ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 1996ዓ.ም፡፡

ተስፋ ገብረ ሥላሴ፡፡ *ተዓምረ ማርያም፡ ግዕዝና አማርኛ፡፡ አዲስ አበባ*፣ በተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 1988ዓ.ም.፡፡

ተስፋዬ ተገኝ፡፡ "በደብረ ነጎድጓድ ሐይቅ እስጢፋኖስ አቡነ ኢየሱስ ሞአ አንድነት ገዳም አመሰራረትና ቁሳዊ ባህል ጥናት"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣ 2003 ዓ.ም፡፡

ተክለፃድቅ መኩሪያ፡፡ *አፄ ምኒሊክ እና የኢትዮጵያ አንድነት*፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1983ዓ.ም.፡፡

________________፡፡ *የግራኝ አህመድ ወረራ፡፡* አዲስ አበባ፣ ብርሀንና ሰላም ቀ.ኃ.ሥ ማተሚያ ቤት፣ 1966ዓ.ም.፡፡

________________፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ*፡፡ አዲስ አበባ፣ በትንሳዔ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 1949ዓ.ም.፡፡

________________፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኑ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል* ፡፡ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 1966ዓ.ም.፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ *በይነ ዲሲፕሊናዊ የስነ ጽሑፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2001ዓ.ም.፡፡

ቴዎድሮስ ይበልጣል፡፡ "የደብረ ወርቅ ማርያም ገዳም አመሰራረት እና በገዳሚ ዙሪያ የሚነገሩ ተረኮች ይዘት ትንተና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣ 2005 ዓ.ም፡፡

ኅሩይ ወልደሥላሴ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግሥተ ሳባ እስከ ታላቁ የአድዋ ድል፡፡* አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ 1999 ዓ.ም.፡፡

አበበ ኃይለመለኮት፡፡ *የአድዋ ድልና የኢትዮጵያ ጀግኖች ውለታ፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1991ዓ.ም.፡፡

አበበ ኃይሌ፡፡ *ትምህርተ ተዋሕዶ፡፡* አዲስ አበባ፣ አፍሮ ማተሚያ ድርጅት፣2005ዓ.ም.፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948 ዓ.ም.፡፡

ወርቁ ከተማ፡፡ *"የሌሙና ቢልቢሎ ወረዳ የጨፋ መድኃኔዓለም ደብረ ቁስቋም ቅድስት ማርያምና ቅድስት ሰሎሜ የሴቶች አንድነት ገዳም አመሰራረትና ፎክሎራዊ ገጽታ"፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣ 2000 ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡* አዲሰ አበባ፣ 2001ዓ.ም.፡፡የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ *መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡* አዲሰ አበባ፣ 2001ዓ.ም፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡፡ *ድርሳነ ዑራኤል፤ ግዕዝና አማርኛ፡፡* አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 1991 ዓ.ም.፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፡፡ *ተአምረ ማርያም፤ ግዕዝና አማርኛ፡፡* አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ፣ 1989 ዓ.ም.፡፡

ዮናስ አድማሱ፡፡ አስረኛንኩዋ?፤ ሀዲስ አለማየሁና የማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው፤ የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ ጽሑፍ መጽሔት፣ ቁጥር 10፡፡ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1992 ዓ.ም.፣ ገፅ 77-119፡፡

ጋስፓሪኒ ጉ-ማ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፡፡* አዲስ አበባ፣ ሸዋ ማተሚያ ቤት፣ 1952 ዓ.ም፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነ ቃል መምሪያ፡፡* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1991 ዓ.ም፡ ፡

ፍስሐ ያዜ፡፡ *የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖህ እስከ ኢሀአዴግ፡፡* አዲስ አበባ፣ ሕትመት አልፋ አሳታሚዎች፣ 2003ዓ.ም.፡፡

*ፍካሬ ኢየሱስ ወትንቢተ ነቢያት፡፡* 4ኛ ዕትም፣ አዲስ አበባ፣ 1991 ዓ.ም.፡፡

ፍፁም ኩራባቸው፡፡ "የዝዋይ ደስያት ገዳምና አድባራት ተረኮችና ቁሳዊ ባህሎች ጥናት"፡፡ አዲስ  አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ፣ 2006 ዓ.ም፡፡

Barthes, R. and Lionel, D. “An Introduction to the Structural Analysis of Narrative.” *NewLiterary History*. Vol. 6, no. 2 (1975): 237-272.

Bascom, William. “Four Functions of Folklore”. *The Journal Of American Folklore*; Vol.67,No.266, PP. 333-349, Jan-Mar, 1965, pp. 3-20.

______________. “The Form of Folklore Prose Narretives”. *The Journal Of American Folklore.* Vol.78,No.302.

Danielson, Larry. ”Religious Folklore” In *Folk Groups And Folk Genres: An Introduction*. Logon; Utah State University Press, 1986.

Davis, Ash J. “The Church-State Ideal In Ethiopia” In IBADAN Journal. No 21, October 1965, p 47-52.

Degh, Linda. “Oral Folklore, Oral Narretives”. In *Folklore And Folklife*; Richard M. Dorson(ed) Chicago And London; The University of Chicago Press, 1972.

Dorson, Richard. *Folklore And Folklife*: An Introduction. Chicago; The Univeresity of Chicago Press, 1972.

Finnegan, Ruth. *Oral Tradition And The Verbal Arts*. London And Newyork; Routledge,1992.

Goldstein, Kenneth. *A Guide For Field Work in Folklore*. Habtboru; Published By Gale Research Company, 1964.

Lauri Harvilahti. Folklore and Oral Tradition. In Journal of *University of Helsinki Oral Tradition*, 18/2 (2003): 200-202.

Jhon C. Messenger “Oral Folklore, Oral Narretives”. In *Folklore And Folklife*; Richard M. Dorson(ed) Chicago And London; The University of Chicago Press, 1972.

Oring, Elliot. *Folk Groups And Folk Genres*: *An Introduction*. Logan; Utah State University Press, 1986.

Sims, Martha C. And Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction To The Study of People And Their Tradition.* Logan; Utah State University Press, 2005.

Taddesse Tamrat. *Churh And State In Ethiopia*. Oxford Clarendon Press, 1972.

*Virve Sarapik.* "RAINBOW, COLOURS AND SCIENCE MYTHOLOGY", FOLKLORE. Electronic Journal of Folklore. www.folklore.ee/folklore/vol6/rainbow.htm, Pages in printed version 7-19, Folklore 6 1998.